

# ድርሳነ፡ ዑራኤል ።

## ግዕዝና ፥ አማርኛ ።

መልክአ ፥ ዑራኤል ፥ በግዕዝ ።

ኣዲስ ፥ አበባ ፥ ግንቦት ፲፱፻፺፩ ዓ/ም

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ



ለ ዕ ዝ ራ ፡ (ነ ቢ ይ) ፡ ሱ ቱ ኤ ል ።
ጽዋዐ፡ልቡና፡ዘከመ ፡ አስተዮ፡ኡራኤል ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ
ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

ኢሳይያስ ። ዘይቤ ፡ ናሁ ፡ ድን ግል ፡ ትፀንስ ፡ ወትወልድ ፡ ወልደ ፡ ወትሰምዮ ፡ ስሞ ፡ ዐማኑኤል ።

፵፪ ፤ ወእምዝ ፡ አውሥአ ፡ ባዚን ፡ ንጉሥ ፡ ለአኪን ፡ ወይቤሎ ፡ በአይቴ ፡ ሀገር ፡ ትወልድ ፡ ይቤ ።

፵፫ ፤ ወአውሥአ ፡ አኪን ፡ ወይቤሎ ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ዘይሁዳ ።

፵፬ ፤ ወናሁ ፡ መጽአ ፡ ውስተ ዛቲ ፡ ሀገርከ ፡ አኰሱም ፤ ከመ ፡ ይባርክ ፡ አድባራቲሃ ፤ ወበሐውርቲሃ ፡ ወገዳማቲሃ ፤ ወይሬስያ ፡ እስከ ፡ ሕልቀተ ፡ ዓለም ፡ ማኅደረ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ወመካነ ፡ አግብርቲሁ ፡ እለ ፡ ይሜህሩ ፡ በጽድቅ ፡ ሃይማኖተ ፡ ሥላሴ ፡ ቅድስት ።

፵፭ ፤ ወከመ ፡ ተወልደ ፡ በሕቱም ፡ ድንግልና ፡ ሥጋ ፡ ዘእንበለ ፡ አርኅዎ ፡ ሥጋሃ ፡ በጥበበ ፡ መለኮቱ ፡ እግዚአ ።

፵፮ ፤ በከመ ፡ ተነበየ ፡ ሕዝቅኤል ፡ ወአስተርአየ ፡ ወተናገረ ፡ ብሂሎ ፡ ርኢኩ ፡ ኖኀተ ፡ በምሥራቅ ፤ ወቦአ ፡ ውስቴታ እግዚአ ፡ ብርሃናት ፡ ወወፅአ ፡ እንዘ ፡ ኅትምት ፡ ይእቲ ፡ ኖኅታ።

ኤል ፡ ትለዋለች ፡ ሲል ፡ ኢሳይያስ ፡ በትንቢቱ ፡ ከተናገረው ቃል ፡ ለንጉሡ ፡ ለባዚን ፡ አነበበለት ።

፵፪ ፤ ንጉሡ ፡ ባዚንም ፡ በወዴት ፡ አገር ፡ ትወልዳለች ፡ ይላል አለው ።

፵፫ ፤ የካህናቱ ፡ አለቃ ፡ አኪንም ፤ በይሁዳ ፡ አገር ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ነው ፡ አለው ።

፵፬ ፤ በእውነት ፡ በቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ሃይማኖት ፡ ለሚያስተምሩ ፡ ወገኖቹ ፡ ሁሉ ፡ መኖሪያ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ የጌትነቱ ፡ ማደሪያ ፡ ሲያደርጋት ፡ ገዳሞችዋንና ፡ ተራሮቿን ፡ አድባራቷንም ፡ ሁሉ ፡ ይባርክ ፡ ዘንድ እነሆ ፡ አሁን ፡ መጥቷል ።

፵፭ ፤ በመለኮታዊ ፡ ጥበቡ ፡ ማኅተመ ፡ ድንግልናዋን ፡ ሳይለውጥ ፡ ከማርያም ፡ በኅቱም ፡ ድንግልና ፡ እንደተወለደ ።

፵፮ ፤ ነቢዩ ፡ ሕዝቅኤል ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ የተቆለፈች ፡ ደጃፍ ፡ አየሁ ፡ በዚያችም ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ የብርሃናት ፡ ጌታ እንደተቆለፈች ፡ ገብቶ ፡ እንደ ተቆለፈች ፡ ሲወጣ ፡ አየሁ ፡ ብሎ ፡ በትንቢቱ ፡ እንደተናገረ ።



፵፯ ፤ ወይእቲኒ ፡ ከማሁ ፡ ኢተርኅወ ፡ ማኅተመ ፡ ድንግልናሃ በወሊደ ፡ መለኮት ።

፵፰ ፤ በኃይለ ፡ ጥበቡ ፡ ረሰያ፡ ትለዶ ፡ በሥጋ ፡ ንጹሕ ፡ እምኃጢአት ።

፵፱ ፤ ወአጽንዓ፡ ከመ ፡ ትጹሮ በማኅፀና ፡ ዘኢያገምሮ ፡ ኃያለ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ፡ ወዘኢይክል ጾሮቶ ፡

፶ ፤ ወእንዘ ፡ ይትናበብ ፡ ባዚን ንጉሥ ፡ ምስለ ፡ አኪን ፡ ሊቀ ካህናት ፡ ይቤ ፡ ወልድየ ፡ ሶቤሃ ፡ እ ፡ እምየ ፡ ተንሥኢ ፡ እምዛቲ፡ ሀገር ፡ ወአርእየኪ ፡ ካልአነ ፡ አኅጉራተ ፡ ዘእሁበኪ ፡ ዐሥራተ ፡ በአምሳሊሃ ፡ ለዛቲ ፡ ሀገር

፶፩ ፤ ወሶቤሃ ፡ ተንሥእኩ ፡ ወመጻእኩ ፡ ደመና ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ዘጸላተ ፡ ሙሴ ወተዐዕንኩ ፡ ምስለ ፡ ወልድየ ፡ ወዮሴፍ ፡ ወሰሎሜ ።

፶፪ ፤ ወእሉሰ ፡ ሠለስቱ ፡ እና ብስት ፡ ዘተለውነ ፡ እምሀገረ ፡ ግብጽ ፡ ሐለፉ ፡ በታሕቴነ ።

፶፫ ፤ ባዚን ፡ ንጉሥ ፡ ወአኪን ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ወሠራዊተ ፡ ባዚን ፡ ወካህናቲሃ ፡ ለታ

፵፯ ፤ እስዋም ፡ አምላክን ፡ በመውለድዋ ፡ ማኅተመ ፡ ድንግልናዋ ፡ አልተለወጠም ።

፵፰ ፤ በጥበቡ ፡ ብዛት ፡ ከኃጢአት ፡ ንጹሕ ፡ በሆነ ፡ ሥጋ፡ እንድትወልደው ፡ አደረጋት ፡ እንጂ ።

፵፱ ፤ ሁለተኛም ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ኃይላት ፡ ሊሸከሙ ፡ ትና ፡ ሊወስኑት ፡ የማይቻላቸውን በማኅፀኗ ፡ ትወስነው ፡ ዘንድ ፡ አጸናት ፡ እንጂ ።

፶ ፤ ንጉሡ ፡ ባዚን ፡ ከሊቀ ፡ ካህናት ፡ ከአኪን ፡ ጋር ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሚነጋገሩበት ፡ ጊዜ ፡ ልጄ ፡ እናቴ ፡ በዚች ፡ አገር ፡ አምሳያ ፡ ላንቺ ፡ ዐሥራት ፡ አድርጌ ፡ የምሰጥሽን ፡ አገሮች ፡ አሳይሽ ፡ ዘንድ ፡ ከዚች ፡ አገር ፡ ተነሺ ፡ አለኝ ።

፶፩ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ የሙሴ ፡ ጸላት ፡ ከአለችበት ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ደመና ፡ መጣና ከልጄና ፡ ከዮሴፍ ፡ ከሰሎሜም፡ ጋር ፡ በደመና ፡ ተጭነን ፡ ለመሄድ ፡ ተነሣን ።

፶፪ ፤ እነዚያ ፡ ከግብጽ ፡ ተከትለውን ፡ የመጡ ፡ ሦስቱ ፡ አንበሶች ፡ ግን ፡ ከኛ ፡ በታች ፡ (በምድር ፡ ላይ ? ) ይሄዱ ፡ ነበር

፶፫ ፤ ንጉሡ ፡ ባዚንና ፡ ሊቀ ካህናቱ ፡ አኪን ፡ የንጉሡ ፡ የባዚን ፡ ሠራዊትና ፡ የታቦተ ፡ ጽዮን

፱ ፤ ወኮኑ ፡ አሥራዊሁ ፡ ፫ተ
፻ተ ፡ ፲ተ ፡ ወ፰ተ ፡ ዘአውፅኦሙ
እምሥርወ ፡ ውእቱ ፡ ዕፅ ።

፲ ፤ ወይቤለኒ ፡ ንዒኢ ፡ አሐዱ
ሥርወ ፡ ህንኪ ፡ እምየ ፡ ብልዒ ፡
ዘንተ ፡ ሥርወ ፡ ዕፅ ።

፲፩ ፤ ወአውሣእክዎ ፡ ለወ
ልድየ ፡ እንዘ ፡ እብል ፡ ሶቤሃ
አ ፡ ወልድየ ፡ ይመርረኒ ፡ እስመ
ኢለመድኩ ፡ በሊዓ ፡ ዕፅ ፡ ዘእ
ንበለ ፡ ሥርናይ ፡ ዕራቅ ።

፲፪ ፤ ወይቤ ፡ ዘይመርረኪ ፡
ዝንቱ ፡ ዕፅ ፡ ሀለው ፡ ዘይበልዕዎ
መነኮሳት ፡ ቅዱሳን ፡ ወይጥ
ዕሞሙ ፡ እመዓር ፡ ወሦከር ።

፲፫ ፤ ስምዒ ፡ ወጽልዊ ፡ እዝ
ነኪ ፡ ከመ ፡ ታጽምዒ ፡ ዘእነግረኪ

፲፬ ፤ በደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ ይመ
ጽኡ ፡ ብዙኃን ፡ መነኮሳት ፡
እምበሐውርቲሆሙ ፡ ውስተ ፡
ዛቲ ፡ ገዳም ፡ ወይነብሩ ፡ ውስቴታ ፡
እለ ፡ ያከብሩኪ ፡ በስብሐት ፡
ወበውዳሴ ፡ ወይዘክሩ ፡ ስመኪ ።

፲፭ ፤ ወአመ ፡ ተሰምዓ ፡ ዜና ፡
ወሊዶትኪ ፡ የአምኑ ፡ ቅድመ ፡
እምሰብአ ፡ ኢትዮጵያ ፡ወሰብአ
ትግራይ ፡ ወ ጐዣም ።

፱ ፤ ከእንጨቱም ፡ ውስጥ ፡
ያወጣቸው ፡ ሥሮች ፡ ሦስት ፡ መቶ
አሥራ ፡ ስምንት ፡ ሥሮች ፡ ነበሩ።

፲ ፤ አንዱን ፡ ሥር ፡ አንሥቶ
እናቴ ፡ ይህን ፡ የእንጨት ፡ ሥር
እንቺ ፡ ብይው ፡ አለኝ ።

፲፩ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ልጄ ፡ ሆይ
ከስንዴ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ እንጨት
መብላትን ፡ አለመድሁምና ፡ ይመ
ረኛል ፡ ብዬ ፡ መለስሁለት ።

፲፪ ፤ ይህ ፡ ይመረኛል ፡ የም
ትይው ፡ የእንጨት ፡ ሥር ፡ ከ
ማር ፡ ከሱካር ፡ ይበልጥ ፡ እየጣ
ፈጣቸው ፡ የሚመገቡት ፡ ቅዱ
ሳን ፡ መነኰሳት ፡ አሉ ።
አለኝ ።

፲፫ ፤ የምነግርሽን ፡ ታስተ
ውይ ፡ ዘንድ ፡ ጆሮሽን ፡ አንቅ
ተሽ ፡ ስሚኝ ።

፲፬ ፤ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ስምሽን
የሚጠሩ ፡ በፍጹም ፡ ምስጋና ፡
አንቺን ፡ የሚያከብሩ ፡ ብዙ ፡ መነ
ኰሳት ፡ ከየሀገራቸው ፡ መጥ
ተው ፡ በዚች ፡ ገዳም ፡ ውስጥ
ይኖራሉ ።

፲፭ ፤ እኔን ፡ የመውለድሽ ፡
ዜና ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮ
ጵያ ፡ ከሚኖሩ ፡ ማለት ፡ ከትግ
ራይና ፡ ከጐጃም ፡ ሰዎች ፡ አስ
ቀድመው ፡ ያምናሉ ።



፲፮ ፤ ወበደኃሪ ፡ መዋዕል ፡
ይመጽኡ ፡ እምኵሎሙ ፡ በሐ
ውርቲሃ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ወይሜ
ንኑ ፡ ዓለመ ፡ ምድረ ፡ ኃላፌ ፡
ወይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ገዳም ፡

፲፯ ፤ ወካዕበ ፡ ይመጽኡ ፡ እም
ሰብአ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በእንቲአየ ፡
ወበእንተ ፡ ፍቅረ ፡ ዚአኪ ፡ ወይ
ሁቡ ፡ ዐሥራተ ፡ እምብዕሎሙ
ለዛቲ ፡ ገዳም ።

፲፰ ፤ ወአነሂ ፡ አድኅኖሙ ፡
እምእኩይ ፡ ገር ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡
ኃላፌ ፡ ወእሞተ ፡ ሲኦል ፡ በእ
ንተ ፡ ስምኪ ።

፲፱ ፤ ወእንዘ ፡ ይትናገረኒ ፡
ዘንተ ፡ ነገረ ፡ መጽኡ ፡ ብነ ፡
አናብስት ፡ ግሩማን ፡ እምውስተ
ገዳም ፡ ወሶቤሃ ፡ ሰፍሐ ፡ እደ
ዊሁ ፡ ወልድየ ፡ ወይቤሎሙ ፡
ለእሉ ፡ አናብስት ፡ ንዑ ፡ ስግዱ ፡
ቅድሜሃ ፡ ለእምየ ፡ ወቅረቡ ፡
ኀቤሃ ፤ ወቀርቡ ፡ ኀቤየ ፡ ወሰገዱ
ሊተ ።

፳ ፤ ወነበቡኒ ፡ በልሳነ ፡ ሰብእ
እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ሰላም ፡ ለኪ ፡
አ ፡ እሙ ፡ ለፀሐየ ፡ ጽድቅ ፡
አምላክነ ፡ ወፈራቂነ ።

፳፩ ፤ ወአንፈርዓጹ ፡ በፍሥሐ
እንዘ ፡ ይቀንጹ ፡ ላዕለ ፡ ወይጥ
ሕሩ ፡ ታሕተ ፡ ምድር ፡ በአፉ
ሆሙ ፡ ቅድሜየ ፡ ከመ ፡ ያንፈ

፲፮ ፤ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ኃላፊ ፡
የሆነውን ፡ ዓለም ፡ እየናቁ ፡ ከኢ
ትዮጵያ ፡ አውራጃዎች ፡ መጥ
ተው ፡ በዚች ፡ ገዳም ፡ ውስጥ ፡
ይኖራሉ ።

፲፯ ፤ ዳግመኛም ፡ ስለእኔና
ስላንቺ ፡ ፍቅር ፡ የኢትዮጵያ ፡
ሰዎች ፡ እየመጡ ፡ ለዚችው ፡
ገዳም ፡ ከገንዘባቸው ፡ ዐሥራትን፡
እያወጡ ፡ ይሰጣሉ ።

፲፰ ፤ እኔም ፡ ስለስምሽ ፡
ከዚህ ፡ ከኃላፊው ፡ ዓለም ፡ ከፉ
ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከሲኦልም ፡ መከራ
አድናቸዋለሁ ።

፲፱ ፤ እንዲህም ፡ እያለ ፡ በሚ
ነግረኝ ፡ ጊዜ ፡ ግሩማን ፡ አናብ
ስት ፡ ወደኛ ፡ መጡብን ፡ ልጄ
ግን ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ እናንት፡
አንበሶች ፡ ኑ ፡ ከእናቴ ፡ ዘንድ
ቀርባችሁ ፡ ከፊቷ ፡ ስገዱ ፡ አላ
ቸውና ፡ እነሱም ፡ ወደኔ ፡ ቀር
በው ፡ ሰገዱልኝ ።

፳ ፤ እንደዚሁም ፡ ፀሐየ ፡
ጽድቅ ፡ የሚባል ፡ የፈጣሪአች
ንና ፡ የአምላካችን ፡ እናት ፡ ሆይ፡
ሰላምታ ፡ ላንቺ ፡ ይገባል ፡ እያሉ
በሰው ፡ ቋንቋ ፡ ተናገሩ ።

፳፩ ፤ እምበሳ ፡ ጥጃ ፡ በእ
ናቱ ፡ ፊት ፡ በደስታ ፡ እንደሚ
ፈነጭ ፡ በፊቴ ፡ ሆነው ፡ ወደላ
ይና ፡ ወደታች ፡ እየዘለሉና ፡

ርዕዕ ፡ ጣዕዋ ፡ በቅድመ ፡ እሙ ።

፳፪ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤሎሙ ፡ ወልድየ ፡ ለእሉ ፡ ሠለስቱ ፡ አናብስት ፡ እለ ፡ ምስሌነ ፡ መጽኡ ፡ እምድረ ፡ ግብጽ ፡ ሑሩ ፡ ተደመሩ ፡ ምስለ ፡ እሉ ፡ አናብስተ ፡ ዛቲ ፡ ገዳም ።

፳፫ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ብዝኁ ፡ ወተባዝኁ ፡ ወምልእዋ ፡ ለምድር ከመ ፡ ሣዕር ፡ ዘዲቤሃ ፡ በቆለ ።

፳፬ ፤ ወውሉድክሙኒ ፡ ይኩን ዎሙ ፡ ምዕራፈ ፡ ከመ ፡ አፍራስ ሊጻማ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ለእለ ፡ ያፈቅርዋ ፡ ለእምየ ፡ እስከ ፡ ኅልፈተ ፡ ዓለም ።

፳፭ ፤ ወይኩኑ ፡ ቡሩካነ ፡ እን በለ ፡ ሙስና ፡ በውስተ ፡ ዛቲ ፡ ገዳም ።

፳፮ ፤ ጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ የሃሉ ፡ ምስለ ፡ ገብሩ ። ______________

ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ወደ ፡ ምድርም ፡ እየጮሁ ፡ ይቦርቁ ፡ ጀመር ።

፳፪ ፤ ዳግመኛም ፡ ልጇ ፡ ከኛ ጋር ፡ ከግብጽ ፡ አገር ፡ የመጡትን ፡ እኒህን ፡ ሦስቱን ፡ አንበሶች ፡ በዚች ፡ ገዳም ፡ ካሉት ፡ አንበሶች ፡ ጋር ፡ ተደባለቁ ፡ አላቸው ።

፳፫ ፤ ምድርን ፡ በላይዋ ፡ ላይ ሣር ፡ አብቅሎ ፡ እንዳለበሳት ፡ እናንተም ፡ ብዙ ፡ ተባዙና ፡ ምድርን ፡ ምኋት ፡ አላቸው ።

፳፬ ፤ ልጆቻችሁም ፡ እናቴን ለሚወዱ ፡ ለቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡ ለሥጋቸው ፡ ድካም ፡ ማረፊያ እስከ ፡ ዓለም ፡ መጨረሻ ፡ እንደ ፈረስና ፡ በቅሎ ፡ ለመጓጓዣ ፡ ያገልግሉአቸው ።

፳፭ ፡ በዚች ፤ ገዳም ፡ ውስጥ ያለጥፋት ፡ የተባረኩ ፡ ሁነው ፡ ይኑሩ ፡ ብሎ ፡ ባረካቸው ።

፳፮ ፤ የቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ጸሎቱና ፡ በረከቱ ፡ ከአገልጋዩ ፡ ______________ጋር ፡ ይሁን ።

ለዘለዓለሙ ፡ አሜን ።



፩ ፤ ሰላም ፡ ለምጽአትክሙ ጥንተ ፡ ዜና ፡ ነገር ፡ አእመነ ፡ በዓለ ፡ ደመና ፡ ዑራኤል ፡ ወድ ንግለ ፡ ሲና ፡ እምነ ። ሰሎሜ ፡ ወዮሴፍ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድርነ።

ተፈሥሒት ፡ ዓውደ ፡ ጽዮን ፡ ወተሰርገወት ፡ ብርሃነ ።

እስመ ፡ ጽዮን ፡ እንዘ ፡ ጽዮን ፡ አብዓለት ፡ ጽዮነ ።

፪ ፤ ዑራኤል ፡ ምስለ ፡ ማርያም ፡ አመ ፡ ረሰይከ ፡ ፍኖተ ።

ልዕልና ፡ ዚአከ ፡ ጥቀ ፡ በወርኃ ፡

ጽዮን ፡ ተከሥተ ። ካህናቲሃ ፡ ለጽ

ዮን ፡ በጊዜ ፡ ለብሱ ፡ ፍርሃተ ።

ነጺሮሙ ፡ ታሕተ ፡ ደመና ፡

አናብስተ ፡ ገዳም ፡ ሠለስተ ።

እንዘ ፡ ትብል ፡ ቁሙ ፡ አይዳ

እከ ፡ ምሕረተ ።

፫ ፤ እምገቦ ፡ የማንየ ፡ ደመ አመ ፡ ይትከዓው ፡ ቀራንዮ ።

በተዲሐ ፡ ዝንቱ ፡ ዑራኤል ፡ ዐዐፈ ፡ ብርሃን ፡ ሎማዮ ። ኅበ እሙንቱ ፡ ያቀድም ፡ ንዝኃተ ፡ ደምየ ፡ ለአስተስርዮ ። በና ግራን ፡ ወልደ ፡ እምላክ ፡ እስመ

፩ ፤ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የተነ ገረውን ፡ ዜና ፡ ለማሳመን ፡ የደ መናው ፡ ባለቤት ፡ ዑራኤል ፡ ዮሴፍና ፡ ሰሎሜ ፡ የሲናዋ ፡ ድን ግል ፡ እናታችን ። ሰላምታ ፡ ይገ ባል ፡ ለአደረጋችሁት ፡ አመጣጥ በኢትዮጵያ ፡ ምድራችን ።

እርስዋ ፡ ጽዮን ፡ ስትሆን ፡ የጽ ዮንን ፡ በዓል ፡ አከበረች ፡ ጽዮን የጽዮንም ፡ ዐደባባይ ፡ ደስ ፡ እያላት ፡ አጌጠች ፡ በብርሃን ።

፪ ፤ ዑራኤል ፡ ከማርያም ፡ ጋር ባደረግህ ፡ ጊዜ ፡ ጉዞ ፡ በጐዳና። በጽዮን ፡ ወራት ፡ ተገለጸ ፤ የል ዕልናህ ፡ ዜና ።

የጽዮን ፡ ካህናት ፡ ሦስት ፡ አንበ ሶችን ፡ አይተው ፡ መትሕተ ፡ ደመና ።

ባደረባቸው ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ፍር ሐት ፡ ልቡና ።

አትፍሩ ፡ ስትል ፡ የምሕረትን ፡ ቃል ፡ አብሥረሃልና ።

፫ ፤ በቀራንዮ ፡ ዐደባባይ ፡ የጌታ ፡ ደሙ ፡ ከቀኝ ፡ ጐኑ ፡ በፈሰሰበት ፡ ዕለት ።

ብርሃንን ፡ የተጐናጸፈ ፡ ዑራ ኤል ፡ ስለኃጢአት ፡ ስርየት ፡ በነዚህ ፡ ቦታዎች ፡ ያስቀድማል፡ ደሙን ፡ ቀድቶ ፡ ለመርጨት ። የአምላክ ፡ ልጅ ፡ የመረጠውን ፡ በናግራን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋ

፳፰ ፤ ወውእቱኒ ፡ ወልደ ፡ መኰንን ፡ ሐይወ ፡ እምደዌሁ ፡ ወንሕነኒ ፡ ነበርነ ፡ ሠለስተ ፡ አውርኃ ፡ ወዐሠርተ ፡ ዕለተ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ደሴት ።

፳፱ ፤ ወአመ ፡ ዐሡሩ ፡ ወስሙኑ ፡ ለወርኃ ፡ ጥር ፡ እምድኅረ ፡ በአትነ ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ባሕር ፡ መጽአ ፡ ዑራኤል ፡ መልአክ ፡ ወአብሠረኒ ፡ ከመ ፡ ሞተ ፡ ሄሮድስ ።

፴ ፤ ወይቤለኒ ፡ ተንሥኢ ፡ እግዝእትየ ፡ ከመ ፡ ንሑር ፡ ሀገረኪ ፡ ናዝሬተ ፡ ወተጽዕኒ ፡ ዲበ ሠረገላ ፡ ብርሃን ፡ መልዕልተ ፡ ደመና ፡ ዘሀሎ ።

፴፩ ፤ ወአሜሃ ፡ መጽአ ፡ ውእቱ ፡ መኰንን ፡ እንዘ ፡ ንትናሣእ ፡ ወንሑውር ፡ እምይእቲ ፡ ባሕር ፡ ወይቤ ፡ አይቴ ፡ ተሐውሩ አጋዕዝትየ ፡ ወለምንት ፡ ትንሣእክሙ ፡ ለሐዊር ፡ እምዛቲ መካን ፡ ወሚመ ፡ እኩየ ፡ ገበርኩ ፡ ላዕሌክሙ ።

፴፪ ፤ ወሶበ ፡ ዘንተ ፡ ይትናገረነ ፡ መጽአ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዑራኤል ፡ ፩ዱ ፡ እምሊቃናት ፡ ወይቤሎ ፡ ወአኮ፡ አንተ ፡ ዘገበርከ ፡ እኩየ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ በእንተዝ ፡ ይትመየጡ፡ ውስተ ፡ ሀገሮሙ ፡ ገሊላ ፡ በይነ ሞቱ ፡ ለሄሮድስ ፡ ዘገብረ ፡ እኩየ ላዕሌሆሙ ።

፳፰ ፤ የዚያ ፡ የመኰንኑ ፡ ልጅም ፡ ከበሽታው ፡ ዳነና ፡ እኛም ከዚያችው ፡ ደሴት ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ከዐሥር ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ ተቀመጥን ።

፳፱ ፤ በጣና ፡ ደሴት ፡ ገብተን ፡ ተቀምጠን ፡ ሳለ ፡ በጥር ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ዑራኤል ፡ መልአክ ፡ መጥቶ ፡ የሄሮድስን ፡ መሞት ፡ አበሠረኝ ።

፴ ፤ ከዚያም ፡ እመቤቴ ተነሺ ፡ ከደመናው ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ የብርሃን ፡ ሠረገላ ፡ ላይ ፡ ወጥተሽ ፡ ተቀመጭና ፡ ወደ ፡ ሀገርሽ ፡ ወደ ፡ ናዝሬት፡ እንሂድ ፡ አለኝ ።

፴፩ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከባሕሩ ደሴት ፡ ወጥተን ፡ ስንሄድ ፡ መኰንኑ ፡ መጥቶ ፡ ጌቶቼ ፡ ከዚች ፡ ቦታ ፡ ለመሄድ ፡ ለምን ፡ ተነሣችሁ ፡ ? ወይም ፡ በኛንተ ፡ ላይ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠራሁባችሁ ፡ ይሆን ? አለን ።

፴፪ ፤ ይህን ፡ ነገር ፡ ሲናገረኝ ፡ ከመላእክት ፡ አለቆች ፡ አንዱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ዑራኤል ፡ መጥቶ ፡ አንተ በነሱ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠርተህባቸው ፡ አይደለም ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ የሠራባቸው ፡ ሄሮድስ፡ ስለሞተ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ስለሚ መለሱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አለው ።



፴፫ ፤ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ዘንተ ነገረ ፡ እምአፈ ፡ ዑራኤል ፡ መልአክ ፡ በከየ ፡ ወአስቆቀወ ፡ ጥቀ ፡ ውእቱ ፡ መኰንን ።

፴፬ ፤ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ ሰብአ ይእቲ ፡ ሀገር ፡ ወደሴተ ፡ ባሕር ፡ ቃለ ፡ ብካዩ ፡ ለውእቱ ፡ መኰንን ወይቤልዎ ፡ ምንት ፡ ያበክየከ ፡ ወምንተ ፡ ኮንከ ፡ አ ፡ እግዚእነ ።

፴፭ ፤ ወአውሥአ ፡ መኰንን ፡ ወይቤሎሙ ፡ ምንተ ፡ ይበቍዓ ክሙ ፡ ለእመ ፡ ነገርኩክሙ ፡ ኀዘንየ ፡ ኵሎ ፡ ዘረከበኒ ፡ ዮም ባሕቱ ፡ ይኄይሰኒ ፡ መዊት ፡ እምተፈልጠቶሙ ፡ ለእሉ ፡ ሰብእ በኃጢአትየ ፡ ኃደጉኒ ፡ እንዘ ፡ የሐውሩ ፡ ሀገሮሙ ።

፴፮ ፤ ወእንዘ ፡ ዘንተ ፡ ይትናገር ፡ ውእቱ ፡ መኰንን ፡ አሜሃ ተጸበ ፡ ደመና ፡ ወልድየ ፡ እንዘ ሀሎ ፡ በዘባነ ፡ ሰሎሜ ።

፴፯ ፤ ወይቤለኒ ፡ ዑራኤል ፡ መልአክ ፡ ንዒ ፡ ተጽዕኒ ፡ እግዝእትየ ፡ መልዕልተ ፡ ደመና ፡ ወአዕረገኒ ፡ ዲበ ፡ ሠረገላ ፡ ዘብርሃን ።

፴፰ ፤ ወቆምነ ፡ ውስተ ፡ አየር ዘሰማይ ፡ እንዘ ፡ ይኔጽሩነ ፡ ሰብአ ይእቲ ፡ ሀገር ።

፴፱ ፤ ወሶቤሃ ፡ ጸርሑ ፡ በዓቢይ ፡ ቃል ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ አእግዚእ ፡ መሐረነ ፡ እምላክነ ፡

፴፫ ፤ መኰንኑም ፡ ከመልአኩ ፡ ከቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ አን ደበት ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ፡ ጮኾ ፡ አለቀሰ ።

፴፬ ፤ በዚያች ፡ ሀገር ፡ የባሕር ፡ ደሴት ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎችም የመኰንኑን ፡ ልቅሶውንና ፡ ጩኸቱን ፡ ሰምተው ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ ምን ፡ ሁነሃል ? ምንስ ፡ ያስለቅስሃል ፡? አሉት ።

፴፭ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ መኰንኑ ዛሬ ፡ ያገኘኝን ፡ ኀዘን ፡ ሁሉ ፡ ብነግራችሁ ፡ ምን ፡ ይጠቅማችኋል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ በኃጢአቴ ፡ ምክንያት፡ ተለይተውኝ ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ ከሚሄዱ ፡ ብሞት ፡ ይሻለኝ ፡ ነበር ፡ አላቸው ።

፴፮ ፤ መኰንኑ ፡ ይህን ፡ ነገር ሲናገር ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ልጄ ፡ በሰሎሜ ፡ ጀርባ ፡ ታዝሎ ፡ ሳለ ፡ ደመና ፡ ጠቀሰ ።

፴፯ ፤ መልአኩ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤልም ፡ እመቤቴ ፡ ከደመናው ፡ ላይ ፡ ተቀመጪ ፡ አለኝና ፡ ከብርሃኑ ፡ ሠረገላ ፡ ላይ ፡ አወጣኝ።

፴፰ ፤ የዚያች ፡ አገር ፡ ሰዎችም ፡ እያዩን ፡ ከሰማዩ ፡ አየር ላይ ፡ ወጥተን ፡ ቆምን ።

፴፱ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ አቤቱ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ በእንግድነት ፡ የነበሩትን ፡ የነዚ

ናት ፡ ጽዮን ፡ ዘወፅአ ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ በመዋዕለ ፡ ወልዱ ፡ ለሰሎሞን ፡ ንጉሠ ፡ ይሁዳ ።

፵፬ ፤ **ወሶቤሃ ፡ ተንሥአ** ፡ እመንበሩ ፡ ወተወከፈኒ ፡ በፍሥሐ ፡ ወአንበረኒ ፡ ምስሌሁ ፡ ኀበ ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ሠናይ ፡ እስመ ፡ መፍቀሬ ፡ ሰብእ ፡ ውእቱ ፡ በእንተ ፡ **እግዚአብሔር** ።

፵፭ ፤ **ወጸውዖ ፡ ለፍሬምናጦስ ፡** እምነ ፡ ቤቱ ፡ እስመ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ የአምር ፡ ነገረ ፡ ልሳን ፡ ዘብሔረ ፡ ሀገሩ ፡ ለእንበረም ፡ ወተሐፅነ ፡ በውስተ ፡ ቤቱ ፡ እምጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ለአቡሁ ፡ ወኃደጎ ፡ በኀቤሁ ።

፵፮ ፤ **ወይቤሎ ፡ ለእንበረም ፡** አቡሁ ፡ ለፍሬምናጦስ ፡ እምቅድመ ፡ ሞቱ ፡ አመሐፅን ፡ ኀቤከ ፡ አ ፡ እንበረም ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በእንተ ፡ ወልድየ ፡ አንሰ ፡ እምሰብአ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ዘመጻእኩ ፡ በተአንግዶ ፡ ውስተ ፡ ሀገርከ ፡ ዘመድ ፡ ወነገድ ፡ አልብየ ፡ ዘእንበሌከ ፡ እምታሕተ ፡ አምላክነ ፡ ዮም ።

፵፯ ፤ **ወበጽሐ ፡ ጊዜ ፡ ሞትየ ፡** ወአማኅፀንኩከ ፡ በእንተ ፡ **እግዚአብሔር ፡ አምላክ** ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡ ትኩኖ ፡ ለወልድየ ፡ አበ ።

ካህናት ፡ የተማረውን ፡ የእስራኤል ፡ የአሪታቸውን ፡ ትምህርት ፡ ሲያስተምር ፡ አገኘነው ።

፵፬ ፤ **ያን ፡ ጊዜ** ከመቀመጫው ፡ ተነሥቶ ፡ በደስታ ፡ ተቀበለንና ፡ እሱ ፡ ካለበት ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ በመልካም ፡ ቦታ ፡ አስቀመጠን ፡ **ለእግዚአብሔር** ፡ ብሎ ፡ ሰውን ፡ ይወዳልና ።

፵፭ ፤ **አባቱ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡** በእንበረም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያደገና ፡ አባቱም ፡ እሱ ፡ ቤት ፡ ስለተወው ፡ ፍሬምናጦስ ፡ የእንበረምን ፡ ሀገር ፡ ቋንቋ ፡ በማወቁ ፡ ፍሬምናጦስን ፡ ከቤቱ ፡ አስጠራው ።

፵፮ **የፍሬምናጦስ ፡** አባት ፡ ከመሞቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ እንበረም ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ሰዎች ፡ ስሆን ፡ ወደሀገርህ ፡ በእንግድነት ፡ የመጣሁ ፡ ነኝ ፡ ከፈጣሪአችን ፡ በታች ፡ ያለአንተ ፡ ዘመድ ፡ ወገን ፡ የሌለኝ ፡ ነኝና ፡ የልጄን ፡ ነገር ፡ አደራ ፡ እልሃለሁ ፡ አለው ።

፵፯ ፤ **የኔ ፡ ጊዜ ፡** ሞቴ ፡ ደርሷልና ፡ ልጄን ፡ **ስለእግዚአብሔር ፡** ብለህ ፡ አባት ፡ ትሆነው ፡ ዘንድ ፡ ዓለምን ፡ ሁሉ ፡ በፈጠረ ፡ አምላክ ፡ አማፅንሃለሁ ።



፵፰ ፤ **ወትረስዮ ፡** ከመ ፡ አሐዱ ፡ ሕፃን ፡ ዘእምወልደ ፡ ቤትከ ፡ ወሐፅኖ ፡ በሠናይ ፡ ወመሀሮ ፡ ሕገ ፡ አበዊከ ፡ ሌዋውያን ፡ ቡሩካኑ ፡ **ለአምላክነ** ።

፵፱ ፤ **ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡** ሞተ ፡ አቡሁ ፡ ለፍሬምናጦስ ፡ ውእቱኒ ፡ እንበረም ፡ ሐፀኖ ፡ በሠናይ ፡ ሕፅነት ፡ ወመሀሮ ፡ ነገረ ፡ ልሳን ፡ ብሔሩ ፡ ኵሎ ፡ ለመጽሐፈ ፡ ግእዝ ።

፶ ፤ **ወውእቱ ፡ ፍሬምናጦስ፡** እስመ ፡ የአምር ፡ ነገረ ፡ ልሳን ፡ ዘሀገረ ፡ ብሔሮሙ ፡ ለ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ።

፶፩ ፤ **ወሊተኒ ፡** የአምረኒ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በሀገረ ፡ አቡሁ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ምስለ ፡ ዘሥጋ ፡ አኃዊሁ ።

፶፪ ፤ **ወበእንተዝ ፡ ጸውዖ ፡** እንበረም ፡ ለፍሬምናጦስ ፡ ከመ ፡ ያስተሳንዓነ ፡ በበልሳነ ፡ ብሔርነ ።

፶፫ ፤ **ወጠየቀኒ ፡ አሚሃ፡** ነገረ ፡ ምጽአትየ ፡ ኀቤሁ ፡ በአፈ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ እንበረም ፡ ወዘፈቀድነ ፡ ነገረ ፡ ይግበር ፡ ለነ ።

፶፬ ፤ **ወአውሥእዎ ፡** ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ወነገርዎ ፡ ዘከመ ፡

፵፰ ፤ **ከቤተሰብህ ፡** እንደ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ አድርገህ ፡ በመልካም ፡ አስተዳደግ ፡ አሳድገው ፡ ቡሩካን ፡ የሆኑ ፡ የአምላካችን ፡ ካህናት ፡ አባቶችንም ፡ ወይም ፡ የሌዋውያንን ፡ ሕግ ፡ አስተምረው ።

፵፱ ፤ **ይህን ፡ ተናግሮ ፡** የፍሬምናጦስ ፡ አባት ፡ ሞተ ፡ እንበረምም ፡ በመልካም ፡ አስተዳደግ ፡ እያሳደገ ፡ የሀገሩን ፡ ቋንቋና ፡ ፡ የግእዝን ፡ መጽሐፍ ፡ አስተማረው ፡

፶ ፤ **ፍሬምናጦስ ፡** የዘጠኙን ፡ ቅዱሳን ፡ የሀገራቸውን ፡ ቋንቋ ያውቅ ፡ ነበርና ።

፶፩ ፤ **እኔንም ፡ በአባቱ ፡ አገር ፡** ከሥጋ ፡ ወንድሞቹ ፡ ጋር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሳለ ፡ ያውቀኛል ።

፶፪ ፤ **ስለዚህ ፡ በየሀገራችን ፡** ቋንቋ ፡ እየተረጐመ ፡ ያነጋግረን ፡ ዘንድ ፡ ፍሬምናጦስን ፡ ጠራው ።

፶፫ ፤ **ያንጊዜ ፡** ሊቀ ፡ ካህናት ፡ እንበረም ፡ ወደሱ ፡ የመጣሁበትን ፡ ነገር ፡ በፍሬምናጦስ ፡ አስተርጓሚነት ፡ የፈቀድሁትን ፡ ነገር ፡ እንዲያደርግልኝ ፡ ጠየቀኝ ።

፶፬ ፤ **ዘጠኙ ፡ ቅዱሳንም ፡** አስቀድመው ፡ እንደነገሩት ፡ ከሀ

እንጦንስ ፡ ምስሌየ ፡ ወአርእየ ክሙ ፡ ፍኖቶ ።

፱ ፤ ወሐዊሮ ፡ እምኀቤነ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ፱ቱ ፡ ቅዱሳን፡ ወ፪ቱ ፡ ነገሥት ፡ ወኀበ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ወእንበረም ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ወነገሮሙ ፡ ዜና ፡ ሑረትነ ፡ ኀበ ፡ ብሔርነ ።

፲ ፤ ወእምዝ ፡ መጽአ ፡ ጊዜ ፡ ንቅወተ ፡ ዶርሆ ፡ ኀቤነ ፡ ተከዘ ፡ ወኃዘኑ ፡ በእንተ ፡ ተፈልጦትነ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወበከዩ ፡ ጥቀ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ አኃዊነ ፡ በእንተ ፡ እግዝእተ ፡ ኵልነ ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ንስእለክሙ ፡ ከመ ፡ ኢትሑሩ ፡ እምሀገርነ ፡ ኢትትፈለጡ ፡ እምኔነ ፡ እስመ ፡ ሐዲስ ፡ ተክል ፡ ንሕነ ፡ ወትሜህሩነ ፡ ቃለ ፡ ወንጌሉ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

፲፩ ፤ ወአውሥአ ፡ አባ ፡ ኤፍሬም ፡ ወይቤሎሙ ፡ አኮ ፡ ንሕነ ፡ በፈቃድነ ፡ ዘንሐውር ፡ አላ ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ አኃዊነ ፡ ኢታተክዙነ ፡ በኀዘነ ፍቅርክሙ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል፡ ነገረነ ፡ ከመ ፡ ንሑር ፡ ውስተ ፡ ብሔርነ ።

፲፪ ፤ ወባሕቱ ፡ ኢንትፈለጥ ፡ እምዛቲ ፡ ደብረ ፡ ጽዮን ፡ በበ ዓመት ፡ እመ ፡ ሀለውነ ፡ በሕይ ወት ፡ ወእመኒ ፡ ሞትነ፡ ንመጽእ ፡

መንገዱንም ፡ አመራችሁ ለሁ ፡ አለን ።

፱ ፤ ከኛም ፡ ዘንድ ፡ ሄደና ፡ ለዘጠኙ ፡ ቅዱሳንና ፡ ለሁለቱ ፡ ነገሥታት ፡ ለአባ ፡ ሰላማና ፡ ለሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ለእንበረም ፡ ወደሀገራችን ፡ የመሄዳችንን ፡ ዜና ፡ ነገራቸው ።

፲ ፤ ዶሮ ፡ ሲጮህም ፡ ወደኛ ፡ መጥተው ፡ ከነሱ ፡ በመለየታ ችን ፡ በጣም ፡ አዘኑ ፤ ወንድሞ ቻችን ፡ ስለመቤታችን ፡ ስለ ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ እንለምና ችኋለን ፡ እኛ ፡ ገና ፡ አዲስ ፡ ተክል ፡ ነንና ፡ የጌታችን ፡ የኢ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቃለ፡ ወንጌሉን፡ ታስተምሩናላችሁ ፡ ከሀገራችን ፡ አትሂዱብን ፡ እያሉ ፡ አለቀሱ ።

፲፩ ፤ እኛ ፡ የምንሄደው ፡ በራ ሳችን ፡ ፈቃድ ፡ አይደለም ፡ በእግዚ አብሔር ፡ ፈቃድ ፤ ነው ፡ እንጂ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ሆይ ፡ በፍቅራችሁ ፡ ትዝታ ፡ ልታገ ብሩን ፡ አትሞክሩ ፡ እንሄድ ፡ ዘንድ ፡ እነሆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ አዞናልና ፡ ሲል ፡ አባ ፡ ኤፍሬም ፡ ነገራቸው ።

፲፪ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ካለን ፡ በየዓመቱ ፡ ከዚች ፡ ከደብረ ፡ ጽዮን ፡ አንለይም ፤ ብን ሞትም ፡ ሳንማር ፡ በመንፈስ ፡



በአካለ ፡ ነፍስ ፡ ፪ተ ፡ ጊዜ ፡ ለሰሚዓ ፡ ቃለ ፡ ቅዳሴሃ ፡ ወው ዳሴሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም፡ ዘደረስነ ፡ በእንቲአሃ ፡ በጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘእንበለ ፡ ትምህርት ።

፲፫ ፤ ወዝንቱኒ ፡ ዘኮነ ፡ አመ ፡ አስተየነ ፡ ጽዋዓ ፡ ልቡና ፡ ዝንቱ ፡ ዑራኤል ፡ መልአክ ፡ እምዕዝራ ፡ ነቢይ ፡ ዘተርፈ ።

፲፬ ፤ ወሶቤሃ ፡ ተመስጠ ፡ ኀሊናነ ፡ በአእምሮ ፡ ምሥጢ ራት ፡ ወሰከረ ፡ መንፈስነ ፡ በስቴ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፲፭ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ አባ ፡ ኤፍሬም ፡ ሶርያዊ ፡ ወሀቦ ፡ መጽ ሐፈ ፡ ውዳሴሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ለአባ ፡ እንበረም ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ።

፲፮ ፤ ወእነኒ ፡ ሕርያቆስ ፡ ወሀ ብክዎ ፡ መጽሐፈ ፡ ቅዳሴሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ለአባ ፡ ሰላማ ፡ ምስለ ፡ ቅዳሴሆሙ ፡ ለሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ባስልዮስ ፡ ወእ ኁሁ ፡ አባ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ወቅ ዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ ወኤጲፋንዮስ፡ ወ፫፻፲፰፡ ወ፫ቱ ፡ ርቱ ዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ እስመ ፡ እሙ ንቱ ፡ ፍቁራኒሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ።

፲፯ ፤ ወዘንተኒ ፡ መጽሐፈ ፡ ድርሳኑ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡

ቅዱስ ፡ ተገልጾልን ፡ ስለ ፡ እመ ቤታችን ፡ ስለ ፡ ድንግል ፡ ማር ያም፡ የደረስነውን ፡ ውዳሴዋ ንና ፡ ቅዳሴዋን ፡ ለመስማት ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ በዓመት ፡ሁለት ፡ ጊዜ ፡ እንመጣለን ፡ አሏቸው ።

፲፫ ፤ ይኸውም ፡ የሆነው ፡ መል አኩ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ለነ ቢዩ ፡ ዕዝራ ፡ ጽዋዓ ፡ ልቡና ፡ አጠጥቶት ፡ የተረፈውን ፡ ለኛ ፡ በአጠጣን ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

፲፬ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ መንፈሳችን፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መጠጥ ፡ ሰከረና ፡ ምሥጢራትን ፡ ለማ ወቅ ፡ አእምሮአችን ፡ ተከፈተ ።

፲፭ ፤ ይህንንም ፡ ተናግሮ ፡አባ ፡ ኤፍሬም፡ የመቤታችንን ፡ የው ዳሴዋን ፡ መጽሐፍ ፡ ለሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ለአባ ፡ እንበረም ፡ ሰጠው ።

፲፮ ፤ እኔም ፡ አባ ፡ ሕርያቆስ ፡ የእመቤታችንን ፡ የቅዳሴዋን ፡ መጽሐፍ ፡ ከሊቃነ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ከአባ ፡ ባስልዮስና ፡ ከወንድሙ ፡ ከአባ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ከዮሐንስ ፡ አፈወርቅና ፡ ከኤጲፋንዮስ ፤ ሃይ ማኖታቸው ፡ ከቀና ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንቱ ፡ ሊቃ ውንት ፡ ቅዳሴ ፡ ጋር ፡ ለአባ ፡ ሰላማ ፡ ሰጠሁት ። እነዚህ ፡ ሁሉ የእመቤታችን ፡ የድንግል ፡ ማር ያም፡ ባለሟሎች ፡ ናቸውና ።

፲፯ ፤ ይህንንም ፡ የመልአኩ፡ የቅዱስ ፡ ዑራኤልን ፡ የድርሳን ፡

ንቱ ፡ ምስለ ፡ ፬ቱ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ።

፳፱ ፤ **ወእሉ ፡ እሙንቱ ፡** ዘነበሩ ፡ ምስሌነ ፡ አባ ፡ አትናቴዎስ ፡ ዘእስክንድርያ ፡ ወአባ ፡ ክርስትዶሉ ፡ ዘሮሜ ፡ ወአባ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘሶርያ ፡ ወዘቍስጥንጥንያ ፡ ወአባ ፡ ሳዊሮስ ፡ ዘሀገረ ፡ አንጾኪያ ፡ ወኤጲስቆጶስ ፡ ዘኢየሩሳሌም ፡ አባ ፡ ቄርሎስ ፡ ወአበ ፡ ምኔት ፡ ዘገዳመ ፡ እንጦንስ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ።

፴ ፤ **ወኮኑ ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡** ኵሎሙ ፡ ሰማዕተ ፡ ለዝንቱ ፡ ገቢረ ፡ ተአምራት ፡ ወለዜና ፡ ክብሩ ፡ **ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡** ዘከመ ፡ ገብረ ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ።

፴፩ ፤ **ወእንበይነ ፡ ዝንቱ ፡** ናሁ ፡ ጸሐፍነ ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ነገረ ፡ ውዳሴሁ ፡ **ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡** ዘርኢናሁ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ **ኢትዮጵያ ፡** ወወሰክነ ፡ እምዘጸሐፎ ፡ አብርኮርስ ፡ ረድአ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ፍቁረ ፡ **እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።**

፴፪ ፤ **ወፈጸምነ ፡ ዘንተ፡** በረድኤተ ፡ **እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡** ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ምስለ፡ አቡሁ ፡ ወምስለ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ፡ እምይእዜ ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ።

ራቱ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ጋር ፡ በአንድነት ፡ አደነቅን ።

፳፱ ፤ **እነሱም ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡** የነበሩት ፡ የእስክንድርያው ፡ አባ ፡ አትናቴዎስና ፡ የሮማው ፡ አባ ፡ ክርስትዶሉ ፡ የሶርያውና ፡ የቍስጥንጥንያው ፡ አባ ፡ ዮሐንስና ፡ የአንጾኪያው ፡ አባ ፡ ሳዊሮስ ፡ የኢየሩሳሌሙ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አባ ፡ ቄርሎስና ፡ የአባ ፡ እንጦንስ ፡ ገዳም ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ናቸው ።

፴ ፤ **በዚህ ፡ ሁሉ ፡** ተአምራትና ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ የሆነ ፡ ለመልአኩ ፡ **ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡** ለክብሩ ፡ ዜና ፡ ይህንም ፡ ሁሉ ፡ እንዳደረገ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምስክሮች ፡ ናቸው ።

፴፩ ፤ **ስለዚህ ፡ ነገር ፡** እነሆ ፡ **በኢትዮጵያ ፡** ውስጥ ፡ ያየነውን ፡ **የቅዱስ ፡ ዑራኤልን ፡** ታሪክ ፡ ሁሉ ፡ **የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡** ወዳጅ ፡ የሚሆን ፡ የዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ አብሮኮሮስ ፡ በጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ አድርገን ፡ ጽፈናል ።

፴፪ ፤ **ዛሬም ፡ ዘወትርም ፡** እስከ ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ ከአባቱ ፡ ከአብና ፡ **ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡** ጋር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ **በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡** ረዳትነት ፡ ይህንን ፡ ፈጽመናል ።



፴፫ ፤ **ወተጽሕፈ ፡ ዝንቱ ፡** መጽሐፈ ፡ ድርሳኑ ፡ **ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡** ኢ፻ቱ ፻፵ ወ፬፡ዓመት ፡ እምልደተ ፡ **እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡** ወእምፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ በ፶፻ ወ፰፻፺ ወ፪፡ዓመት ፡ በመዋዕለ ፡ መንግሥቶሙ ፡ ለአብርሃ ፡ ወአጽብሐ ፡ ነገሥተ ፡ **ኢትዮጵያ ፡** ወበሢመተ ፡ ጵጵስናሁ ፡ ለአባ ፡ ሰላማ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ወሊቀ ፡ ካህናት ፡ እንበረም ፡ ዘተሰምየ ፡ ሕዝበ ፡ ቀድስ ፡ በጥቅምተ ፡ ክርስትና ፡ በእደ ፡ ውእቱ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ጳጳስ ፡ **ዘኢትዮጵያ ።**

፴፬ ፤ **ወተመይጠ ፡ ዝንቱ ፡** መጽሐፈ ፡ ድርሳን ፡ **ዘቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡** በልሳነ ፡ ዮናኒ ፡ በግእዝ ፡ በእደ ፡ እንበረም ፡ ተቀጺሎ ፡ እምአፉሁ ፡ ለአባ ፡ ጌዴዎን ፡ ዘሀገረ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ረድአ ፡ አባ ፡ ሕርያቆስ ፡ ዘሀገረ ፡ ብህንሳ ፡ ወመምህሩ ፡ ለአባ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ ወልደ ፡ ገበዘ ፡ አክሱም ፡ በዓለ ፡ ዜማ ፡ ጥዑመ፡ ልሳን ።

፴፭ ፤ **ጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡** የሃሉ ፡ ምስለ ፡ ገብሩ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፴፫ ፤ **ይህ፡የመላእክት ፡ አለቃ ፡ የቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡** ድርሳን ፡ የተጻፈው ፡ **ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከእመቤታችን ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡** በሥጋ ፡ በተወለደ ፡ በሁለት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ዓለም ፡ በተፈጠረ ፡ በአምስት ፡ ሺህ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ዘጠና ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ **የኢትዮጵያ ፡** ነገሥታት ፡ በአብርሃና ፡ አጽብሐ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ጵጵስና ፡ በተሾመበት ፡ ዘመንና ፡ እንዲሁም ፡ በአባ ፡ ሰላማ ፡ እጅ ፡ በክርስትና ፡ ጥምቀት ሕዝበ ፡ ቀድስ ፡ ተብሎ፡ በተሠየመ ፡ በሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ በእንበረም ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

፴፬ ፤ **ይህ ፡ የቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡** የድርሳን ፡ መጽሐፍ ፡ በዮናኒ ፡ ቋንቋ ፡ ጥዑመ ፡ ልሳን ፡ ተብሎ ፡ ለተጠራ ፡ ለዜማው ፡ ባለቤት ፡ ለያሬድ ፡ አስተማሪ ፡ ከሆነው ፡ ከቍስጥንጥንያው ፡ አገር ፡ ከብህንሳው ፡ ከአባ ፡ ሕርያቆስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ከአባ ፡ ጌዴዎን ፡ እየተተረጐመ ፡ በአባ ፡ እንበረም ፡ እጅ ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ተጻፈ ።

፴፭ ፤ **የመላእክት ፡ አለቃ ፡ የቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡** ጸሎቱና ፡ በረከቱ ፡ ለዘላለሙ ፡ ይሁን ፡ አሜን ።

፩ ፤ ኦ ፡ ዘረዳእኮሙ ፡ ማዕበ ላተ ፡ ባሕር ፡ አመ ፡ ተንሥኡ ። በፍሬምናጦስ ፡ ወሬዛ ፡ ወበ ጳንጠሌዎን ፡ ካልኡ ። እምነ ፡ ሰማይ ፡ ዑራኤል ፡ እስመ ፡ ኃይ ላቲከ ፡ መጽኡ ፡ ኮኑ ፡ ከመ ፡ ኖትያ ፡ ወማዕበለ ፡ ሐመር ፡ አኀድኡ ። እለ ፡ ቀብጹ ፡ ተስፉ ፡ ሕይወት ፡ ውስተ ፡ የብስ ፡ ወፅኡ ።

፪ ፤ ኦ ፡ ዘከሠትከ ፡ ምሥጢረ ፡ ክህነት ፡ ሐዲሰ ። ለሊቀ ፡ ካህ ናት ፡ እንበረም ፡ ከዊነ ፡ ሰላማ ፡ ጳጳሰ ፤ ዑራኤል ፡ መልአክ ፡ በዓለ ፡ ከዊን ፡ ሞገሰ ፡ ወዜነ ውከ ፡ ካዕበ ፡ ለሊቃናት ፡ በዘ ቄርሎስ ፡ ተውዳሰ ። ወለአት ናቴዎስ ፡ ከሠትከ ፡ ካዕበተ ፡ መንፈሰ ።

፫ ፤ ሕርያቆስ ፡ ወኤፍሬም ፡ አመ ፡ ተራከቡ ፡ በጽርሐ ፡ጽዮን ፡ ዓውደ ፡ ሥላሴ ፡ ለሠሪዓ ፡ ቍር ባን ፡ ተኃርዩ ፡ በጊዜ ፡ ገቢር ፡ ቅዳሴ ፡ እስመ ፡ መሥዋዕቶሙ ፡ ዓብየ ፡ እመሥዋዕተ ፡ አሪት ፡ ዘሙሴ ።

፩ ፤ በወጣቱ ፡ በፍሬ ፡ ምና ጦስና ፡ በጳጠሌዎንም ፡ ላይ ፡ በኋደኛው ፡ የባሕር ፡ ማዕበል ፡ በተነሣባቸው ፡ ጊዜ ፡ የደረስክላ ቸው ፡ ዑራኤል ፡ ሆይ ፡ ኃይሎ ችህ ፡ ከሰማይ ፡ መጥተው ፡ የባሕሩን ፡ ማዕበል ፡ ጸጥ ፡ አደ ረጉት ፤ እንደዋነተኛ ፡ ሆነው ፡ ተስፋ ፡ የቆረጡትም ፡ የብስ ፡ ረገጡ ፡ ከባሕር ፡ ወጥተው ።

፪ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ባለሟልነትን ፡ አግኝተህ ። ስለ አዲስ ፡ ምሥጢረ ፡ ክህነት ፡ ከላይ ፡ ከሰማይ ፡ መጥተህ ፡ ስለ ሰላማ ፡ ጳጳስ ፡ መሆን ፡ ለሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ለእንበረም ፡ ገለጽህ ። ዳግመኛም ፡ ሰላማ ፡ ተብሎ ፡ እንዲሰየም ፡ በአባ ፡ ቄርሎስ ፡ አንደበት ፡ ተናገርህ ፡ ለአትናቴ ዎስም ፡ እጥፍ ፡ የመንፈስ ፡ ጸጋ ፡ እንዳደረበት ፡ አስረዳህ ።

፫ ፤ ሕርያቆስና ፡ ኤፍሬም የሥላሴ ፡ ማደሪያ ፡ በምትሆን ፡ በጽዮን ፡ አዳራሽ ፡ ተገናኝተው ። መሥዋዕት ፡ እንዲሠዉ ፡ ተመ ረጡ ፡ ለቅዳሴው ፡ መሪ ፡ ሆነው ። እነሱ ፡ የሚያቀርቡት ፡ መሥዋ ዕት ፡ ይበልጣልና ፡ ከቀድሞው ፡ መሥዋዕት ፡ በሙሴ ፡ ሕግ ፡ ከሚቀርበው ፡ ስለዚህ ፡ የምስ



ሶቤሃ ፡ ወረደ ፡ ምስለ ፡ እሙ ፡ አምላከ ፡ ከዊን ፡ ውዳሴ ፡ ለ፦ወክፎ ፡ እሎ ፡ መሥዋ ዕት ፡ ዘአልቦ ፡ ድምሳሴ ። ስብ ሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወለወ ላዲቱ ፡ ድንግል ። ወላዕሌነ ፡ ይኩን ፡ ምሕረት ፡ ወሣህል ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም፡ አሜን ።

ጋና ፡ ባለቤት ፡ አምላክ ፡ ከናቱ ፡ ጋር ፡ ከሰማይ ፡ ወርደው ። ነውር ፡ ነቀፋ ፡ የሌለበት ፡ የቍርባናቸውን፡ ጸሎት ፡ ተቀበላቸው ፡ ለእግዚአ ብሔርና ፡ ለናቱ ፡ ለድንግል ፡ ማርያምም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ። ለኛም ፡ ለዘላለሙ ፡ ምሕረት ፡ ይቅርታ ፡ ይደረግልን ፡ አሜን ።

ድርሳነ ፡ ዑራኤል ፡ ዘየካቲት ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ አሜን ።

ድርሳን ፡ ዘቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡

ዘይትነበብ ፡

አመ ፡ ፳ወ፪ ፡ ለወርኃ ፡ የካቲት ።

ጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ የሃሉ ፡ ምስለ ፡ ገብሩ

ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ በእውነት ፡ አምነን ፡ በየካቲት ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ የሚነበብ ፡ የሚ ጸለይ ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ የሚሆን ፡ የቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ድርሳን ፡ ይህ ፡ ነው ።

ጸሎቱ ፡ ልመናውና ፡ በረከቱ ፡ ከወዳጁ ፡ ጋራ ፡ ይሁን ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## ም ዕ ራ ፍ ፩ ።

፩ ፤ እምቅድመ ፡ ዜናሁ ፡ ወተአምሪሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ንዝክር ፡ ልዕልናሁ ፡ ወዕበዮ ፡ ወግብሮ ፡ ለአአምላክነ ፡ ዘሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

፪ ፤ በቀዳሚት ፡ ዕለት ፡ ፈጠረ እግዚአብሔር ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ፡ ነፋሰ ፡ ወእሳተ ፡ ማየ ፡ ወጽልመተ ፡

፫ ፤ ወእምድኅሬሁ ፡ ፈጠሮሙ ለመላእክት ፡ በአርአያሁ ፡ ወበአምሳሊሁ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዋሕድ ።

፬ ፤ እስመ ፡ ዋሕድና ፡ አምላክ ፡ ኮነ ፡ ዋሕድና ፡ ባሕር ፡ ይናሆሙ ፡ ወአልቦ ፡ ዘየአምር ፡ ጥንተ ፡ ተፈጥሮቶሙ ።

፭ ፤ ወእምጽአሙ ፡ እግዚአብሔር፡ እምኅበ ፡ አልቦ ፡ ኅበ ፡ቦ ።

፮ ፤ እመ ፡ ኮነ ፡ ተፈጥሮቶሙ ፡ እምነፋስ ፡ አው ፡ እምእሳት ፡ ለሊሁ ፡ የአምር ፡ በኀሊናሁ ፡ ዘሠዘራ ፡ ለሰማይ ፡ በሥዝሩ ።

## አንደኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ ከሚሆን ፡ ከቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ዜና ተአምር ፡ አስቀድመን ፡ ለዘላለሙ ፡ ምስጋና ፡ ገንዘቡ ፡ የሚሆን ፡ የፈጣሪአችንን ፡ ገናናነቱንና ፡ ጌትነቱን ፡ ድንቅ ፡ የሚሆን ፡ ሥራውንም ፡ ሁሉ ፡ መናገር ፡ ይገባናል ።

፪ ፤ በመጀመሪያው ፡ ቀን እግዚአብሔር ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ነፋስንና ፡ እሳትን ፡ ውኃንና ፡ ጨለማን ፡ ፈጠረ ።

፫ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ የሚሆን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ በአርአያውና ፡ በምሳሌው ፡ መላእክትን ፡ ፈጠረ ።

፬ ፤ የመላእክት ፡ የባሕርያቸው አንድነት ፡ ከአምላክ ፡ አንድነት ፡ ተዋሕደዋልና ፡ ማለት ፡ ባለመሞት ፡ የተፈጥሮአቸውን ፡ ጥንተ ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ስንኳ፡ የሚያውቅ ፡ የለምና ።

፭ ፤ ስለሆነም ፡ እግዚአብሔር ካለመኖር ፡ ወደመኖር ፡ አምጥቶ ፈጥሮአቸዋልና ።

፮ ፤ ሰማይን ፡ በክንዱ ፡ የሠፈራት ፡ እግዚአብሔር ፡ የመላእክት ፡ ተፈጥሮአቸው ፡ ከነፋስ ወይም ፡ ከእሳት ፡ እንደሆነ ፡ በባሕርዩ ፡ የሚያውቅ ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ብቻ ፡ ነውና ።



፯ ፤ ተፈጥሮተ ፡ መላእክት ፡ ዕጹብ ፡ ውእቱ ፡ ለኃልዮ ፡ ኣኮ ፡ ለሰብእ ፡ ባሕቲቱ ፡ አላ ፡ ለመላእክትኒ ፡ ዕጹብኬ ፡ ዕጹበ ፡ ኮኖሙ ።

፰ ፤ ወተኃብአሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኅቡአቲሁ ፡ ዝኒ ፡ ዕጹብ ውእቱ ፡ ለተናግሮ ።

፱ ፤ ሰበ ፡ ኃጥአ ፡ ምሳሌሆሙ ሰብእ ፡ እስመ ፡ ሕቀ ፡ ውእቱ ፡ ለሊሁ ፡ በኀሊናሁ ፡ አስተማስለ ጥንተ ፡ ተፈጥሮቶሙ ፡ እምነፋስ፡ ረቂቅ ፡ ወእምነ ፡ እሳት ፡ በላዒ ።

፲ ፤ እመቦ ፡ ዘይብል ፡አአምር ተፈጥሮቶሙ ፡ ለመላእክት ፡ነፍሰ ዕዕብት ፡ ሕስው ፡ ውእቱ ፡ ወባሕርየ ፡ መላእክትሰ ፡ እምጥንተ ፡ ጥበቢሁ ፡ ህልው ፡ ውእቱ ።

፲፩ ፤ እምቅድመ ፡ ይፍጥር ፡ መላእክተ ፡ ለቅዳሴ ፡ ኢተጸርዓ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ዘሀሎ ፡ ወይሄሉ ።

፲፪ ፤ ከማሁ ፡ ነፍስ ፡ ዕቅብት፡ እንዘ ፡ ኢተኃድር ፡ ውስተ ፡ ሥጋ ነበረት ፡ ውስተ ፡ ሕይወት

፯ ፤ የመላእክት ፡ ተፈጥሮ በኀሊና ፡ ሲያስቡት ፡ ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ ድንቅነቱም ፡ ለሰው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለመላእክትም ፡ እንኳ ፡ ለራሳቸው ፡ አስደናቂ ፡ ሁኖባቸዋል ።

፰ ፤ እግዚአብሔር ፡ በረቂቅ ፡ ባሕርዩ ፡ ተሰወራቸው ፡ ይህንም ፡ ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ ከማለት ፡ በስተቀር ፡ ለመናገር ፡ የማይቻል ነው ።

፱ ፤ ሰው ፡ የመላእክትን ፡ ተፈጥሮ ፡ ተመራምሮ ፤ ለማወቅ ፡ የሚቻለው ፡ ቢሆን ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ፈጽሞ ጥንተ ፡ ተፈጥሮአቸውን ፡ በረቂቅ ፡ ነፋስና ፡ በሚያቃጥል ፡ እሳት ፡ መሰላቸው ።

፲ ፤ የመላእክትን ፡ ተፈጥሮ ፡ ዐውቃለሁ ፡ የሚል ፡ ቢኖር ፡ ነፍስ ፡ ከወዴት ፡ እንደተገኘች፡ አስጨናቂ ፡ ከሆነ ፡ እንግዲያማ ፡ ሐሰት ፡ ነዋ ! የመላእክትስ ባሕርይ ፡ ከጥንታዊው ፡ ባሕርየ ፡ ጥበቡ ፡ የተገኘ ፡ ነው ።

፲፩ ፤ መላእክትን ፡ ለምስጋና ከመፍጠሩ ፡ በፊት ፡ ምስጋናው፡ ያለመጓደል ፡ ያለ ፡ ነው ። እሱ ፡ ከዓለም ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ ከዓለምም ፡ በኋላ ፡ የሚኖር ፡ ነውና ።

፲፪ ፤ እንደዚሁም ፡ ነፍስ ፡ በሥጋ ከመዋሐዷ ፡ በፊት ፡ አስደናቂ በሚሆን ፡ ሕይወት ፡ ውስጥ ነበረች ።

፲፫ ፤ ብሂለ ፡ ከመዝሰ ፡ ዕጹብ ውእቱ ፡ ኢይትከሃል ፡ ለሰብእ፡ እንዘ ፡ ኅቡእ ፡ ውእቱ ፡ ባሕርየ ፡ ነፍስ ፡ ክሡት ፡ ኮነ ፡ ሶበ ፡ ኀደረ ፡ በሥጋ ፡ ቀይሕ ።

፲፬ ፤ ወእምዝ ፡ እምኀቡዓተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ ርእሰ ፡ መላእክት ፡ አስተጋብኦሙ ፡ በኅቡአቲሁ ።

፲፭ ፤ ወተከሐዱ ፡ ወተስሕቱ መላእክተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በበ ይናቲሆሙ ፡ ወተዓቅፉ ፡ በዝንቱ ፡ ነገር ።

፲፮ ፤ እስመ ፡ ተጸለለ ፡ ልቦሙ እምብርሃን ፡ ወስዕነ ፡ አሚኖ ቶሙ ፡ ወስሕተ ፡ ልቦሙ ። ወኃ ሠሡ ፡ ተኃጕሎቶሙ ።

፲፯ ፤ ወሠራዊተ ፡ ሚካኤል ፡ በበነገዶሙ ፡ ይቀውሙ ፡ ዓውደ ፡ መንበሩ ፡ ለልዑል ፡ መፍርህ ፡ ወመደንግፅ ።

፲፰ ፤ ወሠራዊተ ፡ ገብርኤል ፡ በበጾታሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ጽርዓት በኢያርምሞ ፡ ይሴብሕዎ ፡ ለእ ግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ ።

፲፱ ፤ ወካልአንሂ ፡ መላእክት ሱራፌል ፡ ወኪሩቤል ፡ ያዓብ

፲፫ ፤ የነፍስ ፡ ባሕርይ ፡ የተሰ ወረ ፡ ሁኖ ፡ ሳለ ፡ በግዙፍ ፡ ሥጋ አድሮ ፡ የተገለጠ ፡ ቢሆንም ፡ የነፍስንና ፡ የመላእክትን ፡ ባሕ ርይ ፡ መርምሮ ፡ አውቃለሁ ፡ ማለት ፡ ለሰው ፡ እጅግ ፡ አስጨ ናቂ ፡ ነው ።

፲፬ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ከከሃሊነቱ ፡ የተነሣ ፡ ከርእሰ ፡ መላእክት ፡ ጋር ፡ አስ ተባበራቸው ።

፲፭ ፤ የእግዚአብሔር ፡ መላእ ክትም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ተደናቀፉና ፡ ሁኔታውን ፡ ያወጡ ፡ ያወርዱ ፡ ጀመር ።

፲፮ ፤ ስለሆነም ፡ እምነታቸው ተንደለ ፤ ኅሊናቸውም ፡ ሳተ ፡ ጥፋታቸውንም ፡ ፈለጉ ፡ ልባቸው ፡ ከዕውቀት ፡ ብርሃን ፡ ተሰው ሯልና ።

፲፯ ፤ የሚካኤል ፡ ሠራዊት ፡ ግን ፡ ግሩምና ፡ አስፈሪ ፡ በሆነ በልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐደ ባባይ ፡ በየነገዳቸው ፡ ጸጥ ፡ ብለው ፡ ቆመዋል ።

፲፰ ፤ የገብርኤልም ፡ ሠራዊት ፡ በየወገናቸው ፡ ሆነው ፡ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ ያለማቋረጥና ፡ ያለ ፡ ዝምታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመ ሰግኑ ፡ ነበር ።

፲፱ ፤ ሌሎቹም ፡ መላእክት ፡ ሱራፌልና ፡ ኪሩቤል ፡ አንድ ፡



ይዎ ፡ ወይሴብሕዎ ፡ ለትሥል ስተ ፡ መለኮቱ ፡ በዋሕድና ።

፳ ፤ ወእሉሂ ፡ ሕያዋን ፡ እሙ ንቱ ፡ ኢይመውቱ ፡ ወኢይደ ክሙ ፡ ለማኅሌት ፡ ወለሰብሐተ ፡ እግዚእሙ ፡ በአርያም ።

፳፩ ፤ ዑራኤል ፡ ወሩፋኤል ፡ ትጉሃን ፡ እለ ፡ ኢይነውሙ ፡ በበነገዶሙ ፡ ይሴብሕዎ ፡ ለእ ግዚአብሔር ።

፳፪ ፤ ወሀለዉ ፡ በበሙፋሮሙ ምሉአነ ፡ አዕይንት ፡ እልፍ ፡ አእ ላፋት ፡ እሳታውያን ፡ ይሴብሕዎ ወይባርክዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ሠራዊተ ፡ መላእክት ፡ ወሊጉላቋሆሙኒ ፡ አልቦቱ ፡ ወሰን ።

፳፫ ፤ ፯ወ፱ቱ ፡ ነገደ ፡ መላ እክት ፡ ስርግዋነ ፡ መብረቅ ፡ ይሴብሕዎ ፡ ወየአኵትዎ ። ለእ ግዚአብሔር ።

፳፬ ፤ ወሰብልያኖስሰ ፡ አስሔ ቶሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ተላውያኒሁ ፡ መላእክት ፡ በብሂለ ፡ አምላክ ፡ አነ ።

፳፭ ፤ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ተቃ ሐዉ ፡ ጸርሐ ፡ ገብርኤል ፡ መል አክ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አሜሃ ፡ ንቁም ፡ በበህላዌነ ፡ እስከ ፡ ንረክቦ ፡ ለአምላክነ ።

ነቱን ፡ ሦስትነቱን ፡ ክፍ ፡ ክፍ በማድረግ ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ ያመ ሰግኑት ፡ ነበር ።

፳ ፤ እነሱም ፡ ሕያዋን ፡ ናቸው፡ በአርያም ፡ ያለ ፡ ጌታቸውን ፡ በፍጹም ፡ ምስጋና ፡ ለማመስገን ፡ ድካም ፡ የለባቸውምና ።

፳፩ ፤ ዕንቅልፍ ፡ የሌላቸው ፡ ትጉሃን፡ የሚሆኑ ፡ ዑራኤልና ፡ ሩፋ ኤልም ፡ በየነገዳቸው ፡ እግዚአ ብሔርን ፡ ያመሰግናሉ ።

፳፪ ፤ ለብዛታቸው ፡ ወሰን ፡ ሥፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ ሁለ ንተናቸው ፡ በዓይን ፡ የተመላ ፡ እልፍ ፡ አእላፋት ፡ እሳታውያን ፡ ሠራዊት ፡ መላእክት ፡ በየተመ ደቡበት ፡ ቦታ ፡ ሆነው ፡ እግዚ አብሔርን ፡ ያመሰግኑታል ፡ ያገ ኑታልም ።

፳፫ ፤ መብርቅትን ፡ የተጐናጸፉ ዘጠና ፡ ዘጠኙ ፡ ነገደ ፡ መላእክት እግዚአብሔርን ፡ ፈጽመው ፡ ያመ ሰግናሉ ።

፳፬ ፤ ሰብልያኖስ ፡ ግን ፡ አም ላክ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ የሱን ፡ ተከታዮች ፡ መላእክት ፡ ሁሉንም አሳታቸው ።

፳፭ ፤ ክርክር ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ መልአኩ ፡ ገብርኤል ፡ ፈጣሪያ ችንን ፡ እስክናገኘው ፡ ድረስ ፡ በያለንበት ፡ ጸጥ ፡ ብለን ፡ እንቁም በማለት ፡ አሰምቶ ፡ ተናገረ ።

፳፮ ፡ ወሰሚዖሙ ፡ ቃለ ፡ ገብርኤል ፡ መልአክ ፡ ሐድኦ ፡ እምሑከቶሙ ፡ ኵሎሙ ፡ ትዕይንተ ፡ መላእክት ፡ እምብሂለ ፡ መኑ ፡ ፈጠረነ ፡ ወመኑ ፡ አምላክነ ፡ ወመኑ ፡ እንጋ ፡ ይከውን ፡ እምላክነ ፡ በብሂሎቶሙ ፡ ዘነበሩ ፡ በዝንቱ ፡ ጻሕቀ ፡ ኀሊና ፡ ውዑይ ፡ ወበተስእሎት ፡ ብዙኅ ፡

፳፯ ፡ ወእመ ፡ ሕቀ ፡ እመኢጸርሐ ፡ ቃለ ፡ ገብርኤል ፡ እምክህዱ ፡ ወእምስሕቱ ፡ ኵሎሙ መላእክት ።

፳፰ ፡ ወካዕበ ፡ ተብህለ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ እመ ፡ ኢኮነ ፡ ዝንቱ መኑ ፡ ፈጠረነ ፡ ከመ፡ንትናገር ፡ ህልውናሁ ፡ ለአብ ፡ ወብርሃነ ፡ ጽድቁ ፡ ለወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥልሰ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ እምኑ ።

፳፱ ፡ ወካልእንሂ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ መኑ ፡ እንጋ ፡ እግዚእ ፡ ኵልነ ፡ ወሚጠ፡ ቃሎሙ፡ ዳግመ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ መኑ ፡ ፈጠረነ ፡ በጽልመት ።

፴ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ነቢይ ፡ ወረሰየ ፡ ጽልመተ ፡ ምስዋሮ ፡ ወዓውዶሂ ፡ ጽላሎቱ ።

፴፩ ፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ለይኩን ፡ ብርሃን ፡ ለዓለም ።

፳፮ ፡ ማን ፡ ፈጠረን ፡ ማነው ፡ አምላካችን ? ፈጣሪያችንስ ፡ የሚሆን ፡ ማነው ፡ እንጃ ፡ በሚል ፡ ሐሳብ ፡ ተውጠውና ፡ በብዙ ፡ መጠያየቅ ፡ ተጨንቀው ፡ የነበሩት ፡ ነገደ ፡ መላእክት ፡ ሁሉ ፡ የመልአኩ ፡ የገብርኤልን ፡ቃል ፡ ሰምተው ፡ ጸጥ ፡ አሉ ።

፳፯ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ መልአኩ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ጸጥ ፡ በሉ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ቃል ፡ አሰምቶ ፡ ባይናገር ፡ ኑሮ ፡ ጨርሰው ፡ መላእክት ፡ ሁሉ ፡ በካዱና ፡ በሳቱ ፡ ነበር ።

፳፰ ፡ ዳግመኛም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡የእውነተኛው ፡ ብርሃን ፡ የእግዚአብሕርን ፡ ልጅና ፡ የአብን ፡ ህልውና ፡ እንድንናገር ፡ ያደረገን ፡ ይህ ፡ አምላካችን ፡ ካልሆነ ፡ ማን ፡ ፈጠረን ፡ በማለት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ፡ ህልውናውን፡ አመኑ።

፳፱ ፡ ሌሎቹም ፡ የሁላችን ፡ ጌታ ፡ ማነው ? ካሉ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ደግሞ ፡ በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ የፈጠረን ፡ ማን ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ተለዋወጡ ።

፴ ፡ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፡ በትንቢቱ ፡ መሰወሪያውን ፡ ጨለማ ፡ ዐደባባዩንም ፡ ጥላው ፡ አደረገ ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ።

፴፩ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ብርሃን ፡ ይሁን ፡ አለ ።



፴፪ ፡ ወሶቤሃ ፡ ተከሥተ ፡ ብርሃን ፡ ማእከለ ፡ ጽልመት ፡ ብርሃን ፡ ዘበአማን ፡ ዘላዕሌሁ ፡ ወዘታሕቴሁ ።

፴፫ ፡ ወባሕቱ ፡ ብዙኃን ፡ መላእክት ፡ ወድቁ ፡ እመዓርጊሆሙ ፡ በትዕቢተ ፡ ሊቆሙ ፡ ሥርዋ ለዓመፃ ፡ ወመልአክ ፡ በቀል ።

፴፬ ፡ ወኅሩያንሂ ፡ መላእክት ፡ ፍጡር ፡ አንተ ፡ ከማነ ፡ እመ ፡ ይቤልዎ ፡ አንሰኬ ፡ ፈጣሪ ፡ አነ፡ በብሂሎቱ ፡ ወድቀ ፡ እመዓርጊሁ ።

፴፭ ፡ ወተረክበ ፡ እንዘ ፡ የኃሥሥ ፡ መንግሥቶ ፡ ወጽድቆ ፡ ለአምላክነ ።

፴፮ ፡ ወይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሰብልያኖስ ፡ ስምከ ፡ ይኩን ፡ ሰይጣን ፡ እስመ ፡ ብሂለ ፡ ሰይጣን ፡ ውዱቅ ፡ ወርኁቅ ፡ እምነ ፡ ክብር ።

፴፯ ፡ ወተበውሐ ፡ ላዕሌሁ ፡ ትዕቢት ፡ ወዓመፃ ፡ ያስተብዕል ፡ ወይሜህር ፡ ትዕቢተ ፡ ለነፍስ ፡ ኵሉ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

፴፪ ፡ በጨለማው ፡ መካከል ፡ በላይም ፡ በታችም ፡ እውነተኛ ፡ ብርሃን ፡ ይሁን ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ወዲያው ፡ ብርሃን ፡ ተገለጠ ።

፴፫ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በአለቃቸው ፡ ትዕቢት ፡ ብዙዎቹ ፡ መላእክት ፡ ከመዓርጋቸው ፡ ወደቁ ፡ ተዋረዱ ፡ እሱ ፡ አለቃቸው ፡ ለዓመፅ ፡ መሠረቷ ፡ ለቂም ፡ በቀልም ፡ ጌታዋ ፡ ነውና ።

፴፬ ፡ የመኑ ፡ የተመረጡ መላእክት ፡ ማን ፡ አንተ ፡ እንደኛው ፡ ፍጡር ፡ ነህ ፡ ስላሉት ፡ እኔስ ፡ ፈጣሪ ፡ እንጂ ፡ ነኝ ፡ በማለቱ ፡ ከማዕርጉ ፡ ወደቀ ፡ ተዋረደ ።

፴፭ ፡ የአምላካችንን ፡ መንግሥቱንና ፡ እውነተኛ ፡ ፈጣሪነቱን ፡ ክዶ ፡ አምላክነቱን ፡ሲሻ ፡ ተገኝቷልና ።

፴፮ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሰብልያኖስን ፡ እንግዲህ ፡ ስምህ ፡ ሰይጣን ፡ ተብሎ ፡ ይጠራ ፡ ሰይጣን ፡ ማለት ፡ ከማዕርጉ ፡ የወደቀ ፡ ከክብሩ ፡ የተዋረደ ፡ ከክብር ፡ ይልቅ ፡ ውርደትን ፡ የመረጠ ፡ ማለት ፡ ነውና ።

፴፯ ፡ ከራሱ፡ ላይ ፡ ትእቢትና ፡ ተንኰል ፡ የሰለጠነበት ፡ ለሰውም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ትዕቢትን ፡ የሚያስተምርና ፡ የሚያባልግ ፡ ነውና ።

፴፰ ፤ ከመ ፡ ይቤ ፡ ኢዮብ ፡ ትዕቢትስ ፡ ኢተፈጥረ ፡ ለዘተወልደ ፡ እምብእሲት ፡ ዘእንበለ ፡ ለአሐዱ ፡ ሰይጣን ፡ በእንተ ፡ እከዩ ፡ ወዓመፃሁ ፡ ዘወዕአ ፡ እምልቡ ፡ ቀቲለ ፡ ነፍስ ፡ ወሐይድ ።

፴፱ ፤ ወበእንተዝ ፡ አትሐተ ፡ ወአውደቀ ፡ እግዚአብሔር ዘይገብር ፡ ትዕቢተ ፡ ወትዝህርተ ፡ ውስተ ፡ ገጸ ፡ ሊቁ ።

፵ ፤ ወአስተፋነዎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዲያብሎስ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ሠራዊቱ ፡ ውስተ ፡ ከርሠ ፡ ሲኦል ፡ ወአንበሮ ፡ ህየ ፡ ኀበ ፡ ዘእኩይ ፡ ምግባሩ ።

፵፩ ፤ ወሶበ ፡ ርእዩ ፡ ብርሃነ ፡ እንዘ ፡ ይውኅዝ ፡ እምሥራቅ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ አምኑ ፡ ኵሎሙ ፡ መላእክት ፡ ወሊቃነ ፡ መላእክት ፡ ወሰገዱ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዕበየ ፡ መለኮቱ ፡ ወለትሥልስቱ ፡

፵፪ ፤ ወእምድኅረ ፡ አስተኖበረ ፡ እግዚአብሔር ፡ሰማየ ፡ ወምድረ ፡ በጥበቢሁ ፡ ዘገብረ ፡ ኵሎ ፡ዓለመ ፡ ወዘውስቴቱ ፡ እስከ ፡ የኃልፉ ፡ ብዙኃን ፡ ዕለታት ፡ ተፈሥሐ ፡በመላእክቲሁ ፡ ኅሩያን ።

፵፫ ፤ ወትንሥአ ፡ ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ወገብርኤል ፡

፴፰ ፤ ኢዮብ ፡ ትዕቢት ፡ በሥጋ ፡ ከተወለደ ፡ ከሴት ፡ ልጅ ፡ አልተገኘም ፡ በተንኰሉና ፡ በክፋቱ ፡ ቅሚያንና ፡ ነፍስ ፡ ማስገደልን ፡ ከልቡ ፡ የሚያመነጭ ፡ ከአንዱ ፡ ከሰይጣን ፡ በቀር ።

፴፱ ፤ ዳግመኛም ፡ እግዚአብሔር ፡ በአለቃው ፡ ፊት ፡ የሚኰራና ፡ የሚታበየውን ፡ አዋርዶታል ፡ ጥሎታልም ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ።

፵ ፤ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዲያብሎስን ፡ በክፉ ፡ ሥራው ፡ የተነሣ ፡ ከነሠራዊቱ ፡ በሲኦል ፡ በጨለማ ፡ ሥቃይ ፡ እንዲኖር ፡ አሰናበተው ።

፵፩ ፤ ብርሃን ፡ ከምሥራቅ ፡ ወደጨለማው ፡ ክፍል ፡ ሲጐርፍ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ መላእክትና ፡ ሊቃነ ፡ መላእክት ፡ ሁሉ ፡ አመኑና ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡እያሉ ፡ ለአንድነቱና ፡ ለሦስትነቱ ፡ ለጌትነቱ ፡ ክብር ፡ ሰገዱ ።

፵፪ ፤ እግዚአብሔር ፡ በጥበቡ ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ በውስጡ ፡ ያለውንም ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ካዘጋጀ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ቀኖች ፡እስኪያልፉ ፡ ድረስ ፡ በተመረጡ ፡ መላእክቶቹ ፡ ተደሰተ ።

፵፫ ፤ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ ሚካኤልና ፡ ገብርኤል ፡ አንድ



ኀቡረ ፡ ከመ ፡ ይትበዓሱ ፡ ወይትቃተሉ ፡ ምስለ ፡ ሠራዊተ ፡ ዲያብሎስ ፡ በቀስት ፡ ወበሰይፍ ፡ ዘመብረቅ ፡ ወባሕቱ ፡ ኢሞእዎ ፡ በጊዜሁ ፡ ወኢጐየ ።

፵፬ ፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ተሥዕለ ፡ በክነፊሆሙ ፡ ከመ ፡ ይማእዎ ፡ በነደ ፡ እሳት ፡ በብሂለ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፩ዱ ፡ አምላክ ።

፵፭ ፤ሶበ ፡ ርእየ ፡ ዲያብሎስ ፡ ዘንተ ፡ ሥዕለ ፡ ክነፊሆሙ ፡ ወድቀ ፡ እመንበሩ ፡ ወጐዩ ፡ ሠራዊቱ ፡ ውስተ ፡ ደይን ።

፵፮ ፤ወአንበሮ ፡ ለዲያብሎስ ፡ ህየ ፡ እስከ ፡ ሕልቀተ ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡ ይትወከፍ ፡ ሥቃየ ፡ ለሲኦል ፡ ወኵነኔሃ ።

፵፯ ፤ ወመላእክተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሚካኤል ፡ ወገብርኤል ፡ ሱራፌል ፡ ወኪሩቤል ፡ ወኵሎሙ ፡ ኅሩያኒሁ ፡ አልዓሉ ፡ ወአዕበዩ ፡ ስሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ስብሐት ፡ ለወልድ ፡ ስብሐት ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፵፰ ፤ ጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ የሃሉ ፡ ምስለ ፡ ገብሩ ።

ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ነት ፡ ሁነው ፡ ዲያብሎስን ፡ ከነሠራዊቱ ፡ ድል ፡ ለማድረግ ፡ በመብረቅ ፡ የተሸፈነ ፡ ጦርና ፡ ሰይፍን ፡ በመያዝ ፡ ሊዋጉት ፡ ተነሡ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለጊዜው ፡ ስላላሸነፉት ፡ አልሸሸም ።

፵፬ ፤ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ድል ፡ ለማድረግ ፡ ይችሉ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ የሚሆን ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በቀለመ ፡ እሳት ፡ በክንፋቸው ፡ ላይ ፡ ተጻፈ ።

፵፭ ፤ ዲያብሎስ ፡ በክንፋቸው ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ጽሑፍ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ከዙፋኑ ፡ ወደቀ ፡ ሠራዊቱም ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ሸሹ ።

፵፮ ፤ ዲያብሎስን ፡ እስከ ፡ ኅልቀተ ፡ ዓለም ፡ የሲኦልን ፡ ሥቃይዋንና ፡ ቅጣቷን ፡ ይቀበል፡ ዘንድ ፡ ከዚያው ፡ አስቀመጠው ።

፵፯ ፤ የእግዚአብሔር ፡ መላእክት ፡ ሚካኤልና ፡ ገብርኤል ፡ ኪሩቤልና ፡ ሱራፌል ፡ የተመረጡም ፡ መላእክት ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ አገነኑ ፡ ከፍ ፡ ከፍም ፡ አደረጉ ፤ ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዛሬም ፡ ለዘወትርም ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ ምስጋና ፡ ይሁን፡ ምስጋና ፡ ይገባል ፡ እያሉ ፡ አመሰገኑ ።

፵፰ ፤ ልመናውና ፡ በረከቱ ፡ ከወዳጁ ፡ ጋር ፡ ለዘላለሙ ፡ ይሁን ፡ አሜን ።

## ተአምር ፡ ፩ ።

ተአምር ፡ ዘገብረ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ በሀገረ ፡ ድልማኑታ ።

፩ ፤ ወሀሎ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ ተንባላታዊ ፡ በሀገረ ፡ ድልማኑታ ፡ ወሥዩም ፡ ውእቱ ፡ ለምድረ ፡ ደንኩራር ።

፪ ፤ ወበጥቃ ፡ ኀሩ ፡ ሀለዉ ፡ ብእሲ ፡ ወብእሲት ፡ ክርስቲያናውያን ፡ ወእሉኒ ፡ ጥቀ ፡ ይፈርህዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወለቅዱስ ፡ ዑራኤልኒ ፡ ያፈቅርዎ ፡ ወይገብሩ ፡ ተዝካረ ፡ በዓሉ ፡ ወይሁቡ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ፡ ለለወርኁ ።

፫ ፤ ወዝንቱስ ፡ ብእሲ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ጥቀ ፡ ያፈቅሮ ፡ ለውእቱ ፡ ተንባላዊ ፡ በኵሉ ፡ ኀሊናሁ ፡ ይበልዕ ፡ ወይሰቲ ፡ ምስሌሁ ።

፬ ፤ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ ተዘከረ ፡ ከመ ፡ በጽሐ ፡ ዕለተ ፡ በዓሉ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ወይቤላ ፡ ለብእሲቱ ፡ አ ፡ እኅትየ ፡ አእምሪ ፡ ከመ ፡ የዮም ፡ በጽሐ ፡ ዕለተ ፡ በዓሉ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ።

፭ ፤ ቅድመ ፡ አስተዳልዊ ፡ ዘይደሉ ፡ ለዕለተ ፡ በዓሉ ።

፮ ፤ ወትቤሎ ፡ ብእሲቱ ፡ እሆ ፡ አ ፡ እኁየ ፡ ኵሉ ፡ ይትገበር ፡

## ፩ኛ ፡ ተአምር ።

ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ድልማኑታ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ ያደረገው ፡ ተአምር ፡ ይህ ፡ ነው ።

፩ ፤ ደንኩራር ፡ ለምትባል ፡ አውራጃ ፡ ሹም ፡ የሆነ ፡ በድልማኑታ ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ እስላም ፡ ነበር ።

፪ ፤ ክርስቲያኖች ፡ የሆኑ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ከቤቱ ፡ አጠገብ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ እነሱም ፡ ፈጽመው ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈሩና ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤልን ፡ ከመውደዳቸው ፡ የተነሣ ፡ በየወሩ ፡ ዝክሩን ፡ እየዘከሩ ፡ ለድሆችና ፡ ለተጐዱ ፡ ሰዎች ፡ የሚሰጡ ፡ ነበሩ ።

፫ ፤ ይህም ፡ ክርስቲያን ፡ ሰው ፡ እስላሙን ፡ ከመውደዱ ፡ የተነሣ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ ይበላ ፡ ይጠጣ ፡ ነበር ።

፬ ፤ ከዕለታት ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ የቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ በዓል ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ አሰበና ፡ ሚስቱን ፡ እኅቴ ፡ ሆይ ፡ የቅዱስ ፡ ኡራኤል ፡ በዓል ፡ እንደደረሰ ፡ ዕወቂ ።

፭ ፤ በመጀመሪያ ፡ ለበዓሉ ፡ የሚሆን ፡ ወይም ፡ የሚገባውን ፡ አዘጋጅ ፡ አላት ።

፮ ፤ እሷም ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ እሺ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ በቤት ፡



ውስተ ፡ ቤትነ ፡ ባሕቱ ፡ አልብነ ፡ ዔው ፡ ሑር ፡ ኀበ ፡ ፍቁርከ ፡ ተንባላታዊ ፡ ለእመ ፡ ቦቱ ፡ ይሁበነ ፡ ወለእመ ፡ አልቦቱ ፡ ይትሌቃሕ ፡ ለነ ።

፯ ፤ ወሰሚዖ ፡ ምታ ፡ እሆ ፡ ብሂሎ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ተንባላታዊ ፡ ወነበቦ ፡ ከመ ፡ የሀቦ ።

፰ ፤ ውእቱኒ ፡ ተንባላታዊ ፡ ወሀቦ ፡ በፍሥሐ ፡ ዘሰዓሎ ።

፱ ፤ ወአሚሃ ፡ ተሰዓሎ ፡ ውእቱ ፡ ተንባላታዊ ፡ ለውእቱ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ምንተ ፡ ይገብር ፡ ለክሙ ፡ ዘትብልዎ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ዘትገብሩ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ፡ ለለወርኁ ፡ መብልዓ ፡ ወመስቴ ፡ ለነዳያን ፡ በስሙ ።

፲ ፤ ስምዓኒ ፡ አ ፡ እኁየ ፡ ነገረ ፡ ዘእነግረከ ፡ አነኒ ፡ ወብእሲትየ ፡ ነበርነ ፡ በሕማም ፡ ወበጻዕር ፡ እምንእስነ ፡ ብዙኃ ፡ አዝማነ ፡ ባሕቱ ፡ እንዘ ፡ ንሔውር ፡ ኵሎ ፡ ዕለተ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ዘተጸለየ ፡ ቦቱ ፡ በስሙ ፡ ንሰቲ ፡ ወንጠመቅ ፡ ወእምድኅሬሁኒ ፡ በብዙኅ ፡ ዕለታት ፡ ንሕነኒ ፡ ወብእሲትየ ፡ እምሕማምነ፡ ወእምደዌነ ፡ ዘተሳቀይነ ፡ ቦቱ ፡ በይነ ፡ ዘአድኃነነ ፡ ንገብር ፡ በዓሎ ፡ ለወርኁ ፡ ይቤሎ ።

፲፩ ፤ ወካዕበ ፡ አነኒ ፡ እንዘ ፡ አሐውር ፡ ማእከለ ፡ ገዳም ፡ ወሐ

ይዘጋጃል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጨው ፡ ስለሌለን ፡ ከወዳጅህ ፡ ከእስላሙ ፡ ዘንድ ፡ ሂደህ ፡ አምጣ ፡ ቢኖረው ፡ ይሰጥሃል ፡ ከሌለውም ፡ ይበደርልሃል ፡ አለችው ።

፯ ፤ ባልየውም ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ሄዶ ፡ እስላሙን ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ለመነው ።

፰ ፤ እስላሙም፡ የለመነውን ፡ በደስታ ፡ ሰጠው ።

፱ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ እስላሙ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ እያላችሁ ፡ በየወሩ ፡ ድሆችን ፡ የምታበሉና ፡ የምታጠጡ ፡ ይህ ፡ ዑራኢል ፡ የምትሉት ፡ ምን ፡ ሊያደርግላችሁ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ።

፲ ፤ ክርስቲያኑም ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ስማኝ ፡ የዚህን ፡ ነገር ፡ እነግርሃለሁ ፡ እኔና ፡ ሚስቴ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ በበሽታ ፡ ስንሠቃይ ፡ ኑረናል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እየሄድን ፡ በስሙ ፡ የተጸለየበትን ፡ ማየ ፡ ጸሎት ፡ እንጠጣለን ፡ እንጠመቃለንም ፡ ከብዙ ዕለታት ፡ በ፡ኋላ ፡ ግን ፡ ስንሠቃይበት ፡ ከነበርነው ፡ በሽታችን ፡ ስለአዳነን ፡ በበዓሉ ፡ ቀን ፡ በየወሩ ፡ እንዘክራለን ፡ አለው ።

፲፩ ፤ ዳግመኛም ፡ እኔ ፡ በበረሃ ፡ ውስጥ ፡ ስሄድ ፡ ሰው ፡ የሚ

ቅል ፡ ተንሥአ ፡ ብየ ፡ ዓቢይ ፡ ተመን ፡ ዘይውኅጥ ፡ ሰብአ ፡ ከመ ፡ የኃጠኒ ፡ ወአሜሃ ፡ ጸዋዕኩ ፡ ስሞ ፡ **ለአምላከ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል** ፡ ወውእተ ፡ አሚረ ፡ ቀይሕ ፡ ሰብእ ፡ እንዘ ፡ ይነሥእ ፡ ኵናተ ፡ መጽአ ፡ ኀቤየ ፡ ወገሠጸ ፡ ከመ ፡ ይርግዞ ፡ ወሰበርእየ፡ ኵናቶ ፡ ውእቱ ፡ ተመንገሮየ ፡ ኃዲጎ ፡ ኪያየ ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ ፍኖት ።

፲፪ ፤ **ወውእተ ፡ ጊዜ** ፡ ይቤለኒ ፡ ዘአድኃነኒ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ **ዑራኤል ፡ መልአክ** ፡ ዘአድኃንኩከ ፡ በኃይለ ፡ አምላኪየ ፡ ብሂሎ ፡ ተሰወረ ፡ እምአዕይንትየ ።

፲፫ ፤ **ወበዝንቱ፡ ምግበሪሁ፡**ወመንክራቲሁ ፡ ናፈቅሮ ፡ ወናዓብዮ ፡ **ለቅዱስ ፡ ዑራኤል** ፡ ከመ ፡ ያድኅነነ ፡ በሥጋነሂ ፡ ወበነፍስነሂ ፡ እምኵሉ ፡ መንሱት ፡ ወካዕበ ናከብር ፡ በዓሎ ፡ ለለወርኁ ፡ በውሂበ ፡ ንዋይ ፡ ለነዳያን ፡ ይእዜኒ ፡ ከመ ፡ ያድኅነነ ፡ እመንሱት ።

፲፬ ፤ **ወተመስጠ ፡ ኅሊናሁ** ፡ በነገረ ፡ ዝንቱ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ውእቱ ፡ ተንባላታዊ ፡ ወእምአሜሃ ፡ ኃደረ ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡ ፍቅሩ ፡ **ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት** ።

፲፭ ፤ **ወእምዝ ፡ ተመይጠ** ፡ ውእቱ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ነሚኦ ፡

ውጥ ፡ ዘንዶ ፡ አገኘኝና ፡ ሊውጠኝ ፡ ፈልጎ ፡ ሳለ ፡ **የዑራኤል ፡ አምላክ** ፡ አድነኝ ፡ በማለት ፡ ስሙን ፡ በጠራሁ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ቀይ ፡ ሰው ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ መጣና ፡ ዘንዶውን ፡ ቢያስፈራራው ፡ ወዲያውም ፡ ሊወጋው ፡ ሲል ፡ ዘንዶው ፡ ሸሽቶ ፡ ሄደ ።

፲፪ ፤ **ያን ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ያዳነኝ** ፡ ሰው ፡ በፈጣሪዬ ፡ ኃይል ፡ ያዳንኩህ ፡ እኔ ፡ **መልአኩ ፡ ዑራኤል** ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ከዓይኔ ፡ ተሰወረ ።

፲፫ ፤ **እንግዲህ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤልን** ፡ የምናከብረውና ፡ የምናፈቅረው ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ርዳታውና ፡ ተአምራቱ ፡ ነው ፡ ይልቁንም ፡ በሥጋችንና ፡ በነፍሳችን ፡ እንዲያድነን ፡ ስንል ፡ ዳግመኛም ፡ በየወሩ ፡ ለነዳያን ፡ ገንዘባችንን ፡ እየሰጠን ፡ በዓሉን ፡ የምናከብረው ፡ ዛሬም ፡ ከጥፋት ፡ ሁሉ ፡ እንዲያድነን ፡ ነው ፡ አለው ።

፲፬ ፤ **በክርስቲያኑ ፡ አነጋገር** ፡ የተነሣ ፡ የእስላሙ ፡ ሕሊና ፡ ተመሰጠና ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ የሚሆን ፡ **የቅዱስ ፡ ዑራኤል** ፡ ፍቅር ፡ በልቡ ፡ አደረበት ።

፲፭ ፤ **ከዚህ ፡ በኋላ** ፡ ክርስቲያኑ ፡ ከእስላሙ ፡ እጅ ፡ ጨውን ፡



ጊወ ፡ እምእዴሁ ፡ ለተንባላታዊ ፡ ሖረ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ወወሀባ ፡ ለብእሲቱ ።

፲፮ ፤ **ወይእቲ ፡ ብእሲት** ፡ ፈጸመት ፡ ኵሎ ፡ ሥርዓተ ፡ ቤታ ፡ በጥቡዕ ፡ ልብ ፡ ወእምዝ ፡ ወሀቡ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ፡ በዕለተ ፡ በዓሉ ፡ **ለቅዱስ ፡ ዑራኤል** ፡ ወአሥመርዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ገባሬ ፡ ተአምር ፡ ወመንክር ።

፲፯ ፤ **ወእንዘ ፡ ሀለዉ** ፡ በዘከመዝ ፡ ግብር ፡ አዕረፉ ፡ በሰላም ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡

፲፰ ፤ **ውእቱሰ ፡ ተንባላታዊ** ፡ ሥዩመ ፡ ደንኰራር ፡ ነጋዲ ፡ ውእቱ ፡ በግብሩ ።

፲፱ ፤ **ወአሐተ ፡ ዕለተ** ፡ እንዘ ፡ የሐውሩ ፡ ነጋድያን ፡ ሖረ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ወበዊኦ ፡ ማእከለ ፡ ባሕር ፡ ነበረ፡ በየማነ ፡ ጥቃሃ ፡ ለሐመር ።

፳ ፤ **ወመጽአ ፡ ነፋስ ፡ ዓውሎ** ፡ እምዓረብ ፡ ወአንቀልቀላ ፡ ለይእቲ ፡ ሐመር ፡ እስከ ፡ ይሰጠሙ ፡

፳፩ ፡ **ወአሜሃ ፡ በፅዑ** ፡ በከመ ፡ ልማዶሙ ፡ መብዓ ፡ ዘይሁቡ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመ ፡ ያድኅኖሙ ፡ እምኃጕል ፡ ወያግብኦሙ ፡ ውስተ ፡ ብሔሮሙ ፡ በዳኅና ፡ ወበሰላም ።

ተቀበለና ፡ ወደቤቱ ፡ ሂዶ ፡ ለሚስቱ ፡ ሰጣት ።

፲፮ ፤ **ሚስቲቱም ፡ በትጋት** ፡ የቤቷን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አዘጋጅታ ፡ ከጨረሰች ፡ በኋላ ፡ ለድሆችና ፡ ረዳት ፡ ለሌላቸው ፡ **በቅዱስ ፡ ዑራኤል** ፡ ስም ፡ ሰጡና ፡ ወይም ፡ መጸወቱና ፡ ድንቅ ፡ ተአምር ፡ የሚሠራ ፡ እሱን ፡ ደስ ፡ አሰኙት ።

፲፯ ፤ **በዚህም ፡ ዓይነት** ፡ ሥራቸው፡ ሳሉ ፡ ከዚህ ፡ከኃላፊው፡ ዓለም ፡ በሰላም ፡ ዐረፉ ።

፲፰ ፤ ያ ፡ **የደንኰራር ፡ አገር** ፡ ሹም ፡ የሆነ ፡ እስላም ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ ንግድ ፡ ነበር ።

፲፱ ፤ **ከዕለታት ፡ በአንድ ፡ ቀን** ፡ ነጋዴዎች ፡ ወደ ፡ ንግድ ፡ ሲሄዱ ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ሄደና ፡ ከባሕር ፡ መካከል ፡ ገብቶ ፡ በመርከቢቱ ፡ ላይ ፡ በስተቀኝ ፡ በኩል ፡ ተቀመጠ ።

፳ ፤ **ከምዕራብ ፡ በኩል** ፡ ዓውሎ፡ ነፋስ ፡ ተነሥቶ ፡ መርከቢቱ ፡ ለመስጠም ፡ እስከምትደርስ ፡አንቀወጣት ።

፳፩ ፤ **ያን ፡ ጊዜ** ፡ እንደ ፡ ልማዳቸው ፡ ከጥፋት ፡ አድኖ ፡ በሰላም ፡ በጤና ፡ ወደሀገራቸው ፡ ይመልሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚሰጡትን ፡ መብዓ፡ ተሳሉ ።

፳፪ ፤ ወውእቱኒ ፡ መስልም ፡ ውስተ ፡ ጥቃ ፡ ሐመር ፡ ከዊኖ ፡ በፅዓ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ መልአከ ምሕረት ፡ ወማህል ።

፳፫ ፤ እስመ ፡ ቅሩብ ፡ ውእቱ ፡ መካኑ ፡ ለውእቱ ፡ መስልም ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፤

፳፬ ፤ ወእምቀዲሙ ፡ አእመረ ፡ ከመ ፡ ይባልሕ ፡ ሰብኤ ፡ በረድኤቱ ፡ ለዘሰአሎ ፡ እምልብ ።

፳፭ ፤ ወሶቤሃ ፡ አርመመ ፡ ማዕበል ፡ ወኮነ ፡ ዛኅነ ፡ ወቃለፉ ፡ ኵሎሙ ፡ ነጋድያን ፡ በሰላም ።

፳፮ ፤ ወሐሩ ፡ ብሔረ ፡ ቂሳ ርያ ፡ ወቦኡ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ለኤፍሬም ፡ ወቤቱ ፡ እንዘ ፡ ይበልዑ ፡ ወይሰትዩ ፡ እስመ ። ርእሰ ፡ ነጋድያን ፡ ውእቱ ።

፳፯ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ ሐሩ ብሔረ ፡ ርኁቀ ፡ በውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ወገብኡ ፡ ብሔሮሙ ፡ በዳኅና ፡ ወበሰላም ።

፳፰ ፤ ወውእቱሰ ፡ ተንባላታዊ፡ በእንተ ፡ ዘቦአ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ በሰላም ፡ ወበዳኅና ፡ ነሥአ ፡ ውእተ ፡ ብሩረ ፡ ዘበፅዓ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ወወሀቦ ፡ ለዓቃቤ ፡ ቤተ ፡ ክር

፳፪ ፤ እስላሙም ፡ በመርከቡ ፡ ውስጥ ፡ ሁኖ ፡ የይቅርታና ፡ የምሕረት ፡ መልአክ ፡ የሚሆን ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ተሳለ ።

፳፫ ፤ የእስላሙ ፡ ቤት ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ ከሆነ ፡ ከቅዱስ፡ ዑራኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አጠገብ ፡ ነውና ።

፳፬ ፤ ከልብ ፡ ለለመነው ፡ በረዳትነቱ ፡ ሰውን ፡ የሚያድን ፡ መሆኑን ፡ አስቀድሞ ፡ ተረድቷልና ።

፳፭ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ማዕበሉ ፡ ጸጥ ፡ አለና ፡ ነጋዴዎቹ ፡ ሁሉ ፡ በሰላም ፡ ተሻገሩ ።

፳፮ ፤ ከዚያም ፡ ቂሳርያ ፡ ወደ ሚባል ፡ አገር ፡ ሄዱና ፡ ኤፍ ሬም ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ ሲበሉ ፡ ሲጠጡ ፡ አደሩ ፡ እሱ ፡ የነጋዴ ዎች ፡ አለቃ ፡ ነውና ።

፳፯ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዚያን ፡ ሰሞን ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ሄዱና፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ በሰላም ፡ ተመለሱ ።

፳፰ ፤ ያ ፡ እስላም ፡ በሰላም ፡ በጤና ፡ ወደቤቱ ፡ ስለገባ ፡ ለቅ ዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ የተሳለውን ፡ ገንዘብ ፡ በብዙ ፡ መታመን ፡ ወስዶ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ጠባቂ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ በሦስት ፡ ሩብ



ስቲያን ፡ ሰቂሎ ፡ በሰቅለ ፡ ብሩር ፡ ወወርቅ ፡ በተሰፍዎቱ ፡ ብዙኃ ።

፳፱ ፤ ወእምድኅረ ፡ ኀዳጥ ፡ መዋዕል ፡ ውእቱ ፡ ተንባላታዊ ፡ አምነ ፡ ወተጠምቀ ።

፴ ፤ ወሰብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወአፍቀሮ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ወአኃዘ ፡ ይትለአክ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ምስለ ፡ ውሉዱ ፡ ወምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ እስመ ፡ አምኑ ፡ ኵሎሙ ፡ ኅቡረ ፡ ምስሌሁ ።

፴፩ ፤ ወበዘከመዝ ፡ ግብር ፡ እንዘ ፡ ሀለወ ፡ አዕረፈ ፡ በሰላም ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ኅላፊ ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ገነተ ፡ ትፍሥሕት ፡ በጸሎቱ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራ ኤል ።

፴፪ ፤ ጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ለቅ ዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእ ክት ፡ የሃሉ ፡ ምስለ ፡ ገብሩ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ካልእ ፡ ተአምር ።

ተአምር ፡ ዘገብረ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ የሃሉ፡ ምስለ ፡ ገብሩ ፡ ለዓ ለመ ፡ ዓለም ።

፩ ፤ ወሀሎ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ ዲያቆን ፡ ዘስሙ ፡ ባሮክ ፡ ዘይ

መዝኖ ፡ አጠፌታ ፡ አድርጎ ፡ ሰጠው ።

፳፱ ፤ ከጥቂት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ እስላም ፡ አመነና ፡ ተጠመቀ ።

፴ ፤ እግዚአብሔርን ፡ አመሰ ገነው ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤልንም ፡ አከበረው ፡ ወደደው ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያኑንም ፡ ከሚስቱና ፡ ከል ጆቹ ፡ ጋር ፡ ያገለግል ፡ ጀመር ፡ እነሱም ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ አምነዋ ልና ።

፴፩ ፤ በዚህ ፡ በሥራው ፡ ወይም ፡ በአገልግሎቱ ፡ ሳለ ፡ ከዚህ ፡ ከኃላፊው ፡ ዓለም ፡ ዐርፎ ፡ በቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ረዳትነት ፡ ደስታ ፡ ወደ፡አለበት ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ ገባ ።

፴፪ ፤ የቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ጸሎቱና በረከቱ ፡ ከወዳጁ ፡ ጋር ፡ ይሁን፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ፡

ሁለተኛ ፡ ተአምር ።

ልመናውና ፡ በረከቱ ፡ ከአገ ልጋዩ ፡ ጋር ፡ ይሁንና ፡ የመ ላእክት ፡ አለቃ ፡ የሚሆን ፡ የቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ተአምር ፡ ይህ ፡ ነው ።

፩ እመቤታችንን ፡ ከልቡ ፡ የሚያገለግልና ፡ እግዚአብሔርን ፡

ፈርሆ ፡ **ለእግዚአብሔር** ፡ ወይትለአካ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ በኵሉ ፡ ልቡ ።

፪ ፤ **ወዘልፈ ፡ ይስእል ፡** ወይጼሊ ፡ ኀቤሃ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ኢታርእየኒ ፡ ሙስናሃ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ወበእንተ ፡ ሕዝባ ፡ ወበእንተ ፡ ጽሌሃ ፡ **ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ።**

፫ ፤ **ወእሐተ ፡ ዕለተ ፡** እምድኅረ ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕል ፡ በበዓለ ፡ ዕረፍታ ፡ **ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡** ሖረ ፡ ለቀዲሐ ፡ ማይ ፡ ወለሰቢረ ፡ ዕፅ ፡ ብሔረ ፡ ርኁቀ ።

፬ ፤ **ወበጺሖ ፡ ውስተ ፡ ቀላየ ፡** ማይ ፡ ቀድሐ ፡ ውእተ ፡ ማየ ፡ ከመ ፡ ይትኀፀብ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ ወኃሊፎ ፡ እምህየ ፡ ሕቀ ፡ እንዘ ፡ ይትሐፀብ ፡ ረከበ ፡ ቆጽለ ፡ በለስ ፡ ከዊኖ ፡ ውዱቀ ፡ እምሥረዊሁ ፡ ለዖም ፡ ወሶቤሃ ፡ ከደኖ ፡ በቆጽለ ፡ በለስ ፡ ውእተ ፡ ማየ ፡ ዘኮነ ፡ በቀሱት ።

፭ ፤ **ወእምዝ ፡ ነሢኦ ፡** ውእተ ፡ ቀሱተ ፡ ዘማይ፡ እንዘ፡ይትመየጥ ፡ ውስተ ፡ ብሔሩ ፡ ሰምዓ ፡ በውስተ ፡ ፍኖት ፡ ድምፀ ፡ ዖፍ ፡ ወቆመ፡በጊዜሃ ፡ ባሮክ ፡ አንጸረ ፡ ገጸ ፡ ለዖፍ ።

፮ ፤ **ወትቤ ፡ ባሮክ ፡ ባሮክ ፡** ተመየጥ ፡ ኀበ ፡ ሀገርከ ፡ ከመ ፡ ትርአይ ፡ ስብሐተ ፡ **እግዚአብሔር ፡** ወንገሥታተ ፡ ኵሉ፡ ዓለም፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ ተፋጸየት ፡በቃላ ።

የሚወድ ፡ ባርክ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ዲያቆን ፡ ነበረ ።

፪ ፤ **እሱም ፡ ሁል ፡ ጊዜ** የኢየሩሳሌምንና ፡ የሕዝቧን ፡ **የእመቤታችንንም** ፡የጽላቷን ፡ ጥፋት ፡ አታሳይኝ ፡ እያለ ፡ ይጸልይ ፡ ነበር ።

፫ ፤ **በዚህ ፡ ጸሎት ፡** ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ከዕለታት ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ **በእመቤታችን ፡** በዕረፍቷ ፡ በዓል ፡ ውኃ ፡ ሊቀዳና ፡ ዕንጨት ፡ ሊሰብር ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ሄደ ።

፬ ፤ **ከወንዙ ፡ ደረሰና ፡** ውኃውን ፡ ቀድቶ ፡ጥቂት፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ እጅና ፡ እግሩን ፡ ሲታጠብ ፡ ከበለሱ ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ የበለስ ፡ ቅጠል ፡ ወድቆ ፡ አገኘና ፡ በበለሱ ፡ ቅጠል ፡ ያን ፡ በእንስራ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ውኃ፡ ከደነው ፡ ወይም ፡ ሸፈነው ።

፭ ፤ **ከዚህ ፡ በኋላ ፡** በእንሥራው ፡ ያለውን ፡ ውኃ ፡ ይዞ ፡ ወደሀገሩ ፡ ሲመለስ ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ የወፍ ፡ ድምፅ ፡ ሰማና ፡ በወፏ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ቆመ ።

፮ ፤ **ወፏም ፡ በቃሏ ፡** አፏጨችና ፡ ባሮክ ፡ ባሮክ ፡ **የእግዚአብሔርን ፡** ምስጋናና ፡ የዓለ ምን ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ሁኔታ ፡ ትመለከት ፡ ዘንድ ፡ ወደሀገርህ ፡ ተመለስ ፡ አለችው ።



፯ ፤ **ተመሲላ ፡ በአምሳለ ፡** ዖፍ ፡ **እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡** ገሃደ ፡ አስተርአየቶ ፡ አንጸረ ፡ ምዕራቢሃ ፡ ለፀሐይ ።

፰ ፤ **ወሶቤሃ ፡ ተፈትሒት ፡** ነፍሱ ፡ ለባሮክ ፡ ወይቤ ፡ ከመ ፡ ፋጻ ፡ ቀጢን ፡ ወከመ ፡ መሰንቆ ፡ ሐዋዝ ፡ ያስተፌሥሐኒ ፡ ልብየ ፡ በሰሚዖቱ ፡ ዘትቤ ፡ መርዓት ፡ በአፈ ፡ ሰሎሞን ።

፱ ፤ **ወዳግመ ፡ ጸውዓቶ ፡** በነገረ ፡ መላእክት ፡ በአፉሃ ፡ ይእቲ ፡ ዖፍ ፡ ለባሮክ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ አ ፡ ላእክየ ፡ ተመየጥ ፡ ኀቤየ ፡ ከመ ፡ ትስማዕ ።

፲ ፤ **ውእቲኒ ፡ ተመይጠ** ሶቤሃ ፡ መንገለ ፡ ሀለወት ፡ ይእቲ፡ ዖፍ ፡ ወሰምዓ ፡ ድምፀ ፡ ዚአሃ ፡ ዘትቤሎ ፡ ወይቤ ፡ አደመኒ ፡ ድምፀ ፡ ዚአሃ ፡ ለዖፍ ።

፲፩ ፤ **ወሶቤሃ ፡ ከብዳ ፡** አዕይንቲሁ ፡ በንዋም ፡ ወተግሂሦ ፡ እምፍኖት ፡ ሕቀ ፡ ሰከበ ፡ ከመ ፡ እንበሳ ፡ ወነምር ፡ ወነበረ ፡ ውስቴታ ፡ ለገዳም ፡ ተተርኢሶ ፡ እደዊሁ ፡ ላዕለ ፡ ውእቱ ፡ ቀሱት ፡ ዘማይ ።

፯ ፤ **በዖፍ ፡ አምሳል ፡** ተመስላ ፡ እመቤታችን ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ በፀሐይ ፡ መውጫ ፡ በኩል ፡ በግልጥ ፡ ታየችው ።

፰ ፤ **ያን ፡ ጊዜ ፡ ባሮክ ፡** ሰውነቱ ፡ ነፍሷን ፡ ወደማወቅ ፡ ተመለሰችና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ሰሎሞን ፡ ስለሙሽራ ፡ ደስታ ፡ በምሳሌ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ልቤ ፡ ድምፅዋን ፡ በመስማቱ ፡ የበገናና ፡ የመሰንቆ ፡ ድምፅ ፡ ደስ ፡ እንደሚያሰኝ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ፡ አለ ።

፱ ፤ **ዳግመኛም ፡ ያቺ ፡ ወፍ ፡** በመላእክት ፡ ቋንቋ ፡ አገልጋዬ ፡ ባሮክ ፡ ሆይ ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ ወደኔ ፡ ተመለስ ፡ እያለች ፡ ጠራችው ።

፲ ፤ **ያን ፡ ጊዜ ፡ እሱም ፡ ወፏ** ወዳለችበት ፡ ቦታ ፡ ተመለሰና ፡ ወፏ ፡ የምትለውን ፡ ድምፅ ፡ ሰምቶ ፡ ድምጿ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አሰኘኝ ፡ አለ ።

፲፩ ፤ **ያን ፡ ጊዜ ፡ ዓይኖቹ** በዕንቅልፍ ፡ አሸለቡና ፡ ከጐዳናው ፡ ጥቂት ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ አንበሳና ፡ እንደ ፡ ነምር ፡ በውኃ ፡ እንስራው ፡ ላይ ፡ በእጁ ፡ ተንተርሶ ፡ ተኛ ።

፲፪ ፤ ወይቤ ፡ እምድኅረ ፡ ኖምኩ
መሰጠኒ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በእደ፡
ዑራኤል ፡ መልአክ ፤ ወአዕረገኒ
ሰማያተ ።

፲፫ ፤ ወይቤለኒ ፡ ዑራኤል ፡
መልአክ ፡ ጽናዕ ፡ ወተዓገሥ ፡
እመ ፡ ይቤለኒ ፡ ሶቤሃ ፡ ጸናዕኩ ፡
ወተዓገሥኩ ።

፲፬ ፤ ወአርአየኒ ፡ ብዙኃ ፡
ነገረ ፡ ዘኢይተረጎም ፡ ዘነገሥት ፡
ወመኳንንት ፡ ዘእድ ፡ ወዘአንስት ፡
ዘመዘምራን ፡ ዘመነኮሳት ፡ ወዘ
አዕዋፍ ።

፲፭ ፤ ወወሰደኒ ፡ ወአብጽሐኒ ፡
ኀበ ፡ ነጋሢ ፡ አንበሳ ፡ ወነጸ
ርክዎ ፡ እንዘ ፡ ይጠብሕ ፡ መጥ
ብሐ ፡ ዘእንስሳ ፡ ወዘአልህምት ፡
ዘአልቦሙ ፡ ጽጋብ ፡ መጠነ ፡
ብዝኃ ፡ ረኃበ ፡ ከርሦሙ ።

፲፮ ፤ አሜሃ ፡ ሐተትክዎ ፡
ከመ ፡ ይንግረኒ ፡ ከዊኖቶ ፡ በዘ
ኢይደልወኒ ፡ ሐቲቶት ።

፲፯ ፤ ወይቤለኒ ፡ እስኩ ፡ ጽን
ሐኒ ፡ ንስቲተ ፡ እስከ ፡ ይከ
ሥት ፡ ሊተ ፡ እግዚአብሔር ፡
ዘፀሐይ ፡ ወወርኅ ።

፲፰ ፤ ወጸኒሐ ፡ ጥቀ ፡ አይድ
ዓኒ ፡ ናሁ ፡ ዝንቱ ፡ አንበሳ ፡
ዘይነግሥ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ምድር ፡
ዘአልቦ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ፍትሕ ፡

፲፪ ፤ ከተኛሁም ፡ በኋላ ፡ በመ
ልአኩ ፡ በዑራኤል ፡ እጅ ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነጥቆ ፡ ወደ ፡
ሰማይ ፡ አወጣኝ ፡ አለ ።

፲፫ ፤ ከዚያም ፡ መልአኩ ፡
ዑራኤል ፡ ጠንክር ፡ ታገሥ ፡
ባለኝ ፡ ጊዜ ፡ ታገሥሁ ፡ ጠነከ
ርሁም ።

፲፬ ፤ ሊተረጎም ፡ የማይቻል ፡
የነገሥታትንና ፡ የመ ኳንንትን ፡
የወንዶችንና ፡ የሴቶችን ፡ የመ
ዘምራንና ፡ የመምህራንን ፡ የመ
ነኩሳትንና ፡ የወፎችን ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ አሳየኝ ።

፲፭ ፤ ንጉሥ ፡ ከሚሆን ፡ ከአ
ንበሳው ፡ ዘንድ ፡ ወስዶ ፡ አደ
ረሰኝ ፡ እሱም ፡ ከሆዳቸው ፡
መራብ ፡ የተነሣ ፡ ውፍረት ፡
የሌላቸውን ፡ እንስሳዎችንና ፡ ላሞ
ችን ፡ ሲያርድ ፡ ሲያወራርድ ፡
አየሁት ።

፲፮ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ስፍራ ፡ ስን
ቀጠቀጥ ፡ ሁኔታውን ፡ ይነግ
ረኝ ፡ ዘንድ ፡ በማይገባኝ ፡ ምር
መራ ፡ መረመርሁት ።

፲፯ ፤ እግዚአብሔር ፡ የፀሐይ
ንና ፡ የጨረቃን ፡ ነገር ፡ እስኪ
ገልጽልኝ ፡ ድረስ ፡ ትንሽ ፡ቆየኝ ፡
አለኝ ።

፲፰ ፤ ትንሽ ፡ ቆይቶ ፡ እነሆ ፡
ይህ ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የሚ
ነግሠው ፡ አንበሳ ፡ በዘመኑ ፡
ፍትሕና ፡ እውነት ፡ የጽድቅም ፡



ወርትዕ ፡ ወመሥዋዕት ፡ ዘጽ
ድቅ ።

፲፱ ፤ ወካዕበ ፡ አብጽሐኒ ፡
ወወሰደኒ ፡ ኀበ ፡ መስተገብረ ፡
ምድር ፡ ዓቢይ ፡ ወረከብኩ ፡
በህየ ፡ ግብረ ፡ አጋዕዝቲሁ ፡ እንዘ ፡
ይኴንን ፡ ወሉደ ፡ ነገሥት ፡ ወእ
ንዘ ፡ ይዘብጥ ፡ ደቀ ፡ ወአዋልደ፡
ወያስተጻብሕ ፡ ሎቱ ፡ ፲ተ ፡ ወ፪ተ ፡
ጽሕርታተ ፡ ደመ ፡ ትክቶ ፡ አን
ስት ።

፳ ፤ ወካልአ ፡ መንበረ ፡ ርኢኩ ፡
ወኢረከብኩ ፡ በውስቴቱ ፡ ዘእ
ንበለ ፡ አሐቲ ፡ ብእሲት ፡ ወሶ
ቤሃ ፡ ሐተትክዎ ፡ ወእቤሎ ፡
አይቴ ፡ ሀለዉ ፡ ነገሥታት ፡ ወዓ
በይት ፡ መኳንንት ፡ አውሥአ ፡
ወይቤለኒ ፡ በአድልዎ ፡ ፍትሕ ፡
ወበአሕጽጾ ፡ ፍቅር ፡ ተኃጕሉኬ ፡
ትካት ።

፳፩ ፤ ወካዕበ ፡ አርአየኒ ፡ መቅ
ደሰ ፡ ዓቢየ ፡ ኀበ ፡ ነበሩ ፡ ቦቱ ፡
ቀዳሚ ፡ መምህራን ፡ ክቡራን ፡
ወሊቃውንተ ፡ ሕዝብ ፡ እለ ፡
ይሠርዑ ፡ ወይበይኑ ፡ ዘብሉይ ፡
ወዘሐዲስ ፡ ወእለ ፡ ይሜህሩ ፡
መጻሕፍተ ፡ ወብዙኃን ፡ ተሠሪ
ዖሙ ፡ በበገጾሙ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡
ገጸ ፡ መካን ።

፳፪ ፤ ወሶቤሃ ፡ አውማእክዎ ፡
እንዘ ፡ እብል ፡ አይቴ ፡ ሀለዉ ፡
ይእዜ ፡ እልክቱ ፡ መምህራን ፡
ፈካርያነ ፡ መጻሕፍት ፡ ዘነበሩ ፡
ኀበዝ ፡ ቀዲሙ ።

መሥዋዕት ፡ የለም ፡ ሲል ፡ ነገ
ረኝ ።

፲፱ ፤ ዳግመኛም ፡ ወስዶ ፡ ከት
ልቁ ፡ ገበሬ ፡ ዘንድ ፡ አደረሰኝ ፡
ከዚያም ፡ የጌቶቹ ፡ ባሪያ ፡ የነገ
ሥታቱን ፡ ልጆች ፡ ሲቆጣና ፡
ሴቶችንና ፡ ወንዶች ፡ ልጆቹንም ፡
ሲደበድብና ፡ የሴቶች ፡ የወር ፡
ግዳጃቸውን ፡ በዓሥራ ፡ ሁለት ፡
ጋኖች ፡ ሞልቶ ፡ እንደ ፡ ወጥ ፡
ሲያስጠቅስ ፡ አየሁ ።

፳ ፤ ሁለተኛም ፡ ዙፋን ፡ አየሁ ፡
ባጠገቡ ፡ ግን ፡ ያለአንዲት ፡
ሴት ፡ ሌላ ፡ የለም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡
ነገሥታቱና ፡ ታላላቆቹ ፡ መኳ
ንንት ፡ ወዴት ፡ አሉ ፡ ብዬ ፡
ብጠይቀው ፡ ፍትሕን ፡ በማጓ
ደል ፡ ፍቅርን ፡ በማጥፋት ፡ ተፈ
ርዶባቸው ፡ እነሆ ፡ አስቀድሞ ፡
ጠፍተዋል ፡ አለኝ ።

፳፩ ፤ በየደንባቸው ፡ ተመድ
በው ፡ በየቦታው ፡ ሁሉ ፡
የብሉይና ፡ የሐዲስን ፡ ሥርዓት ፡
ያደላደሉ ፡ የሕዝብ ፡ ሊቃውንትና ፡
መጻሕፍትን ፡ የሚያስተምሩ ፡
ክቡራን ፡ መምህራን ፡ አስቀ
ድሞ ፡ የነበሩበትን ፡ ከፍተኛና ፡
ታላቅ ፡ መቅደስ ፡ አሳየኝ ።

፳፪ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡
ከዚህ ፡ ቦታ ፡ የነበሩት ፡ መጻሕ
ፍትን ፡ የሚተረጕሙ ፡ ሊቃው
ንት ፡ ዛሬ ፡ ወዴት ፡ አሉ? ስል
ጠየቅሁት ።

፳፫ ፤ **አውሥአኒ ፡ ወይቤለኒ ፡** በበሊዓ ፡ ንዋየ ፡ ዓመፃ ፡ ወበነሢአ ፡ ዓሥራት ፡ እሉኬ ፡ አቅደሙ ፡ ተኃጉሎ ፡ ውስተ ፡ሲኦል ።

፳፬ ፤ **ወእምዝ ፡ ወሰደኒ ፡** ወአብጽሐኒ ፡ ኀበ ፡ ገዳመ ፡ መንኰሳት ፡ ወበህየ ፡ ረከብኩ ፡ ቆብዓ ፡ ወአስኬማ ፡ ብዙኃ ፡ ዘኢይበቍዖሙ ፡ ወዘኢኮኑ ፡ መድኃኒተ ፡ ነፍሶሙ ።

፳፭ ፤ **ወሶቤሃ ፡ ተሰአልክዎ ፡** እንዘ ፡ እብል ፡ በፍርሃት ፡ አይቴ ፡ ነገዱ ፡ መንኰሳት ፡ መፍቀርያነ ፡ ጾም ፡ ወጸሎት ፡ ወተሐራምያነ ፡ እክል ።

፳፮ ፤ **ውእቱኒ ፡ በመዓት ፡** ወይቤለኒ ፡ ኢታረምምኑ ፡ ኢሰማዕከኑ ወኢለበውከኑ? ከመ ፡ እሉ ፡ ወረዱ ፡ ሕያዋኒሆሙ ፡ ቆላተ ፡ ደይን ፡ በብካይ ፡ ወሐቅየ ፡ ሰነን ፡ በኢያጥርዮ ፡ ንጽሐ ፡ ሥጋሆሙ ፡ እስመ ፡ ክነፊሆሙ ፡ ቅዱስ ፡ ተሰብረ ፡ በርስሐተ ፡ ዓለም ፡ ጥቀ ።

፳፯ ፤**ወእምዝ ፡ ፀበበኒ ፡** ግእዙ ፡ ለሰብእ ፡ ከዊኖ ፡ ንጹሐ ፡ ወተመሲሎ ፡ ጻድቀ ፡ እንዘ ፡ ሥለንታሁ ፡ ኃጥእ ፡ ዝኩ ፡ የዓፅብ ፡ በኀበ ፡ ሰብእ ፡ ወመላእክት ።

፳፫ ፤ **መማለጃን ፡ በመቀበልና ፡** የዓመፅን ፡ ገንዘብ ፡ ማለት ጉቦን በመብላት ፡ እነሆ ፡ አስቀድመው ፡ ወደሲኦል ፡ ሂደው ፡ ጠፍተዋል ።

፳፬ ፤ **ከዚህ ፡ በኋላ ፡** ወደ ፡ መነኰሳት ፡ ገዳም ፡ ወስዶ ፡ አደረሰኝ ፡ ከዚያም ፡ ለነፍሳቸው ፡ መድኃኒት ፡ የማይሆንና ፡ የማይጠቅማቸው ፡ አስኬማና ፡ ቆብ ፡ አገኘሁ ።

፳፭ ፤ **ያን ፡ ጊዜ ፡ እየፈራሁ ፡** እህልን ፡ ባለመብላት ፡ ጸሎትና ፡ ጾምን ፡ ብቻ ፡ የሚወዱ ፡ መነኰሳት ወዴት ሄዱ ስል ጠየቅሁት ።

፳፮ ፤ **እሱም ፡ በቁጣ ፡ መንፈስ ፡** በል ፡ እንጂ ፡ ዝም ፡ በል ፡ ብሎ ፡ እነሱማ ፡ ንጽሕናን ፡ ገንዘብ ፡ ባለማድረጋቸው ፡ ቅዱስ ፡ የሆነ ፡ የጸጋቸው ፡ ክንፍ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ጉስቁልና ፡ ፈጽሞ ፡ ስለተሰበረ ፡ ብዙ ፡ ሥቃይና ፡ ለቅሶ ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ወዳለበት ፡ በሕይወታቸው ፡ ወደ ሲኦል ፡ ጉድጓድ ፡ እንደገቡ ፡ አልሰማህምን ? አላስተዋልክምን ሲል ፡ መለሰልኝ ።

፳፯ ፤ **ከዚህ ፡ በኋላ ፡** የሰው ፡ ጠባይ ፡ ንጹሕ ፡ ጻድቅ ፡ መስሎ ፡ ሁለንተናው ፡ ኃጥእ ፡ ወይም ፡ በደለኛ ፡ በመሆኑ ፡ አስጨነቀኝ ፡ ይህም ፡ በሰውና ፡ በመላእክት ፡ ዘንድ ፡ አስጨናቂ ፡ ነገር ፡ ነው ።



፳፰ ፤ **ወሶቤሃ ፡ እምዘአርአየኒ** በሑረተ ፡ ዓይነ ፡ ኀሊና ፡ ወበጸሊወ ፡ እዝነ ፡ እንዘ ፡ አነክር ፡ ግብሮ ፡ **ለእግዚአብሔር** ፡ ወአሜሃ ፡ ገሠጸኒ ፡ ውእቱ ፡ **መልአክ** ፡ ወይቤለኒ ፡ ዓዲ ፡ ትሬኢ ፡ እምዝ ፡ ዘየዓቢ ።

፳፱ ፤ **ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡** አዕረገኒ ፡ ውስተ ፡ ኖኅ ፡ ሰማይ ፡ ወአርአየኒ ፡ ሀገረ ፡ ብርሀተ ፡ እንተ ፡ ተሐቱ ፡ እምብርሃነ ፡ ፀሐይ ፡ ፯ተ ፡ እደ ፡ ወውሡቅ ፡ በነድ ፡ አቅማሪሃ ፡ አልቦ ፡ ዘቦአ ፡ ውስቴታ ፡ ለዛቲ ፡ ሀገር ።

፴ ፤ **ወአሜሃ ፡ ሐተትክዎ ፡** እንዘ ፡ እብል ፡ እለ ፡ መኑ ፡ ይበውእዋ ፡ ለዛቲ ፡ ሀገር ፡ ሠናይት ፡ ወብርህት ፡ ጥቀ ።

፴፩ ፤ **ወአውሥአ ፡ ወይቤለኒ ፡** ደናግል ፡ ዘኢየአምራ ፡ ብእሴ ፡ በትድምርተ ፡ ሥጋ ፡ ወሕፃናትኒ ፡ ይበውኡ ፡ ኀቤሃ ፡ ዕቤራትኒ ፡ እለ ፡ ሞታ ፡ በንስሐ ።

፴፪ ፤ **ወዓዲ ፡ ኃዲጎሙ ፡** ብሔሮሙ ፡ ወአዝማዲሆሙ ፡ በከዊነ ፡ ፈላሲ ፡ ወነግድ ፡ ወእለ ፡ ሞቱ ፡ በብሔረ ፡ ካልአን ፡ ወባዕዳን ፡ ሰብእ ፡ ወእለሂ ፡ ተቀትሉ ፡ በደመ ፡ ሰምዕ ፡ ወሶቤሃ ፡ ተፈሥሐት ፡ ነፍስየ ።

፳፰ ፤ **ያን ፡ ጊዜ ፡ መልአኩ ፡** ካሳየኝ ፡ ነገር ፡ የተነሣ ፡ ዓይነ ፡ ኅሊናየን ፡ በተመስጦ ፡ ሸፍኜ ፡ እዝነ ፡ ልቡናዬን ፡ በአንክሮ ፡ ከድኜ ፡ **የእግዚአብሔርን ፡** ሥራ ፡ ሳደንቅ ፡ ወዲያው ፡ **መልአኩ ፡** ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ገና ፡ ታያለህ ፡ ሲል ፡ አሳሰበኝ ።

፳፱ ፤ **ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደሰማይ ፡** አውጥቶ ፡ ከፀሐይ ፡ ሰባት ፡ እጅ ፡ የምታበራ ፡ ብርህት ፡ የሆነች ፡ አገር ፡ አሳየኝ ፡ ዙሪያዋም ፡ በእሳት ፡ የታጠረ ፡ በውስጧ ፡ ማንም ፡ ያልገባባት ፡ ነች ።

፴ ፤ **ያን ፡ ጊዜ ፡ ከዚች ፡ እጅግ ፡** የምታምር ፡ ብርህት ፡ ከሆነችው ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የሚገቡ ፡ እነማን ፡ ናቸው ፡ ብየ ፡ ጠየቅሁት ።

፴፩ ፤ **እሱም ፡ ከወንድ ፡ ጋር ፡** የሥጋ ፡ ግንኙትን ፡ የማያውቁ ፡ ደናግል ፡ ሴቶችና ፡ ወንዶች ፡ ሕፃናት ፡ እንዲሁም ፡ ንስሐ ፡ የገቡ ፡ ባልቴቶች ፡ ይገቡባታል ፡ ሲል ፡ መለሰልኝ ።

፴፪ ፤ **ዳግመኛም ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡** ፍቅር ፡ አገራቸውንና ፡ ዘመዶቻቸውን ፡ ትተው ፡ ወይም ፡ ስደተኛ ፡ መጻተኛ ፡ ሁነው ፡ በሰው ፡ ሀገር ፡ የሞቱና ፡ በሰማዕትነትም ፡ ደማቸውን ፡ ያፈሰሱ ፡ ሁሉ ፡ ይገቡባታል ፡ ስላለኝ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ነፍሴ ፡ ደስ ፡ አላት ።

፴፫ ፤ ወዓዲ ፡ ወሰደኒ ፡ ኀበ ፡ ሀለዉ ፡ ጳጳሳት ፡ ወኤጲስቆጶሳት ፡ ወሥዩማነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወርኢክዎሙ ፡ ወሪዶሙ ፡ መትሕተ ፡ ሲኦል ፡ አምጣነ ፡ ክብረ ፡ ስሞሙ ፡ በዲበ ፡ ምድር ።

፴፬ ፤ ወአሚሃ ፡ እንሰኬ ፡ ሐለይክዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ነገር ፡ በልብየ ፡ እስከ ፡ አስእን ፡ ተናግሮ ፡ ወአንከርኩ ፡ ተፈጥሮቶ ፡ ለሰብእ ፡ ወእቤ ፡ እምኄሶ ፡ ለሰብእ ፡ እመኢተፈጥረ ፡ እንዘ ፡ እብል ።

፴፭ ፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ይቤለኒ ፡ ዑራኤል ፡ መልአክ ፡ ተንሥእ ፡ እምንዋምከ ፡ ወሶቤሃ ፡ ተንሣእኩ ፡ ወነቃሕኩ ፡ እምንዋምየ ፡ በሰብዓ ፡ ዓመት ።

፴፮ ፤ ወሶበ ፡ ተንሣእኩ ፡ እምንዋምየ ፡ ተጽዕቀት ፡ ነፍስየ ፡ በይነ ፡ ዘርኢኩ ፡ ዘንተ ፡ ራእየ ፡ ጸበበተኒ ፡ ምድር ፡ እንተ ፡ ቆምኩ ፡ ባቲ ፡ ወእቤ ፡ እሌ ፡ ሊተ ፡ ወይ ሊተ ፡ እንዘ ፡ እብል ፡ በከይኩ ፡ ወአስቆቀውኩ ፡ ብዙኃ ።

፴፯ ፤ ወዘንተ ፡ ራእየ ፡ ርኢኩ ፡ አነ ፡ ዲያቆናዊ ፡ ባሮክ ፡ እቤለክሙ ፡ አኃውየ ።

፴፰ ፤ ወረከብክዋ ፡ ለቆጽለ ፡ በለስ ፡ እንዘ ፡ ኢይጸመልሉ ፡ ልምላሜያቲሃ ፡ ወሶቤሃ ፡ እንዘ ፡ እትፌሣሕ ፡ ወእትሐሠይ ፡ ወእሴብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወለቅዱስ ፡ ዑራ

፴፫ ፤ እንደገና ፡ ደግሞ ፡ ጳጳሳትና ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሹማምንት ፡ ካሉበት ወሰደኝና ፡ ስማቸው ፡ በምድር ፡ የተከበረ ፡ ቢሆንም ፡ ወደ ሲኦል ፡ ወርደው ፡ አየኋቸው ።

፴፬ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ መናገር ፡ እስኪሳነኝ ፡ ድረስ ፡ ይህንን ፡ በልቤ ፡ አሰብሁና ፡ ሰው ፡ ባል ተፈጠረ ፡ በተሻለው ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ የሰውን ፡ ተፈጥሮ ፡ አደነቅሁ ።

፴፭ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መልአኩ ፡ ዑራኤል ፡ ከዕንቅልፍህ ፡ ተነሥ አለኝና ፡ ወደዚያው ፡ ከዕንቅልፌ ፡ በሰብዓ ፡ ዓመት ፡ ነቃሁ ።

፴፮ ፤ ከዕንቅልፌ ፡ በነቃሁ ፡ ጊዜ ፡ ስላየሁት ፡ ራእይ ፡ ሁኔታ ፡ ነፍሴ ፡ ወይም ፡ ሰውነቴ ፡ ተጨነቀችና ፡ የቆምሁባት ፡ ምድር ፡ ጠበበችኝ ፡ ወይኔ ፡ ወዮልኝ ፡ እያልሁም ፡ ብዙውን ፡ አለቀስሁ ።

፴፯ ፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ዲያቆን ፡ የምሆን ፡ እኔ ፡ ባሮክ ፡ ይህንን ፡ ራእይ ፡ አየሁ ።

፴፰ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ የበለሷን ፡ ቅጠል ፡ ከልምላሜዋ ፡ ሳትጠወልግ ፡ ስለ ፡ አገኘኋት ፡ በብዙ ፡ እየተደሰትሁና ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገንሁ ፡ የቅዱስ ፡ ዑራኤልንም ፡ ድንቅ ፡ የሆነው ፡ ሥራ



ኤልኒ ፡ እንዘ ፡ አነክር ፡ ግብሮ ፡ ወፍቅሮ ፡ ሖርኩ ፡ ውስተ ፡ ብሔርየ ፡ በሰላም ።

፴፱ ፤ ወእንበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ነገር ፡ ነበረ ፡ በንጽሕናሁ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞቱ ፡ እንዘ ፡ ያነክር ፡ ዘንተ ፡ ዕጹበ ፡ ግብረ ፡ ዘነጸሮ ፡ በተአምር ።

፵ ፤ ትንብልናሁ ፡ ወሀብተ ፡ ረድኤቱ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ የሃሉ ፡ ምስለ ፡ ገብሩ ፡ ................ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ውንና ፡ ፍቅሩን ፡ እያደነቅሁ ፡ ተመልሼ ፡ ወደሀገሬ ፡ በሰላም ፡ ገባሁ ።

፴፱ ፤ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ይህንን ፡ ያየውን ፡ ዕጹብ ፡ የሆነ ፡ ተአምር ፡ እያደነቀ ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ድረስ ፡ በንጽሕና ፡ ኖረ ።

፵ ፤ የቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ሀብተ ፡ ረድኤቱና ፡ አማላጅነቱ ፡ ከወዳጁ ፡ ከ ................ ጋር፡ ይሁን ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን ።

## ሣልስ ፡ ተአምር ።

ተአምሪሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ የሃሉ ፡ ምስለ ፡ ገብሩ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

፩ ፤ ወሀለወት ፡ አሐቲ ፡ ብእሲት ፡ ተንባላዊት ፡ በውስተ ፡ አሐቲ ፡ ሀገር ፡ ዘአልባቲ ፡ ውሉድ ፡ ዘኮነት ፡ መካነ ።

፪ ፤ ወይእቲ ፡ ትበኪ ፡ ወትቴክዝ ፡ ዘልፈ ፡ በእንተ ፡ ዘአልባቲ ፡ ውሉድ ።

፫ ፤ ወበዘከመዝ ፡ ግብር ፡ ነበረት ፡ ብዙኃ ፡ መዋዕለ ፡ እንዘ ፡ ተሐዝን ፡ ወትቴክዝ ፡ እንዘ ፡

## ሦስተኛ ፡ ተአምር ።

ልመናውና ፡ በረከቱ ፡ ለዘላዓለሙ ፡ ከወዳጁ ፡ ጋር ፡ ይሁንና ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ የሚሆን ፡ የቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ተአምር ፡ ይህ ፡ ነው ።

፩ ፤ በአንዲት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ልጅ ፡ የሌላትና ፡ ወይም ፡ መካን ፡ የሆነች ፡ አንዲት ፡ እስላም ፡ ሴት ፡ ነበረች ።

፪ ፤ እስዋም ፡ ልጅ ፡ ስለሌላት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እየተከዘች ፡ ታለቅስ ፡ ነበር ።

መልአኩ ፡ ዑራኤል ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደም ፡ በባ ረካት ፡ በደብረ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ወይም ፡ በደብረ ፡ ዳሞ ፡ ላይ ፡ በእመቤታችን ፡ በቅድስት ፡ ድን ግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠራ ።

፳፮ ፤ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በን ጉሡ ፡ በገብረ ፡ መስቀል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ መልአኩ ፡ ዑራ ኤል ፡ የአክሱምን ፡ ገበዝ ፡ ልጅ ፡ ያሬድን ፡ ጽዋዓ ፡ ልቡና ፡ አጠ ጣው ።

፳፯ ፤ እሱም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እየተመራ ፡ እንደ ፡ መላ እክት ፡ ዜማ ፡ ያለ ፡ የጣፈጠ ፡ ጸዋትወ ፡ ዜማን ፡ ደረሰ ፡ ።

፳፰ ፤ ያሬድም ፡ ወደደብረ ዳሞ ፡ ወጣና ፡ የገብረ ፡ መስቀ ልን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕንጻ ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ አመሰገናት ፤ የእውነት ፡ ነገሥት ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያንን ፡ በያክንትና ፡ በከርከ ዴን ፡ ዕንቍ ፡ ሠሯት ፡ ይህች ውም ፡ ለብርሃን ፡ ጌታ ፡ እናት ፡ የሥጋዋ ፡ ንጽሕና ፡ አምሳል ፡ ናት ፡ የሕንጻዋን ፡ ሥራ ፡ ማማር ፡ አይቼ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ዞርኋት ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበረ ፡ ዓለምን ፡ አሳልፎ ፡ የሚኖር ፡ ማደሪያ ፡ አድርጓታልና ፡ በክርስቲያን ፡ ፡ አንደበት ፡ በሰላም ፡ ለእርስዋ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይገባታል ።

፷፱ ፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ተንሥኡ ፡ ያሬድ ፡ ወገብረ ፡ መስቀል ፡ ከመ ፡ ይስአልዎ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ያምጽእ ፡ ሎሙ ፡ ነፍሳተ ፡ አባ ፡ ሕርያቆስ ፡ ወኤፍሬም ።

፸ ፤ ወሶበ ፡ ፈጸሙ ፡ ጸሎቶሙ ፡ አምጽአ ፡ ሎሙ ፡ አንሢኦ ፡ እምነ ፡ ምውታን ።

፸፩ ፤ ወተክሉ ፡ ሐይመተ ፡ ብርሃን ፡ ሠራዊተ ፡ ዑራኤል ፡ ሐራ ፡ ሰማያት ።

፸፪ ፤ ወመጽኡ ፡ ሶቤሃ ፡ አባ ፡ ሕርያቆስ ፡ ወአባ ፡ ኤፍሬም ፡ ወነገርዎ ፡ ውዳሴሃ ፡ ወቅዳሴሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ።

፸፫ ፤ ወውእቱኒ ፡ ያሬድ ፡ ዘመረ ፡ ላቲ ፡ በልሳነ ፡ ግእዝ ፡ ወበ፫ቱ ፡ ነገረ ፡ ዜማ ፡ አራራይ ፡ ወግእዝ ፡ ወዕዝል ፡ ዘያስተፌሥሕ ፡ ልበ ፡ ከመ ፡ ወይን ፡ ጥዑም ።

፸፬ ፤ ወእምዝ ፡ ተንሥኡ ፡ ከመ ፡ ይሑሩ ፡ አባ ፡ አረጋዊ ፡ ወገብረ ፡ መስቀል ፡ ወያሬድ ፡ ካህን ፡ ኀበ ፡ ሐነጽዋ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ አብርሃ ፡ ወአጽብሐ ፡ ፪ቱ ፡ ነገሥት ፡ ውስተ ፡ ደሴታቲሃ ፡ ለባሕረ ፡ ጻና ።

፸፭ ፤ ወሶበ ፡ በጽሑ ፡ ኀቤሃ ፡ እሙንቱ ፡ ወደሳ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡

፷፱ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያሬድና ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ አባ ፡ ሕርያቆስንና ፡ ኤፍሬምን ፡ ያመጣላቸው ፡ ዘንድ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤልን ፡ ሊለምኑት ፡ ተነሡ ።

፸ ፤ ጸሎታቸውን ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ከሙታን ፡ አሥነሥቶ ፡ አመጣላቸው ።

፸፩ ፤ ሰማያውያን ፡ ጭፍሮች ፡ የዑራኤል ፡ ሠራዊትም ፡ የብርሃን ፡ ድንኳን ፡ ተከሉ ።

፸፪ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ሕርያቆስና ፤ አባ ፡ ኤፍሬም ፡ መጡና ፡ የአምላክ ፡ እናት ፡ የእመቤታችንን ፡ የድንግል ፡ ማርያምን ፡ ውዳሴዋንና ፡ ቅዳሴዋን ፡ ነገሩት ።

፸፫ ፤ እሱም ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ እንደሚጣፍጥ ፡ እንደ ፡ ወይን ፡ ልብን ፡ ደስ ፡ በሚያሰኙ ፡ በሦስቱ ፡ ጸዋትወ ፡ ዜማዎች ፡ በአራራይና ፡ በግእዝ ፡ በዕዝል ፡ ዘመረላት ።

፸፬ ፤ ከዚያም ፡ አባ ፡ አረጋዊ ፡ ንጉሡ ፡ ገብረ ፡ መስቀልና ፡ ካህኑ ፡ ያሬድ ፡ አብርሃና ፡ አጽብሐ ፡ በጣና ፡ ደሴቶች ፡ ውስጥ ፡ በእመቤታችን ፡ በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ ወደ ፡ አሠሯት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመሄድ ፡ ተነሡ ።

፸፭ ፤ እነሱም ፡ ከዚያ ፡ ከደረሱ ፡ በኋላ ፡ ካህኑ ፡ ያሬድ ፡



ወዘመረ ፡ ላቲ ፡ ከመ ፡ ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ወደብረ ፡ ዳሞ ፡ ሠናየ ፡ መዝሙረ ፡ በጥዑም ፡ ዜማሁ ።

፸፮ ፤ ወእንዘ ፡ ሀለዉ ፡ ውስተ ፡ ደሴተ ፡ ባሕረ ፡ ጻና ፡ ወረደ ፡ እም ሰማይ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ መልአክ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ለአባ ፡ አረጋዊ ፡ ወለያሬድ ፡ ሑሩ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ በጌምድር ፡ ወበህየ ፡ አርእየክሙ ፡ ደብረ ፡ ንእስተ ፡ ዘዓተብክዋ ፡ በደመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ከመ ፡ ትሕንጹ ፡ ላዕሌሃ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በስማ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ።

፸፯ ፤ ወተንሥኡ ፡ ሶቤሃ ፡ እም ባሕረ ፡ ፃና ፡ ወሖሩ ፡ በጌምድር፡ ወበጽሑ ፡ ላዕለ ፡ መርህባ ፡ ለደብር ፡ ወወዓሉ ፡ እንዘ ፡ የኃሥሥዋ ፡ ወኃጥእዋ ፡ ለደብር ።

፸፰ ፤ ወእንዘ ፡ የኃሥሥዋ ፡ ሖሩ ፡ እንተ ፡ ምዕራቢሃ ፡ መንገለ ደቡብ ፡ ወበህየ ፡ ነቢሮሙ ፡ ርእይዋ ፡ በታሕቴሃ ።

፸፱ ፤ እስመ ፡ መስየ ፡ ፀሐይ፡ ውስተ ፡ ውእቱ ፡ ብሔር ፡ ወቤቱ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ በተልዮ ፡ ጽኑዕ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ኀበ ፡ ሀለዉ ፡ መካን ።

፹ ወእንዘ ፡ ይጼሊ ፡ አባ ፡ አረጋዊ ወይቤ ፡ እመ ፡ እረክቦ ፡

በጥዑም ፡ ዜማው ፡ ደብረ ፡ ጽዮንና ፡ ደብረ ፡ ዳሞን ፡ በመልካም ፡ መዝሙር ፡ እንዳመሰገነ ፡ አመስገናት ፡ ወይም ፡ ዘመረላት ።

፸፮ ፤ በባሕረ ፡ ጣና ፡ ደሴት ፡ ውስጥ ፡ ሳሉ ፡ መልአኩ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ከሰማይ ፡ ወረደና ፡ አባ ፡ አረጋዊንና ፡ ያሬድን ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ ሂዱ ፡ ከዚያ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ ደም ፡ የባረክኋት ፡ የማሳያችሁ ፡ አነስተኛ ፡ ተራራ ፡ አለችና ፡ በርስዋ ፡ ላይ ፡ አምላክን ፡ በወለደች ፡ በእመቤታችን ፡ በድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥሩ ፡ አላቸው ።

፸፯ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከባሕረ ፡ ጣና ፡ ተነሥተው ፡ ወደበጌምድር ፡ ሄደው ፡ በተራራዋ ፡ አካባቢ ፡ ደረሱ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ተራራዋን ፡ ለማግኘት ፡ ባለመቻላቸው ፡ በመፈለግ ፡ ዋሉ ።

፸፰ ፤ እየፈለጓት ፡ ሲሄዱ ፡ ለተራራዋ ፡ ምዕራቧ ፡ የሚሆን ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ተቀምጠው ፡ ሳለ ፡ ወደታች ፡ ተመለከቷት ።

፸፱ ፤ ጊዜው ፡ መሽቶ ፡ ነበርና ፡ በዚያው ፡ ባሉበት ፡ ቦታ፡ ላይ ፡ በጽኑዕ ፡ ሐሳብ ፡ አደሩ ።

፹ ፤ አባ ፡ አረጋዊም ፡ ቀድሞ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዳሞ ፡ ያወጣኝ ፡

ለውእቱ ፡ አርዌ ፡ ዘአዕረገኒ ፡
መልዕልቴሃ ፡ ለደብረ ፡ ዳሞ ፡
ይእዜኒ ፡ እምአዕረገኒ ፡ ውስተ ፡
ዛቲ ፡ ደብር ።

፵፩ ፤ ወዘንተ ፡ ነገረ ፡ እንዘ፡
ይፌጽም ፡ ሶቤሃ ፡ ወረደ ፡ እም
ሰማይ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ መል
አክ ፡ ወመጽአ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ወይ
ቤሎ ፡ ለአባ ፡ አረጋዊ ፡ ዑድ ፡
መንገለ ፡ ምሥራቅ ፡ ዐውደ ፡
አባ ፡ ለዛቲ ፡ ደብር ፡ ከመ ፡ ትዕ
ርግ ፡ላዕሌሃ ፡ እስመ ፡ ዛቲ ፡ ይእቲ
ደብር ፡ ዘነገርኩክሙ ፡ ቅድመ፡
በባሕረ ፡ ደሴት ፡ ጣና ፡ እንዘ ፡
ሀሎክሙ ።

፵፪ ፤ ወረስያ ፡ ጽርሐ ፡ ለው
ሉድከ ፡ እስመ ፡ ረሰያ ፡ ለከ ፡
አምላክ ፡ ርስተ፡ ወለውሉድከ ፡
ዘትወልዶሙ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ
ከመ ፡ ሥርዓተ ፡ ወንጌሉ ፡ ለክ
ርስቶስ ፡ ዘይእቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ።

፵፫ ፤ ወገብረ ፡ አባ ፡ አረጋዊ
በከመ ፡ አዘዞ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል፡
መልአክ ።

፵፬ ፤ ወዓርገ ፡ ላዕሌሃ ፡ ለደ
ብር ፡ አባ ፡ አረጋዊ ፡ ወያሬድ ፡
ካህን ።

፵፭ ፤ ወበሣልስት ፡ ዕለት ፡
መጽአ ፡ ንጉሥ ፡ ገብረ ፡ መስ
ቀል ፡ ወተከለ ፡ ዲቤሃ ፡ ሐይ
መተ ፡ ሚላት ፡ ሠናይ ፡ ወተአየኑ፡

ዘንዶ ፡ ዛሬም ፡ በዚህ ፡ ቦታ ፡
ተገኝቶ ፡ ወደዚች ፡ ተራራ ፡ ላይ
ባወጣኝ ፡ እንዴት ፡ መልካም ፡
በሆነ ፡ ነበር ፡ እያለ ፡ ጸለየ ።

፵፩ ፤ ይህን ፡ ነገር ፡ ሲፈጽም ፡
ወዲያው ፡ መልአኩ ፡ ቅዱስ ፡
ዑራኤል ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡
ወደ ፡ እነርሱ ፡ መጣና ፡ አባ ፡
አረጋዊን ፡ ዞር ፡ አባ ፡ ወደ ፡
እርስዋም ፡ ትወጣ ፡ ዘንድ ፡ በም
ሥራቅ ፡ በኩል ፡ ተራራዋን ፡
ዞር ፡ አስቀድሜ ፡ በባሕረ ፡
ጣና ፡ ደሴት ፡ የነገርኋችሁ ፡
ተራራ ፡ ይህች ፡ ናትና ፡ አለው ።

፵፪ ፤ ለልጆችህ ፡ ማደሪያ ፡
አድርጋት ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡
ወንጌል ፡ ሥርዓት ፡ ይህችን ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ለምትወልዳቸው ፡ ልጆ
ችና ፡ ለአንተ ፡ ጭምር ፡ ርስት፡
አድርጎ ፡ ሰጥቷችኋልና ።

፵፫ ፤ አባ ፡ አረጋዊም ፡ መል
አኩ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ እንዳ
ዘዘው ፡ አደረገ ።

፵፬ ፤ አባ ፡ አረጋዊና ፡ ካህኑ ፡
ያሬድም ፡ ከተራራዋ ፡ ላይ ፡
ወጡ ።

፵፭ ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡
ንጉሡ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ መጣና
በተራራዋ ፡ ላይ ፡ የሐር ፡ ድን
ኳን ፡ ተከለ ፡ በተራራዋም ፡ ሥር
ወይም ፡ ከበታቿ ፡ የንጉሡ ፡



በታሕቴሃ ፡ ለደብር ፡ ሠራዊቱ፡
ወሠርዓ ፡ ቍርባነ ፡ አባ ፡ አረ
ጋዊ ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ሐይመተ
ሚላት ፡ ጸዓዳ ፡ ወመጠውዎ ፡
ሥጋሁ ፡ ወደሙ ፡ ለክርስቶስ ፡
ለገብረ ፡ መስቀል ፡ ንጉሥ ።

፵፮ ፤ ወበውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ከልሐ
ያሬድ ፡ ካህን ፡ በዝማሬ ፡ ቃሎሙ
ለሱራፌል ፡ ወኪሩቤል ፡ ካህናተ
ሰማይ ፡ አርያማዊት ፡ ወወደሶሙ
ለንጉሥ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡
ወለአባ ፡ አረጋዊ ፡ ጻድቅ ።

፵፯ ፤ ወበእንተዝ ፡ ተሰምየት ፡
ስማ ፡ ለይእቲ ፡ ደብር ፡ ጽርሐ ፡
አርያም ፡ ወዑድ ፡ አባ ፡ መካነ፡
ማርያም ፡ ቅድስት ።

፵፰ ፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡
ነበረ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ በዛቲ ፡
ደብር ፡ ሠለስተ ፡ ዓመተ ፡ እንዘ
ይሜህር ፡ ነገረ ፡ ዜማ ፡ ጥዑም ፡
ወገብረ ፡ መስቀል ፡ ነበረ ፡ እንዘ
ይገብር ፡ ሕንጼሃ ፡ ለቤተ ፡ ክር
ስቲያን ፡ በዲቤሃ ፡ ወአባ ፡ አረ
ጋዊኒ ፡ ኅቡረ ፡ ነበረ ፡ ምስሌ
ሆሙ ።

፵፱ ፤ ወእምዝ ፡ ተንሥአ ፡
ለሐዊር ፡ ሀገረ ፡ ትግራይ ፡ ወእ
ንዘ ፡ የሐውሩ ፡ ብሔረ ፡ አክሱም፡
በጽሑ ፡ ሀገረ ፡ ሰሜን ፡ ዘትሰ
መይ ፡ ደብረ ፡ ሐዊ ።

፶ ፤ ወበይእቲ ፡ ደብር ፡ ተሰ
ወረ ፡ ያሬድ ፡ እምዓይነ ፡ ሰብእ ፡
ወኮነ ፡ ንብረቱ ፡ ምስለ ፡ መላ
እክት ፡ ዘሰማይ ።

ሠራዊት ፡ ሠፈሩ ፡ ከዚያም ፡
አቡነ ፡ አረጋዊ ፡ በዚች ፡ ባማረች
የሐር ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ቍር
ባን ፡ ሠርቶ ፡ ለንጉሡ ፡ ለገብረ
መስቀል ፡ የክርስቶስን ፡ ሥጋ
ውና ፡ ደሙን ፡ አቀበለው ።

፵፮ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ካህኑ ፡ ያሬድ ፡
የሰማይ ፡ ካህናት ፡ በሚሆኑ ፡
በኪሩቤልና ፡ በሱራፌል ፡ ቃለ
ዝማሬ ፡ ንጉሡ ፡ ገብረ ፡ መስ
ቀልንና ፡ ጻድቁ ። አባ ፡ አረ
ጋዊን ፡ አመሰገናቸው ።

፵፯ ፤ ስለዚህም ፡ ይህች ፡ ደብር
ጽርሐ ፡ አርያምና ፡ ዞር ፡ አባ ፡
(ዞር፡አምባ) ቅድስት ፡ ማርያም ፡
ተብላ ፡ ተሰየመች ።

፵፰ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ካህኑ ፡
ያሬድ ፡ ጥዑም ፡ የሆነ ፡ የዜማን፡
ትምህርት ፡ እያስተማረና ፡ ገብረ
መስቀልም ፡ በዚችው ፡ ተራራ፡
ላይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እያሠራ
ሦስት ፡ ዓመት ፡ ተቀመጡ ።
አባ ፡ አረጋዊም ፡ ከነሱ ፡ ሳይ
ለይ ፡ አብሮ ፡ ነበር ።

፵፱ ፤ ከዚያም ፡ ወደትግራይ ፡
ማለት ፡ ወደ ፡ አክሱም ፡ ሲሄዱ
በሰሜን ፡ በኩል ፡ በምትገኝ ፡
ደብረ ፡ ሐዊ ፡ ከምትባል ፡ አገር፡
ደረሱ ።

፶ ፤ በዚችው ፡ ደብረ ፡ ሐዊ ፡
ከምትባል ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ደረሱ
ያሬድ ፡ ከሰው ፡ ዓይን ፡ ተሰወ
ረና ፡ አናናሩ ፡ ከሰማይ ፡ መላ
እክት ፡ ጋር ፡ ሆነ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ ፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ በሰመንቱ ፡ ትውልድ ፡ እመንግሥተ ፡ አብርሃ ፡ ወአጽብሐ ፡ በመንግሥተ ፡ ስድግዛን ፡ ንጉሥ ተኰለቍ ፡ ፪፻ ካህናት ፡ እምካህናተ ፡ አኵሱም ።

፪ ፤ ወዳግመ ፡ እምደሴተ ፡ ባሕረ ፡ ፃና ፡ ፩፻ ፡ ካህናት ፡ ወእምደብረ ፡ ጽርሐ ፡ አርያም ፡ ዘበጌምድር ፡ ፵ ፡ ካህናት ።

፫ ፤ ወእምሀገረ ፡ እምሐራኒ ፡ ዳውንት ፡ ወመቅደላ ፡ ወሳይንት ፡ ወምድረ ፡ ወለቃ ፡ ፩፻ወ፶ ካህናት ፡ ወምስለ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ አባ ፡ ይድላ ።

፬ ፤ በጽሑ ፡ ወሖሩ ፡ ሀገረ ፡ ሸዋ ፡ ወከፈሎሙ ፡ ኀበ ፡ ፫ቱ ፡ ክፍል ፡ ወአዘዞሙ ፡ ከመ ፡ ይምሐሩ ፡ ወንጌለ ፡ መለኮት ፡ ለኵሉ ብሔረ ፡ ሸዋ ፡ ወከፈሎሙ ፡ አሐደ ፡ ክፍለ ።

፭ ፤ ወቦኡ ፡ ሀገረ ፡ ዞረሬ ፡ ፪ወ፶ ፡ ካህናት ፡ ወሊቀ ፡ ካህናት፡ ኮነ ፡ ሊቆሙ ፡ አባ ፡ ይድላ ።

፮ ፤ ወ፩፪ ፡ ቦኡ ፡ ሀገረ ፡ ሰርማት ፡ ወሊቆሙ ፡ አባ ፡ ስብስትያ

## ሦስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ከአብርሃና ፡ ከአጽብሐ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ቀጥሎ ፡ ከስምንተኛ ፡ ትውልድ ፡ በኋላ ፡ በንጉሥ ፡ ስግድዛን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከአኵሱም ፡ ካህናት ፡ መካከል ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ካህናት ፡ ተመረጡ ።

፪ ፤ ዳግመኛም ፡ ከባሕረ ፡ ጣና ፡ ደሴት ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ካህናት ፡ እንዲሁም ፡ ከበጌምድር ፡ ጽርሐ ፡ አርያም ፡ ከምትባለው ፡ ደብር ፡ ፵ ፡ ካህናት ።

፫ ፤ ከአማራ ፡ አገርም ፡ ከዳውንትና ፡ ከመቅደላ ፡ ከሳይንትና ፡ ከወለቃ ፡ ምድር ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ካህናት ፡ ከሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ከአባ ፡ ይድላ ጋር ፡ ተመረጡ ።

፬ ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ክፍለ አገር ፡ ሄደው ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ በሦስት ፡ ክፍል ፡ ደለደላቸውና ፡ በዚሁ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ሁሉ ፡ የመለኮትን ፡ ወንጌል ፡ እንዲያስተምሩ ፡ አዘዛቸው ።

፭ ፤ አንድ ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ካህናት ፡ ምድረ ፡ ዞረሬ ፡ ገቡ ፡ አለቃቸውም ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ አባ፡ ይድላ ፡ ነው ።

፮ ፤ አንድ ፡ መቶ ፡ ካህናት ፡ ደግሞ ፡ ሰርማት ፡ በምትባል ፡ አገር ፡ ገቡ ፡ የነዚህም ፡ አለቃ



ኖስ ፡ ዘውእቱ ፡ ካልእ ፡ ስሙ ፡ አባ ፡ በግዑ ።

፯ ፤ ወቦኡ ፡ ካልአን ፡ ካህናት ፩፻ ፡ በሀገረ ፡ ተጕለት ፡ ዘትሰመይ ደርደሬ ።

፰ ፤ ወ፫ቱ ፡ ካህናት ፡ ቦኡ ፡ ሀገረ መንዝሀ ፡ ዘትሰመይ ፡ አጋንቻ ።

፱ ፤ ወእምዝ ፡ ተፈልጡ ፡ ፪ ፡ ካህናት ፡ ምስለ ፡ ወልደ ፡ ሊቆሙ ማቴዎስ ፡ ዘስሙ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ወወረዱ ፡ ምድረ ፡ ዊፋት፡ ዘትሰመይ ፡ ቀወት ፡ ዓጸዱ ፡ ለአሽማት ፡ ተንባላታዊ ።

፲ ፤ ወረሰይዎ ፡ ለዝንቱኒ ፡ ተንባላታዊ ፡ በገቢረ ፡ ተአምር ፡ ዓቢየ ፡ ክርስቲያናዌ ።

፲፩ ፤ ወነበሩ ፡ ውስቴታ ፡ ብዙኃ ፡ መዋዕለ ፡ እንዘ ፡ ይሜህሩ ፡ ወንጌለ ፡ መለኮት ፡

፲፪ ፤ ወእምዝ ፡ መርሆሙ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ መልአክ ፡ ለእሉ ፡ ካህናት ፡ ፬፻፡ ወ፯ ፡ ኀበ ፡ ዘቀደሶን ፡ በደሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አድባራት ፡ ኵሎን ፡ ወገብሩ ፡ እሙንቱኒ ፡ ካህናት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እንዘ ፡ ይሜህሩ ፡ ቃለ ፡ ወንጌሉ ፡ ለክርስቶስ ።

ቻቸው ፡ ሁለተኛው ፡ ስሙ ፡ አባ በግዑ ፡ የተባለ ፡ ስብስትያኖስ ፡ ነው ።

፯ ፤ አንድ ፡ መቶ ፡ የሚሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ካህናት ፡ በተጉለት ፡ ውስጥ ፡ ደርደሬ ፡ በምትባል ፡ ቦታ ፡ ተመደቡ ።

፰ ፤ ሦስቱ ፡ ካህናት ፡ ደግሞ ፡ በመንዝ ፡ ውስጥ ፡ አጋንቻ ፡ በምትባል ፡ ቦታ ፡ ተመደቡ ።

፱ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ስሙ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ የተባለ ፡ ከአለቃቸው ፡ ልጅ ፡ ከማቴዎስ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ የሚሆኑ ፡ ካህናት ፡ ተለይተው ፡ በይፋት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የእስላሙ ፡ የአሽማት ፡ ርስት ፡ ወደሆነችው ፡ ቀወት ፡ ተብላ ፡ ወደምትጠራው ቦታ ፡ ወረዱ ።

፲ ፤ እስላሙንም ፡ ተአምራት በመሥራት ፡ የታወቀ ፡ ታላቅ ፡ ክርስቲያን ፡ አደረጉት ።

፲፩ ፤ በዚችው ፡ አገር ፡ ውስጥ ወንጌልን ፡ እያስተማሩ ፡ ለብዙ ጊዜ ፡ ቆዩ ።

፲፪ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ዘጠናውን ፡ ካህናት ፡ መልአኩ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደም ወደባረካቸው ። አድባራት ፡ ሁሉ መራቸውና ፡ እነሱም ፡ የክርስቶስን ፡ ወንጌል ፡ እያስተማሩ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ ሠሩ ።

ጠዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ በንጹሕ ፡ ተክህኖ ።

፲፱ ፤ ወተወክፎ ፡ እምላክነ ፡ ከመ ፡ መሥዋዕተ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ወአብርሃም ።

፳ ፤ ወወሀበ ፡ ኪዳነ ፡ እንዘ ይብል ፡ ዘተመጠወ ፡ በይእቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቍርባነ ፡ ሥጋየ ፡ ወደምየ ፡ አኅድግ ፡ ሎቱ ኃጢአቶ ፡ ወይድኅን ፡ ዝንቱ ፡ እሞተ ፡ ሲኦል ፡ ግሩም ።

፳፩ ፤ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ መጽኡ ፡ ፭፻ ፡ መነኰሳት ፡ እምሀገረ ፡ ሮም ፡ ኅቢሆሙ ፡ ከመ ፡ ይንሥኡ ፡ ቍርባነ ፡ በእዴሆሙ ፡ ወተዘርዉ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ሀገረ ፡ ኢትዮጵያ ።

፳፪ ፤ ወነአኰቶ ፡ ለአብ ፡ ገብረ ፡ ከማሁ ፡ በሀገረ ፡ ሮሀ ፡ እምሥራቃ ፡ እስከ ፡ ምዕራባ ፡ ምድረ ብርሀት ፡ ዘትሜኒ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያነ ፡ ቅድስተ ።

፳፫ ፤ ወነግሡ ፡ በሀገረ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በጽድቅ ፡ ወበሰላም ፡ ወበፈሪሃ ፡እግዚአብሔር ፡ ቀዳሚ እለ ፡ ጸዋዕነ ፡ ስሞሙ ፡ ፪ተ ፡ ፻ተ ፡ ፳ ፡ ወ፪ተ ፡ ዓመተ ።

፳፬ ፤ ወእምአመ ፡ ነግሠ ፡ ነአኵቶ ፡ ለአብ ፡ እምድኅረ ፡ ፲ቱ ፡ ዓመት ፡ ተወልደ ፡ አቡነ፡

በሆነ ፡ ክህነቱ ፡ ቀድሶ ፡ ሕዝቡን ፡ አቌረባቸው ።

፲፱ ፤ አምላካችንም ፡ መሥዋዕቱን ፡ እንደመልከ ፡ ጼዴቅና እንደ ፡ አብርሃም ፡ መሥዋዕት ፡ የተወደደ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ተቀበለው ።

፳ ፤ ከዚያም ፡ በዚች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ሥጋዬን፡ የበላ፡ ደሜን የጠጣ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአቱ ፡ ይሰረይለታል ፡ ግሩም ፡ ከሚሆን ከሲኦል ፡ ሞትም ፡ ይድናል ፡ ሲል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሰጠው ።

፳፩ ፤ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በርሱ ፡ እጅ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ይቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ ከሮም ፡ አገር ፡ የመጡ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ መነኰሳት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ በየአውራጃዋ ፡ ተሠማርተዋል ።

፳፪ ፤ ነአኵቶ ፡ ለአብም ፡ እንደዚሁ፡ ከምሥራቋ፡ እስከ፡ ምዕራቧ በምታበራ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ውብ ፡ የሆነች ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ክርስቲያንን ፡ ሠራ ።

፳፫ ፤ አስቀድመን ፡ ስማቸውን፡ የጠራናቸው ፡ እነዚህ ፡ ነገሥታት ፡እግዚአብሔርን፡ በመፍራት ፡ በእውነትና ፡ በሰላም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ነገሡ ።

፳፬ ፤ ነአኩቶ ፡ ለአብ ፡ በነገሠ ፡ በ፲ኛው ፡ ዓመት ፡ አባታችን ፡ አባ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ተወለደና

«ዓ» ፡ በመጽሐፈ ፤ ድርሳኑ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ።

፱ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ ነግሠ ፡ ንዋየ ፡ ማርያም ፡ ንጉሥ ፡ ዘተሰምየ ፡ ዳግማዊ ፡ ዳዊት ፡ ወካልኡ ፡ ስሙ ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ ዳግማዊ ።

፲ ፤ ወኮነ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ርቱዕ ፡ በጽድቅ ፡ ወመፍቀሬ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ።

፲፩ ፤ ወአምጽአን ፡ ለሥዕላተ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ እለ ፡ ሰዓሎን ፡ ሉቃስ ፡ ወንጌላዊ ፡ እምኢየሩሳሌም ።

፲፪ ፤ ለአሐቲ ፡ ረሰያ ፡ ደብረ ፡ ጅብላ ፡ ዘሀገረ ፡ ጎጃም ፡ ዲበ ፡ ዘዓተባ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ በደሙ ፡ ለአምላክነ ።

፲፫ ፤ ወለአሐቲኒ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ ወርቅ ፡ ወለሣልሳኒ ፡ ውስተ ፡ ሐይቅ ።

፲፬ ፤ ወለሥዕለ ፡ ዑራኤልሰ ፡ ዘሰአሎ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ረሰዮ ፡ ምስሌሁ ፡ ኅቡረ ፡ ውስተ ፡ ከተማሁ ፡ በሐይመተ ፡ ፒሶስ ፡ ዘእንትም ፡ በወርቅ ።

፲፭ ፤ ወለልብሰ ፡ እግዚእነሰ ፡ ከለሜዳ ፡ አንበሮ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ ነገሥት ፡ በሀገረ ፡ እምባሰል ፡ ኀበ ፡ ዘዓተባ ፡ በደመ ፡

ድርሳን ፡ መጽሐፍ ፡ «ዓ» ፡ ተብሎ ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ።

፱ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዳግማዊ ፡ ዳዊት ፡ ማለትም ፡ ሁለተኛው ፡ ስሙ ፡ ዳግማዊ ፡ ቆስጠንጢኖስ የተባለ ፡ ንዋየ ፡ ማርያም ፡ ነገሠ ።

፲ ፤ ይኸውም ፡ ሃይማኖቱ ፡ የቀና ፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ እመቤታችን ፡ ድንግል ፡ ማርያምን ፡ የሚወድ ፡ ነበር ።

፲፩ ፤ እሱም ፡ ወንጌላዊው ፡ ሉቃስ ፡ የሣላቸውን ፡ የእመቤታችንን ፡ ሥዕሎች ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ አስመጣ ።

፲፪ ፤ አንዲቱን ፡ ሥዕል ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ በአምላካችን ደም ፡ በቀደሳት ፡ ጅብላ ፡ በምትባል ፡ ቦታ ፡ በጎጃም ፡ አስቀመጣት ።

፲፫ ፤ ሁለተኛዋን ፡ በደብረ ወርቅ ፡ ሦስተኛዋንም ፡ በሐይቅ፣ ውስጥ ፡ አኖራት ።

፲፬ ፤ ወንጌላዊው ፡ ዮሐንስ ፡ የሣለው ፡ የዑራኤልን ፡ ሥዕል ፡ ግን ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ በወርቅ ፡ ግምጃ ፡ በተሠራ ፡ ድንኳን፣ ውስጥ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ አኖረው ።

፲፭ ፤ የጌታችንን ፡ የቀይ ፡ ግምጃ ፡ ልብሱን ፡ ግን ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ፡ ደም ፡ በቀደሳት ፡ በአምባሰል ፡ ሀገር ፡ በክብረ ፡



እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ።

፲፮ ፤ ወአልዓለ ፡ ክብሮ ፡ ለውእቱ ፡ ደብር ፡ እምክብረ ፡ ኵሎን፣ አድባራት ።

፲፯ ፤ ወሰመዮ ፡ ስሞ ፡ ደብረ ፡ ከርቤ ።

፲፰ ፤ ወመጽኡ ፡ ብዙኃን ፡ ቅዱሳን ፡ ወመጻሕፍት ፡ በመዋዕሊሁ ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ ወእምብሔረ ፡ ሶርያ ።

፲፱ ፤ ወዓዲ ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ ወሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ወመጽሐፈ ፡ ድርሳነ ፡ ዜናሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ምስለ ፡ መጽሐፈ ፡ ተአምረ ፡ ወልዳ ፡ ዘይሰመይ ፡ አልሐቀፋሩ ትሩፈ ፡ ወንጌል ፡ ብሂል ፡ እምሀገረ ፡ ማዕልቃ ፡ ዘምስር ።

፳ ፤ ሣልስ ፡ መጽሐፈ ፡ ኪዳኑ ለእግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡ ኍልቄ አናቅጺሁ ፡ ዘኮነ ፡ ፹ወ፱ቱ ፡ ምስለ ፡ ኍልቄ ፡ ንኡስ ፡ ምዕራፋቲሁ ፡ ፫፻፡፳ወ፱ ፡ ዘጸሐፎን ቴዎግሎስ ፡ ዮሐንስ ፡ ፍቁረ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

፳፩ ፤ ወራብዕ ፡ መጽሐፈ ፡ ተአምራቲሃ ፡ ለእግዝእነ ፡ ማርያም ድንግል ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡

ነገሥት ፡ ደብር ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጠው ።

፲፮ ፤ ያንንም ፡ ደብር ፡ ከከበሩት ፡ አድባራት ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ የሱን ፡ ክብር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገ ።

፲፯ ፤ ስሙንም ፡ ደብረ ፡ ከርቤ ፡ ብሎ ፡ ሰየመው ።

፲፰ ፤ በዘመኑም ፡ ከኢየሩሳሌምና ፡ ከሶርያ ፡ አገር ፡ ብዙዎች ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ መጡ ።

፲፱ ፤ ዳግመኛም ፡ በምሥር ፡ ውስጥ ፡ ከምትሆን ፡ ከማዕልቃ ፡ አገር ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማትና ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ እንዲሁም ፡ አምላክን ፡ የወለደች የእመቤታችን ፡ የድንግል ፡ ማርያም ፡ የድርሳኗን ፡ ዜና ፡ የሚያበሥር ፡ መጽሐፍና ፡ አልሐቀፋሩ ከሚባል ፡ ከልጅዋ ፡ ተአምር ፡ ጋር ፡ መጣ ፡ ይህም ፡ ተረፈ ፡ ወንጌል ፡ ማለት ፡ ነው ።

፳ ፤ ሦስተኛም ፡ የአንቀጹ፣ ቍጥር ፡ አርባ ፡ ዘጠኝ ፡ ከንኡሳን ምዕራፎቹ ፡ ጋር ፡ ሦስት ፡ መቶ ስልሳ ፡ ዘጠኝ ፡ የሆነ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መጽሐፈ ፡ ኪዳኑ ፡ ጭምር ፡ መጣ ።

፳፩ ፤ አራተኛ ፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ የእመቤታችን ፡ የድንግል ፡ ማርያም ፡ የተአምራቶቿ፣ መጻሕፍት ፡ ቍጥር ፡ ሦስት ፡

ርኃ ፡ ጥቅምት ፡ ረሰየ ፡ ከመ ፡ ያክብሩ ፡ ዘንተ ፡ ዓቢየ ፡ በዓለ ፡ ዝንቱ ፡ ኒጋሢ ፡ እንድርያስ ።

፶፮ ፤ ወአመ ፡ ኮነ ፡ ቅዳሴሃ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘደብረ ፡ ዝቋላ ፡ አስተርአየ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምስለ ፡ እሙ ፡ ወምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ መላእክቲሁ ፡ ቅዱሳን ።

፶፯ ፤ ወተመክረ ፡ መሥዋዕተ ፡ ንጹሐ ፡ ዘአልቦ ፡ ነውር ።

፶፰ ፤ ውእቱኒ ፡ ንጉሥ ፡ እንድርያስ ፡ ተመጠወ ፡ ቍርባነ ፡ በእደዊሆሙ ፡ ለካህናት ፡ ኅሩያን ።

፶፱ ፤ ወተፈጸመ ፡ ስመ ፡ ትእምርቱ ፡ ዘተነግረ ፡ በመጽሐፈ ፡ ድርሳኑ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ተብሂሉ ፡ «እ» ፡ ይነግሥ ።

፷ ፤ ወዝንቱኒ ፡ ንጉሥ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በደብረ ፡ የረር ፡ አዕረፈ ፡ በሰላም ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡ ወተቀብረ ፡ በደብረ ፡ ዝቋላ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያና ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ።

፷፩ ፤ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ገነተ ፡ ትፍሥሕት ፡ ዘኢየኃልፍ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ታላቅ ፡ በዓል ፡ በፍጹም ፡ ደስታ ፡ ጥቅምት ፡ ሃያ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ እንዲከበር ፡ አደረገ ፡ እንላቸዋለን ።

፶፮ ፤ የደብረ ፡ ዝቋላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በተባረከች ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከእናቱና ፡ ከቅዱሳን ፡ መላእክቶቹ ፡ ጋር ፡ ተገለጸ ።

፶፯ ፤ ነውር ፡ ነቀፋ ፡ የሌለበትን ፡ መሥዋዕት ፡ ጌታችን ፡ ተቀበለ ።

፶፰ ፤ ንጉሡ ፡ እንድርያስም ፡ በተመረጡ ፡ በካህናት ፡ እጅ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ተቀበለ ።

፶፱ ፤ በቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ የድርሳን ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የስሙ ፡ ምልክት ፡ «እ» ይነግሣል ፡ ተብሎ፡ የተነገረው ፡ ቃል ፡ ተፈጸመ ።

፷ ፤ ይህም ፡ ንጉሥ ፡ በደብረ ፡ የረር ፡ ሳለ ፡ ከዚህ ፡ ከኃላፊው ፡ ዓለም ፡ በሰላም ፡ ዓረፈና ፡ በደብረ ፡ ዝቋላ ፡ አምላክን ፡ በወለደች ፡ በእመቤታችን ፡ በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተቀበረ ።

፷፩ ፤ ለዘላለሙ ፡ ወደማያልፈው ፡ ደስታ ፡ ካለበት ፡ ወደገነት ፡ ገባ ።



ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ነግሠ ፡ እኁሁ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ ወኮነ ፡ ርቱዓ ፡ ሃይማኖት ።

፪ ፤ ወሐነጸ ፡ ቀዳሚ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ዓቢየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በስመ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

፫ ፤ ወካዕበ ፡ በስመ ፡ እሙ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ።

፬ ፤ ወሣልስ ፡ በስመ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ።

፭ ፤ ወካዕበ ፡ ሐረ ፡ ብሔረ ፡ ወግዳ ፡ ወዓርገ ፡ ደብረ ፡ ዓደ ፡ ሸዋ ፡ ወሐነጸ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በስማ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ።

፮ ፤ ወረሰየ ፡ በዓላ ፡ አመ ፡ አሚሩ ፡ ለግንቦት ፡ በዕለተ ፡ ልደታ ።

፯ ፤ ወረሰዮ ፡ ለዛቲ ፡ ደብር ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ለአባ ፡ መባዓ ፡ ጽዮን ፡ ጻድቅ ፡ ወልደ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ዘወገግ ።

፰ ፤ ወእምዝ ፡ ሐረ ፡ ብሔረ ፡ ግብጽ ፡ ለፀቢዓ ፡ አሕመድ ፡

ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሃይማኖቱ ፡ የቀና ፡ ወንድሙ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ ነገሠ ።

፪ ፤ አሱም ፡ መጀመሪያ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ደብረ፡ ብርሃን ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ሠራ ።

፫ ፤ ሁለተኛም ፡ ቅድስት ፡ በሆነች ፡ በእናቱ ፡ በድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ።

፬ ፤ ሦስተኛም ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ በሆነ ፡ በቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ስም ።

፭ ፤ አራተኛም ፡ ወደ ፡ ወግዳ ፡ ሄደና ፡ ዓደ ፡ ሸዋ ፡ ወጥቶ ፡ አምላክን ፡ በወለደች ፡ በእመቤታችን ፡ በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠራ ።

፮ ፤ክብረ ፡ በዓሏም ፡ እመቤታችን ፡ በተወለደችበት ፡ ዕለት ግንቦት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንዲከበር ፡ አደረገ ።

፯ ፤ የወገግ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል፡ ልጅ ፡ የሆነ ፡ ጻድቁን ፡ አባ ፡ መባዓ ፡ ጽዮንን ፡ ለዚች ፡ ደብር ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ወይም ፡ አስተዳዳሪ ፡ አድርጎ ፡ ሾመው ።

፰ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደግብጽ ፡ ሄዶ ፡ የእስላሞቹን ፡ ንጉሥ ፡

ወልደ ፡ ሸሪፍ ፡ ንጉሠ ፡ ተንባ
ላት ፡ ዘሀገረ ፡ ዓረብ ።

፱ ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ንጉሠ ፡
ተንባላት ፡ አሠሮ ፡ ለአባ ፡ ሚካ
ኤል ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘለእስክ
ንድርያ ፡ በእንተ ፡ ንዋየ ፡ ወርቅ ፡
ከመ ፡ የሀቦ ፡ ወአበዮ ፡ ወይቤሎ ፡
አባ ፡ ሚካኤል ፡ ኢይሁበከ ።

፲ ፤ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ወርቅ ፡
ክቡር ፡ ዘአምጽአ ፡ እምደብረ ፡
ቅዱስ ፡ ኖኅ ፡ አቡነ ፡ ወዳግመ ፡
እምዘአቅረብዎ ፡ አምኃሁ ፡ ሰብአ ፡
ሰገል ፡ በጊዜ ፡ ልደቱ ፡ ለአም
ላክነ ፡ ውእቱ ።

፲፩ ፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ረከ
ብዎ ፡ አበውየ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡
ወወሀቡ ፡ መንፈቆ ፡ ለነዳያን ፡
ወመንፈቆኒ ፡ አንበሩ ፡ ለሕንጻ ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፲፪ ፤ ወእመ ፡ መጽአ ፡ ቀዲ
ሙኒ ፡ ንጉሠ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዳግ
ማዊ ፡ ዳዊት ፡ ወሰከ ፡ ላዕሌሁ ፡
ብዙኃ ፡ ወርቀ ፡ ዘአምጽአ ፡
እምሀገሩ ፡ ወአንበሮ ፡ ምስለ ፡
ክቡር ፡ መስቀሉ ፡ ለእግዚእነ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምጽአ ፡
እምኢየሩሳሌም ፡ ከመ ፡ ይኩ
ነነ ፡ ተስፋ ፡ ረድኤተ ፡ ለሰብአ ፡
ግብጽ ።

፲፫ ፤ ወለእመ ፡ ወሀብክዎ ፡
ለዝንቱ ፡ ንጉሠ ፡ ሠራዊተ ፡

የሸሪፍን ፡ ልጅ ፡ አሕመድን ፡
ጦርነት ፡ ይገጥመው ፡ ዘንድ ፡
ተዘጋጀ ።

፱ ፤ ይህ ፡ የእስላም ፡ ንጉሥ ፡
የእስክንድርያውን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳ
ሳት ፡ አባ ፡ ሚካኤልን ፡ ወርቅ ፡
ስጠኝ ፡ ቢለው ፡ እንቢ ፡ አል
ሰጥም ፡ ስላለው ፡ አስሮት ፡
ነበርና ።

፲ ፤ ይህም ፡ ወርቅ ፡ ከክበረ ፡
ከአባታችን ፡ ከቅዱስ ፡ ኖኅ ፡
ደብር ፡ የመጣ ፡ ሲሆን ፡ ዳግመ
ኛም ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ ለአምላካ
ችን ፡ በልደቱ ፡ ጊዜ ፡ እጅ ፡
መንሻ ፡ ይሆነው ፡ ዘንድ ፡ ካመ
ጡት ፡ ወርቅ ፡ ጭምር ፡ ነው ።

፲፩ ፤ ስለዚህ ፡ አባቶቼ ፡ ሊቃነ ፡
ጳጳሳት ፡ እኩሌታውን ፡ ለድኆች ፡
ሰጥተው ፡ እኩሌታውን ፡ ለቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ማሠሪያ ፡ ብለው ፡
ያስቀመጡት ፡ ነው ፡ ሲል ፡ እምቢ ፡
አለው ።

፲፪ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡
ዳግማዊ ፡ ዳዊትም ፡ ወደኢየሩ
ሳሌም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ከሀገሩ ፡
ካመጣው ፡ ብዙ ፡ ወርቅ ፡ በሱ ፡
ላይ ፡ ጨምሮ ፡ ከጌታችን ፡ ከኢ
የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መስቀል ፡
ጋር ፡ ለግብጽ ፡ ሰዎች ፡ ተስፋ ፡
ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ያስቀመጠው ፡
ነው ።

፲፫ ፤ ስለዚህ ፡ ለእስላሞች ፡
ሠራዊት ፡ ንጉሥ ፡ ይህን ፡ ወርቅ ፡



ተንባላት ፡ ይከውነኒ ፡ ኃሣረ ፡
ወኃፍረተ ፡ በቅድመ ፡ ንጉሥ ፡
ሰማያዊ ፡ ብሂሎ ፡ አበየ ፡ ውሂ
ቦቶ ፡ ለዝ ፡ ወርቅ ።

፲፬ ፤ ወእምድኅረ ፡ አበዮ ፡
ሞቅሖ ፡ ለአባ ፡ ሚካኤል ፡ ወአ
ውዓዮን ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲ
ያናት ፡ ኵሎን ፡ ዘግብጽ ።

፲፭ ፤ ወሶበ ፡ ሰምዓ ፡ ዘንተ ፡
ንጉሥ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ ሖረ ፡
በጊዜሁ ፡ ብሔረ ፡ ግብጽ ።

፲፮ ፤ ወቦአ ፡ በሰላም ፡ እንዘ ፡
ይረድኦ ፡ ኃይለ ፡ ረድኤታ ፡ ለእ
ግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ወትንብ
ልናሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡
ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ወቀተሎ ፡
ለውእቱ ፡ ንጉሥ ፡ አሕመድ ፡
ተንባላታዊ ፡ ዘሀገረ ፡ ዓረብ ።

፲፯ ፤ ወለመኰንነ ፡ አዳልኒ ፡
ወጥልጣል ፡ በድላይ ፡ ቀተሎ ።

፲፰ ፤ ወለአባ ፡ ሚካኤልሰ ፡
ፈትሖ ፡ እምነ ፡ ሞቅሑ ፡ ወአ
ምጽአ ፡ ምስሌሁ ፡ ውስተ ፡ ሀገ
ሪትነ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ምስለ ፡
መስቀለ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ።

፲፱ ፤ ወረሰዮ ፡ ለመስቀል ፡
ከመ ፡ ይንበር ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡
ከርቤ ፡ ኀበ ፡ ሕንጻ ፡ አቡሁ ፡
ዳግማዊ ፡ ዳዊት ።

ብሰጠው ፡ በሰማያዊ ፡ ንጉሥ ፡
ፊት ፡ ወቀሳና ፡ ኃፍረት ፡ ይደ
ርስብኛል ፡ ብሎ ፡ ወርቁን ፡ አል
ሰጥም ፡ አለው ።

፲፬ ፤ በእንቢታውም ፡ ስለ ፡
ጸና ፡ አባ ፡ ሚካኤልን ፡ አስሮ ፡
በግብጽ ፡ ያሉትን ፡ አብያተ ፡
ክርስቲያናትን ፡ በሙሉ ፡ በእ
ሳት ፡ አቃጠላቸው ።

፲፭ ፤ ንጉሡ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆ
ብም ፡ ይህንን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡
ወዲያውኑ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ አገር ፡
ሄደ ።

፲፮ ፤ የእመቤታችን ፡ የድን
ግል ፡ ማርያም ፡ የረዳትነቷ ፡
ኃይልና ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡
የቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ አማላጅ
ነት ፡ እየረዳው ፡ ያለምንም ፡
ተቃውሞ ፡ ወደ ፡ ዓረብ ፡ አገር ፡
ገባና ፡ የእስላሙን ፡ ንጉሥ ፡
አሕመድን ፡ ገደለው ።

፲፯ ፤ የአዳልንና ፡ የጥልጣል ፡
ባላባት ፡ በድላይንም ፡ ገደለው ።

፲፰ ፤ አባ ፡ ሚካኤልን ፡ ግን ፡
ከእስራቱ ፡ ፈትቶ ፡ ከጌታችን ፡
ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መስቀል ፡
ጋር ፡ ወደ ፡ ሀገራችን ፡ ወደ ፡ ኢት
ዮጵያ ፡ ይዞት ፡ መጣ ።

፲፱ ፤ መስቀሉንም ፡ አባቱ ፡
ዳግማዊ ፡ ዳዊት ፡ ካሳነጸው ፡
ሕንጻ ፡ ውስጥ ፡ በደብረ ፡ ከርቤ ፡
እንዲቀመጥ ፡ አደረገ ።

፳ ፤ ወአዘዛ ፡ ለእኅቱ ፡ ዕሌኒ ፡ ንግሥት ፡ ወለቱ ፡ ለዳዊት ፡ ዳግማዊ ፡ ከመ ፡ ትሕንጽ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያና ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ሠናየ ፡ ዘኮነ ፡ እምኵሉ ።

፳፩ ፤ ወይእቲኒ ፡ ሐነጸት ፡ አሰርጊዋ ፡ በወርቅ ፡ ወበብሩር ፡ ዘይሜኒ ፡ እምቀዳሚ ።

፳፪ ፤ ወአመ ፡ ኮነ ፡ ቅዳሴ ፡ ቤታ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስተርአዮሙ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ፡ ወነገሮሙ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ጊዜ ፡ ስቅለትየ ፡ በቀራንዮ ፡ ሀገር ፡ ቀዲሖ ፡ እምገቦየ ፡ ደመ ፡ ዑራኤል ፡ ቀደሰ ፡ ኵለንታሃ ፡ ለዛቲ ፡ ደብር ።

፳፫ ፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ባረክዋ ፡ ወቀደስክዋ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ማኅደረ ፡ ለስብሐትየ ።

፳፬ ፤ ወይእዜኒ ፡ ረሰይክዋ ፡ ትኩን ፡ ርስተ ፡ ከመ ፡ ደብረ ታቦር ፡ መካነ ፡ ምሥጢርየ ፡ ወከመ ፡ ቀራንዮ ፡ መካነ ፡ ስቅለትየ ፡ ወከመ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መካነ ፡ እምየ ፡ ሥጋሃ ፡ ወሥጋየኒ ፡ እምነ ፡ ሥጋሃ ፡ ንጹሕ ፡ ኮነ ፡ አሐደ ።

፳፭ ፤ ወለእመ ፡ ተረክበ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ በዕለተ ፡ በዓላ ፡

፳ ፤ የዳግማዊ ፡ ዳዊት ፡ ልጅ ፡ እኅቱ ፡ ዕሌኒ ፡ ንግሥትንም ፡ በእመቤታችን ፡ በድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ ከሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ በሥራውም ፡ ያማረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትሠራ ፡ ዘንድ ፡ አዘዛት።

፳፩ ፤ እስዋም ፡ ከፊተኛው ፡ የሚበልጥ ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡ አስጊጣ ፡ ሠራቻት ።

፳፪ ፤ የዚችው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓተ ፡ ቅዳሴ ፡ ቤቷ ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተገለጸላቸውና ፡ በቀራንዮ ፡ በተሰቀልሁ ፡ ጊዜ ፡ ዑራኤል ፡ ከጐኔ ፡ የፈሰሰውን ፡ ደሜን ፡ ቀድቶ ፡ ይህችን ፡ ደብር ፡ ሁለንተናዋን ፡ ቀድሷታል ።

፳፫ ፤ ስለዚህ ፡ ለጌትነቴ ፡ ምስጋና ፡ ማደሪያ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ባርኬአታለሁ ፡ ቀድሻታለሁም ።

፳፬ ፤ አሁንም ፡ ምሥጢረ ፡ መለኮቴ ፡ እንደተገለጸበት ፡ እንደ፡ ደብረ ፡ ታቦርና ፡ እንደ ፡ ተሰቀልሁበት ፡ እንደቀራንዮ ፡ ዐደባባይ ፡ እንዲሁም ፡ ንጹሕ ፡ የሆነ ፡ ከሥጋዋ ፡ ሥጋ ፡ ነሥቼ ፡ ሰው ፡ እንደመሆኔ ፡ እንደ ፡ እናቴ ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ርስት ፡ አድርጌአታለሁ ፡ ሲል ፡ ነገራቸው ።

፳፭ ፤ ማንኛውም ፡ ክሩቅም ፡ ሆነ ፡ ከቅርብ ፡ መጥቶ ፡ በክብረ ፡



ወዘነገደኒ ፡ ኀቤሃ ፡ እምርኁቅ ፡ ፍኖት ፡ ይከውን ፡ ከመ ፡ ዘነገደ ፡ ኀበ ፡ መቃብርየ ፡ ኢየሩሳሌም ።

፳፮ ፤ ወካዕበ ፡ ለእመ ፡ ተመጠወ ፡ ሥጋየ ፡ ወደምየ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘእምየ ፡ ዘሐነጽዋ ፡ ምስለ ፡ እኅቱ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ ወአቡሁ ፡ ዳዊት ፡ አነ ፡ ኣድኅኖ ፡ እሞተ ፡ ኃጢአት ።

፳፯ ፤ ወአዓድዎ ፡ ካዕበ ፡ እምባሕረ ፡ እሳት ፡ ዘሲኦል ፡ ወአነብሮ ፡ ውስተ ፡ ገነተ ፡ ትፍሥሕት ፡ ዘጽድቅ ፡ ወዘሕይወት ።

፳፰ ፤ ወዘንተ ፡ ኪዳነ ፡ ቃሎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነገሩ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ሚካኤል ፡ ወአባ ፡ ገብርኤል ፡ በመሐላ ፡ ጽኑዕ ፡ ዘኢይትሔሰው።

፳፱ ፤ ወእምዝ ፡ ሐነጸ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፪ተ ፡ በሀገረ ፡ ተጕለት ፡ በስማ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ወሰመያ ፡ ለአሐቲ ፡ ደብረ ፡ ምጥማቅ ፡ በአምሳለ ፡ ደብረ ፡ ምጥማቅ ፡ ዘሀገረ ፡ አትራብ ፡ ዘአውዓያ ፡ ንጉሠ ፡ ተንባላት ።

፴ ፤ ወዳግመ ፡ ፪ተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሀገረ ፡ ሞረት ፡ ኀበ ፡ መቃብሩ ፡ ለቅዱስ ፡ አባ ፡

በዓሏ፡ ላይ ፡ የተገኘ ፡ ሰው ፡ ከመካነ ፡ መቃብሬ ፡ ዘንድ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንደ ፡ ሄደ ፡ ይቈጠርለታል ።

፳፮ ፤ ዳግመኛ ፡ አባቴ ፡ ዳግማዊ ፡ ዳዊትና ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ ከእኅቱ ፡ ጋር ፡ ባሠሯት ፡ በዚች ፡ በእናቴ ፡ ቤተ ክርስቲያን፡ ውስጥ ፡ ሥጋዬንና ፡ ደሜን ፡ የተቀበለውን ፡ ሰው ፡ ከኃጢአት ፡ ሞት ፡ አድነዋለሁ ።

፳፯ ፤ ዳግመኛም ፡ የሲኦልን ፡ ባሕር ፡ አሻግሬ ፡ ጽድቅና ፡ ሕይወት ፡ ደስታም ፡ ካለበት ፡ ገነት ፡ ውስጥ ፡ አኖረዋለሁ ።

፳፰ ፤ ይህም ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የማይታበል ፡ መሆኑን ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳቱ ፡ አባ ፡ ሚካኤልና ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ በጽኑ ፡ መሐላ ፡ አረጋግጠዋል ።

፳፱ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በተጕለት ፡ ውስጥ ፡ በእመቤታችን ፡ በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ ሁለት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠራና ፡ አንደኛዋን ፡ በአትሪብ ፡ አገር ፡ የእስላም ፡ ንጉሥ ፡ ባቃጠላት ፡ በደብረ ፡ ምጥማቅ ፡ አምሳል ፡ ደብረ ፡ ምጥማቅ ፡ ብሎ ፡ ሰየማት ።

፴ ፤ ዳግመኛም ፡ በሞረት ፡ ውስጥ ፡ ቅዱስ ፡ በሚሆን ፡ በአባ ፡ ዜና ፡ ማርቆስ ፡ መቃብር ፡ ላይ ፡

ካህን ፡ ምስለ ፡ መነኰሳት ፡ ቅዱሳን ።

፶፮ ፤ በ ፡ እለ ፡ ይቤሉ ፡ ዘለለ ደብሩ ፡ መነኰሳት ፡ ኢያጸድቅ ፡ ግብረ ፡ ማኅሌቶሙ ፡ ለያሬድ ፡ ካህን ፡ ወለአባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወዘ ርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ ንጉሥ ፡ ወማኅ ሌተ ፡ ጽጌ ፡ ዘአባ ፡ ገብረ ፡ ማር ያም ።

፶፯ ፤ ወይቤ ፡ ስምዑ ፡ አኃ ውየ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ፩ዱ ፡ መነ ኰስ ፡ ዘሀገሪትነ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዘይከልእ ፡ ከመ ፡ ኢይጸልዩ ፡ ድርሰተ ፡ እሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ዘግብረ ፡ ማኅሌት ፡ ወቅኔ ፡ ወሰ ላም ።

፶፰ ፤ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ በቃና ፡ ዘገሊላ ፡ አሐዱ ፡ መምህር ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ምስለ ፡ ውእቱ ፡ እስክንድር ፡ ንጉሥ ፡ እንዘ ፡ ይነግር ፡ መጽሐፈ ፡ ትርጓሜ ፡ ዘወንጌል ፡ ምስለ ፡ ብዙኃን ፡ መነኰሳት ፡ መሰጦ ፡ ማእከለ ፡ ጉባኤ ፡ በቃና ፡ ዘገሊላ ፡ አመ ፡ ፲ወ፫ ፡ ለወርኃ ፡ ጥር ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ።

፶፱ ፤ ወአርአየ ፡ ትዕይንተ ፡ ኵሎሙ ፡ መላእክት ፡ እንዘ ፡ ይዜምሩ ፡ በዘእሉ ፡ ዝማሬ ፡ ለክ

አገባብ ፡ ሁሉ ፡ ከቅዱሳን ፡ መነ ኰሳት ፡ ጋር ፡ ስምምነት ፡ ተደ ረገ ።

፶፮ ፤ የካህኑ ፡ የያሬድና ፡ የአባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የንጉሡ ፡ የዘርዐ ፡ ያዕቆብም ፡ የማኅሌታቸው ፡ ድር ሰት ፡ የአባ ፡ ገብረ ፡ ማርያምም ፡ ማኅሌተ ፡ ጽጌ ፡ አያጸድቅም ፡ የሚሉ ፡ መነኰሳት ፡ በየደብሩ ፡ ነበሩና ።

፶፯ ፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ስለ ዚህ ፡ ነገር ፡ የሀገራችን ፡ የኢ ትዮጵያ ፡ መነኩሴ ፡ የነዚህን ፡ የቅዱሳን ፡ ድርሰት ፡ የማኅሌት ፡ ሥራና ፡ ቅኔ ፡ ሰላምታም ፡ እን ዳይጸለይ ፡ በከለከለበት ፡ ጊዜ ፡ የተፈጸመውን ፡ ተአምር ፡ ልን ገራችሁ ፡ ስሙኝ ፡ አለ ።

፶፰ ፤ ከዕለታት ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ ከንጉሡ ፡ እስክንድርና ፡ ብዙዎች ፡ መነኰሳት ፡ የቃና ፡ ዘገሊላ ፡ በዓል ፡ ላይ ፡ በተገኙ በት ፡ ዕለት ፡ አንድ ፡ መምህር ፡ የወንጌልን ፡ ትርጉም ፡ ሲያስተ ምር ፡ ሳለ ፡ ጥር ፡ ዓሥራ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ የቃና ፡ ዘገሊላ ፡ ዕለት ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ መምህሩን ፡ ከመካከላቸው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አሳረገው ።

፶፱ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ መላእክት ፡ በከተሞቻቸው ፡ ሁነው ፡ በያሬ ድና ፡ በአባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በዘርዐ ፡ ያዕቆብና ፡ በአባ ፡ ገብረ ፡ ማር ያም ፡ ማኅሌት ፡ ወይም ፡ ምስ



ብሬ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ።

፷ ፤ ወአሜሃ ፡ ይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ለውእቱ ፡ መምህር ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ነጸርከ ፡ ወአእ መርከ ፡ ነዓ ፡ ንረድ ፡ እስኩ ፡ ኀበ ፡ እስክንድር ፡ ንጉሥ ።

፷፩ ፤ አውሥአ ፡ ወይቤሎ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ መምህር ፡ አ ፡ ሊቅየ ፡ አንሰ ፡ እነብር ፡ በዛቲ ፡ ሀገር ፡ ሠናይት ፡ ወኢይ ወርድ ፡ እምኔሃ ፡ ወኢየሐውር ፡ ኀበ ፡ እስክንድር ፡ ንጉሥ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ።

፷፪ ፤ ወአሜሃ ፡ አውሥአ ፡ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ኢትነብር ፡ አንተ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ሀገር ፡ ፍጹመ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ዛቲ ፡ መምህራን ፡ መነኰሳት ፡ አባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወአባ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ዘደብረ ፡ ሐጊታ ፡ ወአባ ፡ ሠርጸ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዘደ ብረ ፡ ምስዓለ ፡ ማርያም ፡ ወመ ምህረ ፡ ደብረ ፡ ወርቅ ፡ ዘአን ሥአ ፡ በጸሎቱ ፡ ለወለተ ፡ ንጉሥ ፡ በእደ ፡ ማርያም ።

፷፫ ፤ ወሶቤሃ ፡ ይቤ ፡ ውእቱ ፡ መምህር ፡ አነኒ ፡ እኩን ፡ ከማ ሆሙ ፡ ከመ ፡ እሉ ፡ ቅዱሳን ።

ጋና ፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ እመ ቤታችን ፡ ስለድንግል ፡ ማርያም ፡ ክብር ፡ በነዚሁ ፡ የዜማ ፡ ስል ቶች ፡ ሲያመሰግኑ ፡ አሳየው ።

፷ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራ ኤል ፡ ያን ፡ መምህር ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አየህ ፡ ዐወቅህም ፡ እን ግዲህ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ እስክንድር ፡ እንውረድ ፡ አለው ።

፷፩ ፤ ያም ፡ መምህር ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ በዚች ፡ በምታምር ፡ አገር ፡ እኖ ራለሁ ፡ እንጂ ፡ አልወርድም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ እስክንድ ርም ፡ አልሄድም ፡ ሲል ፡ መለ ሰለት ።

፷፪ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ መልሶ ፡ አንተ ፡ በዚች ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ በፍጹም ፡ አት ኖርባትም ፡ የሚኖሩባት ፡ መም ህራን ፡ የሆኑ ፡ መነኰሳት ፡ አባ ፡ ጊዮርጊስና ፡ የደብረ ፡ ሐጊታው ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ እንዲ ሁም ፡ የንጉሡ ፡ የበእደ ፡ ማር ያምን ፡ ልጅ ፡ በጸሎቱ ፡ ከሞ ተች ፡ በኋላ ፡ ያሥነሣት ፡ የምስ ዓለ ፡ ማርያምና ፡ የደብረ ፡ ወርቅ ፡ መምህር ፡ የሆነ ፡ አባ ፡ ሠርጸ ፡ ጴጥሮስ ፡ ናቸው ፡ አለው ።

፷፫ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ አስተማ ሪው ፡ እኔም ፡ እንደ ፡ ቅዱሳኑ ፡ እሆናለሁ ፡ አለ ።

፪ ፤ ወለውእቱኒ ፡ አስተዮ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ጽዋዓ ፡ ልቡና ፡ ከመ ፡ እኍኍ ።

፫ ፤ ወደረሰ ፡ መልክአ ፡ ውዳሴሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ወሰላመ ፡ ውዳሴ ፡ ዘመልክአቲሃ ፡ ምስለ ፡ ቅዱሳን ፡ መኳንንቲሁ ።

፬ ፤ ወዘእሉኒ ፡ መኳንንት ፡ አስማቲሆሙ ፡ አርከ ፡ ኢየሱስ ፡ ወገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ ወስመ ፡ ምን ኵቲናሆሙ ፡ ሰይ ፡ ራስ ፡ ወባሊያ ።

፭ ፤ ወሐነጸ ፡ ናያድ ፡ ንጉሥ ፡ ዓቢየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዲበ ፡ ሀገረ ፡ በዬ ፡ (ዮ ፡) ኅበ ፡ ከተማሁ ፡ ለውእቱ ፡ መኰንን ፡ ዘተብህለ ፡ ሰይ ፡ ራስ ፡ በስማ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ወሰመያ ደብረ ፡ ሰይ ።

፮ ፤ ወሠርዓ ፡ በውስቴታ ፡ ፫ተ ፡ ፪ተ ፡ ፲ተ ፡ ወ፰ተ ፡ ካህናተ ፡ ቅዱሳነ ፡ ለዝማሬሃ ፡ ወለቅዳሴ ፡ ቍርባን ።

፯ ፤ ወአዘዘ ፡ ከመ ፡ ኢይጸእ ፡ መንበረ ፡ ጳጳሳት ፡ እመንበረ ፡ ክብራ ።

፰ ፤ ወኢይግበሩ ፡ ተድባበ ፡ ርእሶሙ ፡ ንቡራነ ፡ እድ ፡ ዘሀ

፪ ፤ ለእሱም ፡ እንደወንድሙ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ጽዋዓ ፡ ልቡናን ፡ አጠጣው ።

፫ ፤ አምላክን ፡ የወለደች ፡ የእመቤታችን ፡ የድንግል ፡ ማርያምን ፡ መልክአ ፡ ውዳሴዋንና ፡ እንዲሁም ፡ ከቅዱሳን ፡ መኳንንቶቹ ፡ ጋር ፡ የመልኮቿን ፡ የምስጋና ፡ ሰላምታ ፡ ደረሰ ።

፬ ፤ የመኳንንቶቹም ፡ ስም ፡ ፩ኛው ፡ አርከ ፡ ኢየሱስ ፡ ፪ኛውም ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ ሲሆን ፡ የምንኩስና ፡ ስማቸውም ፡ ሰይ ፡ ራስና ፡ ባሊያ ፡ ነው ። ፡

፭ ፤ ንጉሡ ፡ ናያድ ፡ ራስ ፡ ሰይ ፡ በተባለ ፡ በዚሁ ፡ መኰንን ፡ ከተማ ፡ በዬ ፡ (ዮ) ፡ ውስጥ ፡ አምላክን ፡ በወለደች ፡ በእመቤታችን ፡ በድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ ታላቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠራና ፡ ስሚንም ፡ ደብረ ፡ ሰይ ፡ አላት ።

፮ ፤ በውስጧም ፡ መሥዋዕትን ፡ የሚሠውና ፡ በማኅሌት ፡ የሚዘምሩ ፡ ቅዱሳን ፡ የሆኑ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ካህናትን ፡ አዘጋጀ ፡ ወይም ፡ ተከለ ።

፯ ፤ መንበረ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ከዚችው ፡ ደብር ፡ ወደሌላ ፡ እንዳይዛወር ፡ ወይም ፡ እንዳይ ወጣ ፡ አዘዘ ።

፰ ፤ የመሀግል ፡ ሀገር ፡ ንቡራን ፡ እድና ፡ ጳጳስ ፡ የደብረ ፡



ገረ ፡ መሐግል ፡ ወጳጳስ ፡ ወመ ምህር ፡ ዘደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ አመ ፡ መጽኡ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ደብር ።

፱ ፤ ወእሉ ፡ ንቡራነ ፡ እድ ፡ ይግበሩ ፡ ተድባበ ፡ ምስለ ፡ ጳጳስ ፡ መትሕቲሁ ፡ ለጳጳስ ።

፲ ፤ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ገቢሮት ፡ በውስቴታ ፡ ተድባበ ፡ ዘእንበለ ፡ ይእቲ ፡ በዓለ ፡ መንበር ።

፲፩ ፤ እስመ ፡ ተቀብረ ፡ በውስቴታ ፡ ክቡር ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ማርቆስ ፡ ዘአፍለሰ ፡ ዓፅመ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በክብር ።

፲፪ ፤ ወንቡረ ፡ እድ ፡ ዘደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገቢሮቱ ፡ ተድባበ ፡ በእንተ ፡ ገቢአቱ ፡ ቀዳሚ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ሀገር ፡ እምአኀኵራተ ፡ ከተታ ፡ ቀዲሙ ።

፲፫ ፤ እምዝኒ ፡ ገብረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በስመ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ቀዳሚ ።

፲፬ ፤ ወሥልሰ ፡ ገቢሮቱ ፡ ተድ ባበ ፡ ንቡረ ፡ እድ ፡ ዘሀገረ ፡ መሐ ግል ፡ ስብከተ ፡ ዕፃሁ ፡ ለቀው ስጦስ ፡ ንቡረ ፡ እድ ።

ሊባኖስም ፡ መምህር ፡ ወደዚች ፡ ደብር ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ለራሳ ቸው ፡ ድባብን ፡ አያደርጉ ፡ ሲል ፡ አዘዘ ።

፱ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ንቡ ራን ፡ እዶች ፡ ከጳጳሱ ፡ በታች ፡ በመሆን ፡ ከጳጳሱ ፡ ጋር ፡ ድባ ብን ፡ ያሲዙ ።

፲ ፤ በዚችው ፡ ደብር ፡ ውስጥ ፡ ድባብን ፡ ማድረግ ፡ ያለ ፡ ደብሯ ፡ መንበረ ፡ ጳጳስ ፡ በቀር ፡ ክልክል ፡ ነው ።

፲፩ ፤ ዳግመኛም ፡ የአባታችን ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ዓፅም ፡ ያፈለሰ ፡ ክቡር ፡ የሆነ ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ማርቆስ ፡ በውስጧ ፡ ተቀብሯልና ።

፲፪ ፤ የደብረ ፡ ሊባኖሱ ፡ ንቡረ ፡ እድም ፡ ድባብ ፡ ማድ ረጉ ፡ ከከተታ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ በመግባቱ ፡ ነው ።

፲፫ ፤ ከዚህም ፡ በላይ ፡ በመጀ መሪያ ፡ በቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ስም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠር ቷልና ።

፲፬ ፤ ሦስተኛም ፡ የመሐግሉ ፡ ሀገር ፡ ንቡረ ፡ እድ ፡ ድባብ ፡ የሚያደርገው ፡ ንቡረእድ ፡ የሆ ነው ፡ የቀውስጦስ ፡ የስብከቱ ፡ ክፍል ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

፲፭ ፤ ወአሐዱ ፡ ስሙ ፡ ለቀውስጦስ ፡ አቡነ ፡ ዳዊት ፡ በእንተ ፡ ዘኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ በይነ ፡ ተጋድሎቱ ፡ በሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ክርስቶስዊት ፡ ምስለ ፡ ዕልዋን ፡ ነገሥት ።

፲፮ ፡ ወአክበራ ፡ ለይእቲ ፡ ደብር ፡ ናዖድ ፡ ንጉሥ ፡ እምደብረ ፡ ዓባይ ፡ ወአክሱም ።

፲፯ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ ሖረ ፡ ሀገረ ፡ መንዝህ ፡ ወሐነጸ ፡ ፫ተ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ።

፲፰ ፤ አሐቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በስመ ፡ ማርያም ፡ ወለካልእታ ፡ በስመ ፡ ዑራኤል ፡ ወለሣልስታ ፡ በስመ ፡ እግዚእነ ፡ ውስተ ፡ ገዳመ ፡ ክሊና ፡ ዘትት በሃል ፡ እመን ።

፲፱ ፤ ወለካልኡ ፡ ዘብህልናሁ ፡ ዘይብልዎ ፡ ደብረ ፡ ቆጽሮስ ፡ ደንገዜ ።

፳ ፤ ወለሣልሱ ፡ ዘይብልዎ ፡ ምድረ ፡ አዜብ ፡ ደብረ ፡ ምድርያ ።

፳፩ ፤ ወአስርገዎን ፡ ለሠለስቲሆን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በወርቅ ፡ ወበብሩር ፡ ወበ ዕንቍ ፡ ያክንት ።

፲፭ ፤ የቀውስጦስም ፡ አንደኛው ፡ ስሙ ፡ አቡነ ፡ ዳዊት ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመው ፡ ከከሀዲዎች ፡ ወይም ፡ ከአላውያን ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡ የክርስቶስ ፡ እምነት ፡ በሆነች ፡ በቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ተጋድሎ ፡ አድርጎ ፡ ሰማዕት ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

፲፮ ፤ ይህችንም ፡ ደብር ፡ ንጉሡ ፡ ናዖድ ፡ ከደብረ ፡ ዓባይና ፡ ከአክሱም ፡ አብልጦ ፡ አከበራት ።

፲፯ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ መንዝ ፡ አገር ፡ ሄደና ፡ ሦስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠራ ።

፲፰ ፤ አንደኛዋን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእመቤታችን ፡ በድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ ሁለተኛዋንም ፡ በቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ስም ፡ ሦስተኛዋን ፡ እመን ፡ በምትባል ፡ በክሊና ፡ ገዳም ፡ ውስጥ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ሠራ ።

፲፱ ፤ ሁለተኛ ፡ ያልነው ፡ ደንገዜ ፡ ደብረ ፡ ቆጽሮስ ፡ የሚባለው ፡ ነው ።

፳ ፤ ሦስተኛ ፡ ያልነውም ፡ የአዜብ ፡ ምድር ፡ ደብረ ፡ ምድርያ ፡ የሚባለው ፡ ነው ።

፳፩ ፤ እነዚህን ፡ ሦስቱን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡ በሰማያዊ ፡ ዓይነት ፡ ዕንቍ ፡ አስጌጣቸው ፡



፳፪ ፤ ወሠርዓ ፡ ፲ተ ፡ ወ፪ተ ፡ ጉልተ ፡ ሀገር ፡ ለአሐቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ።

፳፫ ፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ወሀቦ ፡ ለናዖድ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ ከመ ፡ ኢይጥፋዕ ፡ ምስፍና ፡ ወምልክና ፡ በምድረ ፡ ሸዋ ፡ ወመንዝህ ፡ ወበሀገረ ፡ ጉራጌ ፡ ዘይብልዎ ፡ ምድረ ፡ ወረብ ፡ ወምሁር ።

፳፬ ፤ ወአዕረፈ ፡ ናዖድ ፡ ንጉሥ ፡ እምጸማ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡ አመ ፡ ፯ ፡ ለነሐሴ ፡ አመ ፡ ፅንሰተ ፡ በዓላ ፡ ለእመ ፡ አምላክ ፡ ፈጣሬ ፡ ኵሎን ፡ ዓለማት ፡ ቅድመ ፡ ፍጻሜሁ ፡ ለፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ በዘኍልቈ ፡ ፭፻ ፡ ዓመታት ፡ እምፍጥረተ ፡ ዓለም ።

፳፭ ፤ እስመ ፡ ውእቱኒ ፡ ናዖድ ፡ ንጉሥ ፡ ሰአሎ ፡ ለአምላክነ ፡ ከመ ፡ ኢይርአያ ፡ ለ፲፻፭ ፡ ዓመት ፡ ዘመነ ፡ ዓመፃ ፡ ወእከይ ፡ ወመዋዕለ ፡ አረሚ ፡ ወተንባላት ።

፳፮ ፤ ስምዑኬ ፡ አ ፡ አኃውየ ፡ አክብርዎ ፡ ወአፍቅርዎ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ እስመ ፡ ረዳኢክሙ ፡ በጊዜ ፡ ምንዳቤ ፡ ወመንሱት ።

፳፪ ፤ ለዚችም ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ ለሆነ ፡ ለቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ርስተ ፡ ጉልት ፡ ሰጠ ።

፳፫ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከምድረ ፡ ሸዋ ፡ ምሁርና ፡ ምድረ ፡ ወረብ ፡ ከሚባለው ፡ ከጉራጌ ፡ አገር ፡ ከመንዝም ፡ አገዛዝና ፡ መስፍንነት ፡ እንዳይጠፋ ፡ ለናዖድ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሰጠው ።

፳፬ ፤ ንጉሡ ፡ ናዖድም ፡ ኃላፊ ፡ ከሆነው ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ድካም ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ የፍጥረት ፡ ቍጥር ፡ ፍጻሜ ፡ ሳይሆን ፡ ዓለም ፡ በተፈጠረ ፡ በሰባት ፡ ሺህ ፡ ዘመን ፡ አስቀድሞ ፡ ዓለማትን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረ ፡ የአምላክ ፡ እናት ፡ የፅንሰቷ ፡ ዕለት ፡ በዓል ፡ በሚከበርበት ፡ ዕለት ፡ በነሐሴ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ዓረፈ ።

፳፭ ፤ ይኸውም ፡ ናዖድ ፡ ንጉሥ ፡ የእስላሞችንና ፡ የአረሚን ፡ ወይም ፡ የከሀዲን ፡ የተንኮልና ፡ የዓመፅን ፡ ዘመን ፡ የሆነችውን ፡ የስምንተኛውን ፡ ሺህ ፡ ዘመን ፡ እንዳያሳየው ፡ አምላካችንን ፡ ለምኖታልና ።

፳፮ ፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ስሙኝ ፡ የሠላእክት ፡ አለቃ ፡ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ በችግርና ፡ በመከራ ፡ ጊዜ ፡ ረዳታችሁ ፡ ነውና ፡ ውደዱት ፡ አክብሩትም ።

፫ ፤ ወበስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ዘተሰብአ ፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ በእንተ ፡ አፍቅሮቱ ፡ ሰብአ ።

፬ ፤ ወበስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘይነብር ፡ መልዕልተ ፡ አርያም ፡ ዘሠረጸ ፡ እምአብ ፡ ዘሎቱ ፡ ይደሉ ፡ ስብሐት ፡ ወአኰቴት ፡ እስከ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

፭ ፤ በዝንቱ ፡ ሥላሴ ፡ አሚነነ ንዜኑ ፡ ዜና ፡ ዕበዩ ፡ ወልዕልናሁ፡ ዘገብረ ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡ ቅዱስ ዑራኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ መልአከ ፡ ኃይልነ ።

፮ ፤ ስምዑኬ ፡ አበውየ ፡ ወአኃውየ ፡ ክቡራነ ፡ ስም ፡ ዘነገረነ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ አቡነ ፡ በድርሳኑ ፡ ዘውእቱ ፡ ነባቤ ፡ መለኮት ወሐዋርያ ፡ ሐዲስ ፡ ይቤ ፡ ቴዎዶጦስ ፡ ረድአ ፡ አብሮኮሮስ ፡ ዘያፈቅሮ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

፯ ፤ አንስ ፡ ርኢኩከ ፡ ኅቤሁ ፡ ለተስእሎተ ፡ ትእምርተ ፡ ትስብእቱ ፡ ለአምላክነ ፡ ማኅየዊ ፡ እስኩ ፡ ንግረኒ ፡ አቡየ ፡ እመ ፡ እቤሎ ፡ በፍርሃት ፡ ወበረዓድ ፡ እሜሃ ፡ አውሥአኒ ፡ ወይቤለኒ ፡

፫ ፤ ሰውን ፡ በመውደዱ ፡ ቅድስት ፡ ከሆነች ፡ ከድንግል ፡ ማርያም ፡ ሥጋዋን ፡ የለበሰ ፡ አንድ ፡ በሚሆን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ወልድ ስም ።

፬ ፤ ለዘላለሙ ፡ ፍጹም ፡ ምስጋና ፡ የሚገባው ፡ በአርያም ፡ የሚኖር ፡ ከአብ ፡ በሠረጸ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ።

፭ ፤ በአካል ፡ ሦስት ፡ በመለኮት ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን፡ እንደዚሁ ፡ አምነን ፡ የኃይላችን ረዳት ፡ የሆነ ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ቅዱስ ፡ ዑራኤል ፡ በምድር ፡ ላይ የሠራውን ፡ የገናናነቱንና ፡ የከፍተኛነቱን ፡ ዜና ፡ እንናገራለን ።

፮ ፤ ጌታችንን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ የሚወድ ፡ የአብሮኮሮስ ፡ ተማሪ ፡ የሆነ ፡ ቴዎዶጦስ ፡ በስም የከበራችሁ ፡ አባቶቼና ፡ ወንድሞቼ ፡ አዲስ ፡ ሐዋርያና ፡ የመለኮትን ፡ ሃይማኖት ፡ የሚያስተምር ፡ አባታችን ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ በድርሳኑ ፡ የነገረንን ፡ ስሙኝ ፡ አለ ።

፯ ፤ ማኅየዊ ፡ የሚሆን ፡ የአምላካችንን ፡ ሰው ፡ የመሆኑን ፡ ምልክት ፡ ለመጠየቅ ፡ ከሱ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ አይቼሃለሁና ፡ አባቴ ፡ ዮሐንስ ፡ እስኪ ፡ ንገረኝ ፡ ብዬ ፡ በፍርሃትና ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ ብጠይቀው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡



ዮሐንስ ፡ ሀሊሁ ፡ ስምዓኒ ፡ ወአጽምዓኒ ፡ ቴዎዶጦስ ፡ ወልድየ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ ብህንሳ ።

፰ ፤ አንሰ ፡ እቤ ፡ እንዘ ፡ ለሊሁ ኅቡእ ፡ በመለኮቱ ፡ ወበሥጋ ፡ ዚአነ ፡ በተዋሕዶቱ ፡ ክሡተ ፡ ኮነ ።

፱ ፤ ዓዲ ፡ ይቤ ፡ ሉትንዮስ ፡ ረድአ ፡ አብሮኮሮስ ፡ ዝሰ ፡ ኩነተ መለኮት ፡ ኅቡእ ፡ ለእመ ፡ እቤ፡ ኢኮነ ፡ ዕጹብ ፡ በኀቤከ ።

፲ ፤ አጠይቀኒ ፡ ባሕቱ ፡ አ ፡ አቡየ ፡ ይክልኑ ፡ ሥጋ ፡ ምድራዊ፡ ምስለ ፡ መለኮት ፡ ሰማያዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ በትእዛዝ ፡ ወበትዕግሥት ።

፲፩ ፤ እመ ፡ ኮነ ፡ ዕፅ ፡ ርጡብ ውስተ ፡ እሳት ፡ ውዑይ ፡ አመ ፡ ቦአ ፡ ኢይጠይስኑ ።

፲፪ ፤ እስመ ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ ሰመይናሁ ፡ ለመለኮት ፡ አመ ተዋሐደ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ አዳም ፡ እፎ ፡ ይከውን ፡ ዝንቱ ፡ ነገር ፡ ይቤ ።

፲፫ ፤ አ ፡ ወልድየ ፡ አርምም ኪነ ፡ ጥበቡ ፡ ዕጹብ ፡ ውእቱ ፡ ለአምላክነ ፡ ለሊሁ ፡ የአምር ፡ ዘገብረ ፡ ሰማያተ ፡ በጥበቡ ።

፲፬ ፤ ወውእቱ ፡ በጥበቡ ፡ ከመ ይረስዮሙ ፡ ግዑዛነ ፡ ለኵሎሙ ፡

ዮሐንስ ፡ መልሶ ፡ የብህንሳው ፡ አገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ልጄ ፡ ቴዎዶጦስ ፡ ስማኝ ።

፰ ፤ በመለኮቱ ፡ የማይመረመር የተሰወረ ፡ ሲሆን ፡ የኛን ፡ ሥጋ በመዋሐዱና ፡ በመልበሱ ፡ የተገለጠ ፡ ሆነ ፡ እላለሁ ።

፱ ፤ ዳግመኛም ፡ የአብሮኮሮስ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ሉትንዮስ ፡ መለኮት ፡ የማይመረመር ፡ የተሰወረ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ብል ፡ ይህ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ አይሆንም ፡ አለ ።

፲ ፤ አባቴ ፡ ሆይ ፡ እስኪ ፡ ንገረኝ ፡ ምድራዊ ፡ ሥጋ ፡ ከሰማያዊ መለኮት ፡ ጋር ፡ በመታዘዝና ፡ በመታገሥ ፡ እንዴት ፡ ሊዋሐድ ፡ ይችላል ? ።

፲፩ ፤ ዕንጨት ፡ ርጥበት ፡ ያለው ከሆነ ፡ እሳት ፡ ውስጥ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ አይጨስምን ።

፲፪ ፤ መለኮትን ፡ እሳት ፡ ነው ካልን ፡ ከአዳም ፡ ሥጋ ፡ ጋር ፡ በተዋሐደ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ እንዴት ይሆናል ? አለ ።

፲፫ ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ታገሥ ፡ የአምላካችን ፡ የጥበቡ ፡ ኃይል ፡ ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ ሰማያትን በጥበቡ ፡ የፈጠረ ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ብቻ ፡ ያውቃል ።

፲፬ ፤ ሁሉን ፡ የፈጠረ ፡ ነደ እሳት ፡ የሆነ ፡ መለኮት ፡ ነባቢ ፡

ነፍሳተ ፡ ጻድቃን ፡ ወኃጥኣን ፡ በትእምርተ ፡ ደሙ ፡ ነባቢ ፡ እንዘ ውእቱ ፡ ነደ ፡ እሳት ፡ መለኮታዊ ዘፈጠረ ፡ ኵሎ ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ በተ ዋሕዶት ፡ ዘምስለ ፡ ሥጋ ።

፲፭ ፤ ወኮነ ፡ ውእቱ ፡ ሥጋ ፡ በተዋሕዶቱ ፡ ዘምስለ ፡ መለኮት ፡ ሕያው ፡ አምላክ ።

፲፮ ፤ ወገነየ ፡ ለውእቱ ፡ ሥጋ ፡ ዘበሰማይኒ ፡ ወዘበምድርኒ ።

፲፯ ፤ ወበተዋሕዶቱ ፡ አዕተታ ፡ ለምንታዌ ።

፲፰ ፤ ወሶበ ፡ አፈድፈደ ፡ ጥይቅና ፡ ወሚመ ፡ ተስዕሎተ ፡ ዝኩ፡ አርመመ ፡ በተጠናቅቆ ፡ ኅሊና ።

፲፱ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ በከይኩ ቅድሜሁ ፡ ሶበ ፡ አርመመኒ ፡ አንሰኬ ፡ ግሙራ ፡ ሐለይኩ ፡ ጥቀ በእንተ ፡ ሥጋዌሁ ፡ ለአምላክነ ፡ እንዘ ፡ እፈርህ ፡ ወእርዕድ ፡ ተወ ሰከ ፡ ብየ ፡ ፍርሃት ፡ በዲበ ፡ ፍርሃት ።

፳ ፤ ወዓዲ ፡ ገሠጸኒ ፡ ዓቢየ ፡ ተግሣጸ ፡ በእንተ ፡ ስእለትየ ፡ ብዙኀ ፡ እመ ፡ አጽሐቅዎ ።

፳፩ ፤ ወዓዲ ፡ ይቤሎ ፡ አብሮ ኮሮስ ፡ ዘእንጊሬፌስ ፡ እስመ ፡ ዓዲ ፡ ሥጋ ፡ ዘነሥአ ፡ ውእቱ ፡

በሆነ ፡ በደሙ ፡ ምልክት ፡ የጻድ ቃንና ፡ የኃጥኣንን ፡ ነፍሳት ፡ በሙሉ ፡ ነፃ ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ እሱ ፡ ራሱ ፡ በፍጹም ፡ ጥበቡ ፡ ከሥጋ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዶ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሆነ ።

፲፭ ፤ እሱ ፡ ሥጋ ፡ ከመለኮት ጋር ፡ በመዋሐዱ ፡ ሕያው ፡ አም ላክን ፡ ሆነ ።

፲፮ ፤ ለዚህም ፡ ሥጋ ፡ በሰማ ይም ፡ በምድርም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ተገዛለት ።

፲፯ ፤ ሥጋ ፡ ከመለኮት ፡ ጋር ፡ በመዋሐዱ ፡ የሁለት ፡ ባሕርይን ፡ ጠባይ ፡ አስወግዶ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ሆነ ።

፲፰ ፤ የዚህን ፡ ጥያቄ ፡ ባበዛ፡ ጊዜ ፡ ሐሳቡን ፡ በመሰብሰብ ፡ ወይም ፡ በመወሰን ፡ ዝም ፡ አለ ።

፲፱ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዝም ፡ ባለኝ ፡ ጊዜ ፡ በፊቱ ፡ አለቀስሁ ፡ ግን ፡ የአምላክ ፡ ሥጋን ፡ ስለመ ልበስ ፡ ስፈራና ፡ ስንቀጠቀጥ ፡ ፈጽሜ ፡ አሰብሁና ፡ ይልቁንም ፡ በፍርሃት ፡ ላይ ፡ ፍርሃት ፡ ተጨመ ረብኝ ።

፳ ፤ መላልሼ ፡ እየለመንሁ ፡ አስጨንቄ ፡ ስለጠየቅሁት ፡ እን ደገና ፡ በብዙ ፡ ተቆጣኝ ።

፳፩ ፤ ዳግመኛም ፡ የእንጊሬፌስ አብሮኮሮስ ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ካም ስት ፡ ቀን ፡ በማኅፀን ፡ ኑሮ ፡



በመለኮቱ ፡ ፴ተ ፡ አውራኃ ፡ ወኃ ምስተ ፡ ዕለተ ፡ ወእመ ፡ ይከውን በምዕር ፡ በተዋልጦ ፡ ኃደረ ፡ ውስተ ፡ ሥጋ ፡ ሰብእ ።

፳፪ ፤ ወይቤ ፡ ዮሐንስ ፡ መጠንዝ፡ ነጊረ ፡ ኢይክል ፡ አንሰ ፡ በሥጋ ፡ መዋቲ ፡ ዘተሳትፎተ ፡ መለኮትሰ ፡ ሕያው ፡ ድኅረ ፡ ተሳተፈ ፡ ሥጋ፡ ሞተ ፡ ከማሁ ።

፳፫ ፤ ወዘንቱ ፡ መለኮት፡ ተአ ዚዞ ፡ ከመ ፡ ገብር ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ ፍጹመ ፡ ወበእንቲኣነ ፡ ነሥአ ሞተ ፡ ዘዚኣነ ፡ ወእንቲኣሁ ፡ ሕይወተ ፡ ወሀበነ ።

፳፬ ፡ ወእምዝ ፡ ነሥአሙ ፡ ዮሐ ንስ ፡ ለ፴ቱ ፡ አኃው ፡ ወአርአዮሙ፡ ትእምርተ ፡ ልደቱ ፡ በቤተልሔም፡ ዘተወልደ ፡ ቦቱ ፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ።

፳፭ ፤ ወካዕበ ፡ አርአዮሙ ፡ ትእምርተ ፡ ጥምቀቱ ፡ በዮርዳ ኖስ ፡ ዘወረደ ፡ ቦቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እምሰማይ ፡ በአምሳለ ፡ ርግብ ፡ ጸዓዳ ፡ ወአብኒ ፡ ከመ ፡ ስምዓ ፡ ኮነ ፡ ላዕለ ፡ ወልዱ ፡ ዋሕድ ፡ ወበህየ ፡ ተግህደ ፡ ምሥ ጢረ ፡ ሥላሴሁ ።

፳፮ ፤ ወሥልሰ ፡ አርአዮሙ፡ ገዳመ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ዘጾመ ፡ ቦቱ ፵ ፡ መዓልተ ፡ ወ፵ ፡ ሌሊተ ፡ ወህየ ፡ ሰገደ ፡ ወአስተብረከ ፡

በመለኮትነቱ ፡ የለበሰውን ፡ ሥጋ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በመለወጥ ፡ በሰው ሥጋ ፡ የአደረ ፡ ቢሆንስ ፡ ቢለው ።

፳፪ ፤ ዮሐንስም ፡ መልሶ ፡ እኔ ይህን ፡ ያህል ፡ ለመናገር ፡ ችሎታ ፡ የለኝም ፡ እኔ ፡ ሟች ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ ሕያው ፡ መለኮት ፡ ግን ፡ ሥጋን ፡ ከለበሰ ፡ በኋላ ፡ በሥ ጋው ፡ ሙቷል ፡ አለ ።

፳፫ ፤ ይኸውም ፡ መለኮት ፡ እንደኛ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ እንደሰው ፡ በመታዘዝ ፡ የኛን ፡ ሞት ፡ ተቀብሎ ፡ የሱን ፡ ሕይወት ለኛ ፡ ሰጠን ።

፳፬ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዮሐንስ፡ ሁለቱን ፡ ወንድማማች ፡ ወስዶ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ የተወለደበትን ፡ የልደ ቱን ፡ ምልክት ፡ አሳያቸው ።

፳፭ ፡ ዳግመኛም ፡ በዮርዳኖስ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በነጭ ፡ ርግብ ተመስሎ ፡ ከሰማይ ፡ የወረደበት ንና ፡ አብም ፡ ከአንድ ፡ ልጁ ፡ እን ደሆነ ፡ ምስክር ፡ የሆነበትን ፡ በዚ ህም ፡ ላይ ፡ የሦስትነቱ ፡ ምሥ ጢር ፡ የተገለጸበትን ፡ የጥምቀ ቱን ፡ ምልክት ፡ አሳያቸው ።

፳፮ ፤ ሦስተኛም ፡ በቆሮንቶስ፡ ገዳም ፡ አርባ ፡ ቀንና ፡ አርባ ፡ ሌሊት ፡ የጾመበትን ፡ በዚህም ፡ ላይ ከሦስትነቱና ፡ ከትስብእቱ ፡ አኗ ኗር ፡ ወይም ፡ አንድነት ፡ ጉድ

**ለሥላሴሁ** ፡ እንዘ ፡ ኢየዓርቅ ፡ እምህላዌ ፡ **ሥላሴሁ** ፡ ወሥጋዌሁ ።

፳፯ ፤ **ወሶበ ፡ ፈጸሙ ፡ ዘንተ** ራእየ ፡ በራብዕት ፡ ሰዓተ ፡ ሌሊት ፡ ወሰዶሙ ፡ ወአብጽሖሙ ፡ ውስተ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ኀበ ፡ ተጋብኡ ፡ አይሁድ ፡ ወረበናት ፡ ሕዝብ ፡ ኵሎሙ ፡ ኀበ ፡ አቅጸሩ ፡ ቦቱ ፡ ሰማዕተ ፡ ሐሰት ፡ በእንተ ፡ በይነ ፡ ምሕረቱ ፡ ወጽድቁ ።

፳፰ ፤ **ወእምዝ ፡ ነሥእሙ ፡** ለ፲ቱ ፡ አኃው ፡ በጾም ፡ ወበንጽሕና ፡ ወበተሐርሞ ፡ ወበጽሙና ፡ ወአብጽሖሙ ፡ መካነ ፡ ቀራንዮ ፡ ኀበ ፡ ተሰቅለ ፡ **እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡** እንዘ ፡ አኃዜ ፡ ኃይል ፡ ውእቱ ፡ ወሰገዱ ፡ ህየ ፡ ወጸለዩ ።

፳፱ ፤ **ወህየ ፡ ኃሊፎሙ ፡ሕቀ ፡** ረከቡ ፡ እንዘ ፡ ይገብሩ ፡ ይባቤ ፡ መልእክተ ፡ ሰማይ ፡ በበማኅበሮሙ ፡ ወውሉጥ ፡ ስብሐቲሆሙ ።

፴ ፤ **ኪሩቤል ፡ ወሱራፌል ፡** ይሰፍሑ ፡ ክነፊሆሙ ፡ እንዘ ፡ ይከድኑ ፡ በመዓዝነ ፡ **መስቀል ፡** ወትላቋሆሙ ፡ እልፍ ፡ አእላፋት ፡ በበጸታሆሙ ፡ ይሴብሕዎ ፡ ወይዜምርዎ ፡ ለልዑል ፡ በውሉጥ ፡ ቃና ፡ ወበጥዑም ፡ ዜማ ።

ለት ፡ ሳይኖርበት ፡ በሰውነቱ የሰገደበትንና ፡ የአኰነበሰበትን አሳያቸው ።

፳፯ ፤ **ከሌሊቱ ፡ በአራተኛው** ሰዓት ፡ ይህን ፡ ምልክት ፡ ወይም ፡ ራዕይ ፡ በፈጸሙ ፡ ጊዜ ፡ አይሁድና ፡ የሕዝብ ፡ ሊቃውንቶች ፡ ሁሉ ፡ ከተሰበሰቡበትና ፡ በእውነተኛነትና ፡ በቸርነቱ ፡ ፈንታ ፡ የሐሰት ፡ ምስክር ፡ ወደቆጠሩበት ወደቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወስዶ ፡ አደረሳቸው ።

፳፰ ፤ **ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በጾምና ፡ በጸሎት ፡** ሁሉን ፡ በመተውና ፡ በብቸኝነት ፡ አድርጎ ፡ **ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡** ኃይል በሱ ፡ እጅ ፡ ሲሆን ፡ ወደተሰቀለበት ፡ ወደቀራንዮ ፡ ቦታ ፡ አደረሳቸው ።

፳፱ ፤ **ከዚያ ፡ ጥቂት ፡ እልፍ ፡** እንዳሉ ፡ የሰማይ ፡ መላእክት ፡ በየአንዳንዳቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ የዝማሬ ፡ ምስጋና ፡ ሲያመሰግኑ ፡ አገኙ ።

፴ ፤ **ቍጥራቸው ፡ እልፍ ፡** አእላፋት ፡ የሆኑ ፡ መላእክት ፡ ኪሩቤልና ፡ ሱራፌልም ፡ በመስቀሉ ፡ ዙሪያ ፡ ክንፋቸውን ፡ ዘርግተው ፡ በየወገናቸው ፡ ለልዑል ፡ ጌታችን ፡ ጣዕሙ ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ ዜማ ፡ ይዘምሩለታል ፡ ያመሰግኑታልም ።



፴፩ ፤ **ወበህየ ፡ አርአዮሙ ፡** ዮሐንስ ፡ ትእምርተ ፡ ሥጋሁ ፡ ምስለ ፡ መለኮት ፡ ዋሕድ ፡ ወዕበየ ፡ መለኮት ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ ቅዱስ ፡ እንዘ ፡ ይፈለፍል ፡ ደመ ፡ ቀይሐ ፡ እምገቦሁ ።

፴፪ ፤ **ወዝንቱ ፡ ደመ ፡ መለኮት ፡** ለስርየተ ፡ ኃጢአት ፡ ወዝንቱ ፡ ሥጋ ፡ ቅዱስ ፡ መብልዓ ፡ ፍሥሐ ፡ ወሐሤት ፡ ወሕይወት ፡ ለመሃይምናን ፡ ወክብረ ፡ ለቅዱሳን ፡ ውእቱ ።

፴፫ ፤ **ወእምዝ ፡ እንዘ ፡ ያነክሩ ፡** ወይደመሙ ፡ በአስተጋብኦ ፡ ኅሊናት ፡ ወለለብዎ ፡ መጻሕፍት ፡ ከሠተ ፡ ሎሙ ፡ **እግዚአብሔር ፡** ምሥጢረ ፡ መለኮት ።

፴፬ ፤ **ወከመ ፡ ነሥአ ፡ አሐዱ ፡** መልአከ ፡ ደመ ፡ እምገቦሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወከመ ፡ ነዝኃ ፡ ኵሎ ፡ ዓለመ ፡ ወበዝንቱ ፡ ደመ ፡ መለኮት ፡ ይኩን ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ ቅዱስ ፡ እምኃጢአት ።

፴፭ ፤ **ወበቀዳሚ ፡ ጠሚዖ ፡ ደመ ፡** በክነፊሁ ፡ ሐረ ፡ ምድረ ፡ ትግራይ ፡ እንተ ፡ ትሰመይ ፡ ሀገረ ፡ ናግራን ፡ ዘተቀትሉ ፡ ባቲ ፡ ሰማዕታት ፡ ነዝኃ ፡ ውስቴታ ።

፴፮ ፤ **ወካዕበ ፡ ሐረ ፡ ነዝኃ ፡ ደመ ፡ እግዚእነ ፡** መካነ ፡ አረጋዊ ፡ ዘተሰምየት ፡ ደብረ ፡ዳሞ ፡

፴፩ ፤ **ዮሐንስም ፡ በዚሁ ሥጋው ፡** ከመለኮት ፡ ጋር ፡ የመለኮትም ፡ ልዕልና ፡ ከቅዱስ ፡ ሥጋው ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሁኖ ፡ ከቀኝ ፡ ጐኑ ፡ ቀይ ፡ ደም ፡ ሲፈስ ፡ አሳያቸው ።

፴፪ ፤ **ይህም ፡ የመለኮት ፡** ደም ፡ ለኃጢአት ፡ ማስተስርያ ፡ ይኸውም ፡ ቅዱስ ፡ ሥጋ ፡ ፍጹም ፡ የደስታ ፡ ምግብ ፡ ለምእመናን ፡ ሕይወትና ፡ ለቅዱሳን ፡ መከበሪያ ፡ ነው ።

፴፫ ፤ **ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኅሊናቸውን ፡** በመሰብሰብ ፡ እየተገረሙና ፡ እየተደነቁ ፡ ሳለ ፡ የመለኮትን ፡ ምሥጢርና ፡ የመጻሕፍትን ፡ ትርጓሜ ፡ ያውቁ ፡ዘንድ ፡ **እግዚአብሔር ፡** ገለጠላቸው ።

፴፬ ፤ **አንዱ ፡ መልአክም ፡** ዓለም ፡ ሁሉ ፡ በዚሁ ፡ በመለኮት ፡ ደም ፡ ከኃጢአት ፡ የነጻ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ከጌታችን ፡ ጐን ፡ የፈሰሰውን ፡ ደም ፡ ወስዶ ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ እንደረጨ ፡ አሳያቸው ።

፴፭ ፤ **መጀመሪያ ፡ ደሙን** በክንፉ ፡ ይዞ ፡ ብዙ ፡ ሰማዕታት ፡ ከተገደሉባት ፡ ትግራይ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ወዳለች ፡ ወደናግራን ፡ ሂዶ ፡ በውስጧ ፡ ረጨ ።

፴፮ ፤ **ዳግመኛም ፡ እግዚአብሔርን ፡** በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳሉ ፡ ከሚያገለግሉት ፡ ከቡራን ፡

እንተ ፡ ውስቴታ ፡ የኃድሩ ፡ ቅዱሳን ፡ ወክቡራን ፡ መምህራን ፡ እለ ፡ ያሠምርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሕይወቶሙ ።

፴፯ ፤ ወዳግመ ፡ አንሥአ ፡ ለይእቲ ፡ ደብር ፡ ወዓተባ ፡ በደመ፡ መስቀሉ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ቡርክተ ፡ ወመዋርስተ ፡ ለኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ።

፴፰ ፤ ወዓዲ ፡ ሠረረ ፡ ወሖረ ፡ ወበጽሐ ፡ ምድረ ፡ አኵሱም ፡ ወዖደ ፡ ውስተ ፡ አድያሚሃ ፡ ወአዕጻዲሃ ፡ ለጽዮን ፡ ወዓተባ ፡ በደመ ፡ እግዚእነ ፡ ማኅየዊ ።

፴፱ ፤ እስመ ፡ ምድረ ፡ አኵሱም ፡ ተመሰለት ፡ መካነ ፡ ቀራንዮ ፡ እንተ ፡ ተሰቅለ ፡ ባቲ ፡ እግዚእነ ፡ ወበውስቴታ ፡ አንሥአ ፡ ባቲ ፡ ሙታነ ፡ ወባረካ ፡ በደሙ ።

፵ ፤ ወእለ ፡ ሀለዉ ፡ ሀየ ፡ ፺ ፡ ወ፱ቱ ፡ ነገደ ፡ መላእክት ፡ ምስለ ፡ ሠራዊቶሙ ፡ እንዘ ፡ ይሴብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቦ ፡ እለ ፡ ይቤሉ ፡ በመዝሙር ፡ እስመ ፡ ኃረያ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለጽዮን ፡ ከመ ፡ ትኩኖ ፡ ማኅደሮ ።

፵፩ ፤ ወቦ ፡ እለ ፡ ይቤሉ ፡ መሠረታቲሃ ፡ ውስተ ፡ አድባር ፡ ቅዱሳን ፡ ያበድሮን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአናቅጸ ፡ ጽዮን ።

መምህራንና ፡ ቅዱሳን ፡ መነኰሳት ፡ ወደሚኖሩባት ፡ ደብረ ፡ ዳሞ ፡ ወደምትባለው ፡ ወደ ፡ አረጋዊ ፡ ገዳም ፡ ሄዶ ፡ የጌታችንን ፡ ደም ፡ ረጨ ።

፴፯ ፤ ዳግመኛም ፡ ይህችን ፡ ደብር ፡ የተባረከችና ፡ የተቀደሰች ፡ ለቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡ የደስታ ፡ ጉልት ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በደመ ፡ መስቀሉ ፡ ባረካት ።

፴፰ ፤ እንደገና ፡ በክንፉ ፡ በሮ ፡ ሄደና ፡ አኵሱም ፡ ምድር ፡ ደርሶ ፡ የጽዮንን ፡ ዙሪያዋንና ፡ ዓጸዶቿን ሁሉን ፡ አዳኝ ፡ በሆነ ፡ በጌታች፡ ፡ ደም ፡ ረጫት ።

፴፱ ፤ የአኵሱም ፡ ምድር ፡ ጌታችን ፡ በደሙ ፡ እንደባረካት ፡ ሙታንንም ፡ እንዳሥነሣባት ፡ እንደ ፡ ተሰቀለባትም ፡ እንደቀራንዮ ፡ ትመሰላለችና ።

፵ ፤ በዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ዘጠና ፡ ዘጠኙ ፡ ነገደ ፡ መላእክትም ፡ ከሠራዊቶቻቸው ፡ ጋር ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገኑ ፡ ጽዮንን ፡ እግዚአብሔር ፡ መረጣት ፡ ማደሪያ ፡ ትሆነውም ፡ ዘንድ ፡ ወደዳት ፡ በማለት ፡ የሚዘምሩ ፡ አሉ ።

፵፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ የጽዮንን ፡ በሮች ፡ ይወዳቸዋል ፡ መሠረቶቿም ፡ በቅዱሳን ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ናቸውና ፡ እያሉ ፡ የሚዘምሩም ፡ አሉ ።



፵፪ ፤ ወአስተናሥአ ፡ ለይእቲ ፡ ደብር ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪሃ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ኃረየ ፡ ወአክበረ ፡ ኪያሃ ፡ ትኩን ፡ ማኅደረ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፵፫ ፤ ወይወርድ ፡ ላዕሌሃ ፡ ጠለ ፡ በረከት ፡ ከመ ፡ አድባረ ፡ ጽዮን ፡ ዘይወርድ ፡ ለለጊዜሁ ፡ ጸጋ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ላዕሌሆን ።

፵፬ ፤ ወመልዕልተ ፡ ኵነ ፡ ንድቀ ፡ አቅማሪሃ ፡ ወሱራሬሃ ፡ ዘወርቅ ፡ ወአዕማዲሃኒ ፡ ዘብሩር ።

፵፭ ፤ ወባረኮ ፡ ዘንተ ፡ ተንሥአ ፡ ወሠረረ ፡ በክነፊሁ ፡ እስከ ፡ የዓርግ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ ሐይቅ ፡ ዘውእቱ ፡ መቃብረ ፡ አበው ።

፵፮ ፤ ወበማእከሌሁ ፡ ሀለዉ ፡ ውሉዱ ፡ ለአባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞአ ፡ መፍቀሬ ፡ ንጽሕ ፡ ወጸሎት ፡ ጽሙድ ፡ ለአምላኩ ፡ ወለስብሐቲሁ ።

፵፯ ፤ ወዝንቱ ፡ አባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞአ ፡ ዘሠርዓ ፡ ሥርዓተ ፡ ቀኖና ፡ ወበሊዐ ፡ በሐፌ ፡ ገጽ ።

፵፰ ፤ አሠነየ ፡ ሎሙ ፡ ለውሉዱ ፡ ቆጽለ ፡ መብልዖሙ ፡ ወአስተጋብአ ፡ ሎሙ ፡ ኵሎ ፡ ተግባሮሙ ።

፵፱ ፤ እስመ ፡ በዝኁ ፡ ደቂቁ ፡ ለአባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞአ ፡ አበ ፡

፵፪ ፤ ይህችን ፡ ደብር ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማደሪያ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቀረባት ፡ እሱ ፡ መርጦ ፡ አክብሯታልና ።

፵፫ ፤ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጸጋ ፡ በየጊዜው ፡ በጽዮን ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ እንደሚወርድ ፡ ሁሉ ፡ በሷም ፡ ላይ ፡ የበረከት ፡ ጠል ፡ ልምላሜ ፡ ይወርዳል ።

፵፬ ፤ መሠረቷ ፡ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ ሁኖ ፡ አዕማዱ ፡ የወርቅ ፡ ምሰሶዎቿም ፡ የብር ፡ ናቸው ።

፵፭ ፤ ይህንን ፡ ከባረከ ፡ በኋላ ፡ የአባቶች ፡ መቃብር ፡ ወደሚገኝበት ፡ ወደ ፡ ሐይቅ ፡ ደብር ፡ ለመውጣት ፡ ተነሥቶ ፡ በክንፉ ፡ በረረ ።

፵፮ ፤ ለፈጣሪው ፡ ምስጋና ፡ የተገዛ ፡ ጸሎትንና ፡ ንጽሕናን ፡ የሚወድ ፡ የአባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞአ ፡ ልጆችም ፡ በመካከሉ ፡ ይገኙበታል ።

፵፯ ፤ ይኸውም ፡ አባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞአ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሕግንና ፡ ደክሞ ፡ ሠርቶ ፡ የመብላትን ፡ ሥርዓት ፡ ያስተማረ ፡ ነው ።

፵፰ ፤ ለልጆቹም ፡ የቅጠል ፡ አበላልንና ፡ ሌላውንም ፡ የሚሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ አሳምሮ ፡ ያዘጋጀላቸው ፡ ነው ።

፵፱ ፤ በበጐ ፡ ምግባርና ፡ በዕውቀት ፡ ያማሩ ፡ የመንፈሳው

መንኰሳት ፡ መንፈሳውያን ፡ ወመንፈሳውያት ፡ ሠናያን ፡ ምግባር ፡ ወአእምሮ ።

፶ ፤ **ወአፈድፈዱ ፡ ቀኖና ፡** እምዘሠርዕዎ ፡ አበው ፡ እንበለ ፡ አንጐርጕሮ ፡ ወተጓህልዎ ፡ በፍቅረ ፡ **መንፈስ ፡ ቅዱስ ።**

፶፩ ፤ **ወኮኑ ፡ የዋሃነ ፡ ከመ ፡ ርግብ ፡ ወከመ ፡ አባግዕ ፡** ሥቡሓን ፡ አዕላፍ ፡ እለ ፡ ተገድፉ ፡ ውስተ ፡ መቅደስ ፡ እምነ ፡ ምሥዋዒሁ ፡ ለአብርሃም ፡ በጊዜ ፡ ፀአቱ ፡ ምድረ ፡ ካራን ።

፶፪ ፤ **አኮ ፡ ከመ ፡ አባግዕ ፡** እለ ፡ ተቀርጸ ፡ ፀጉረ ፡ ዘባኖን ፡ አላ ፡ ከመ ፡ ይሰመዩ ፡ ውሉደ **እግዚአብሔር ፡** አትሒቶ፡ ርእሶሙ።

፶፫ ፤ **ወአኮ ፡ ከመ ፡ አርጋብ** ወኢከመ ፡ ርግበ ፡ ኖኅ ፡ በማእከለ ፡ አይኅ ፡ አላ ፡ እሙንቱ ፡ እዙዛነ ፡ ኮኑ ፡ ለተልእኮት ፡ ለሰቢረ ፡ ዕፅ ፡ ወለቀዲሐ ፡ ማይ ፡ በቀሱት ።

፶፬ ፤ **እስመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡** ያጸንዖሙ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ተግባሮሙ ።

፶፭ ፤ **ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ አሆ ፡** በብሂሎቶሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ጻማ ፡ ብዙኅ ፡ ይትኤዘዙ ፡ በዓቢይ ፡ ትጋህ ።

ያንና ፡ የመንፈሳውያት ፡ መነኰሳት ፡ አባት ፡ የአባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞአ ፡ ልጆቹ ፡ በዝተዋልና ።

፶ ፤ **አባቶች ፡ ከወሰኑት ፡ ይልቅ ፡** እነሱ ፡ **በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፍቅር ፡** ያለተንኮልና ፡ ያለማንጐራጐር ፡ አብዝተው ፡ ይጾማሉና ።

፶፩ ፤ **እንደርግብ ፡ የዋሃን ፡** አብርሃም ፡ ከካራን ፡ ምድር ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ በመሠውያው ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ለመሥዋዕት ፡ እንደተዘጋጁ ፡ ምርጥ ፡ በጎችም ፡ ሆኑ ።

፶፪ ፤ **ጸጕራቸውን ፡ እንደ ፡** ተሸለቱ ፡ በጎች ፡ አይደሉም ፡ **የእግዚአብሔር ፡** ልጆች ፡ ተብለው ፡ እንዲጠሩ ፡ ራሳቸውን ፡ አዋረዱ ፡ እንጂ ።

፶፫ ፤ **እንደ ፡ ርግቦች ፡** ወይም ፡ በማየ ፡ አይኅ ፡ ጊዜ ፡ እንደሆነው ፡ እንደኖኅ ፡ ርግብ ፡ አይደሉም ፡ እነሱስ ፡ በእንስራ ፡ ውኃ ፡ ለመቅዳትና ፡ ዕንጨት ፡ ሰብሮ ፡ ለማምጣት ፡ ለአገልግሎት ፡ የተዘጋጁ ፡ ናቸው ።

፶፬ ፤ **በሥራቸው ፡ ሁሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡** ያጸናቸዋልና ።

፶፭ ፤ **ስለዚህ ፡ እሺ ፡ በጐ ፡** በማለታቸው ፡ ያለመታከት ፡ በትጋት ፡ ይታዘዛሉ ።



፶፮ ፤ **ወውእቱኒ ፡ መልአክ ፡** ዓተባ ፡ **በደመ ፡ እግዚእነ፡** ለዛቲ ፡ ደብር ፡ እስመ ፡ ይእቲ ፡ ደብር ፡ ማእከለ ፡ ባሕር ፡ ስፍሕት ።

፶፯ ፤ **ወእምዝ ፡ እንዘ ፡ ያነክር ፡** ውእቱ ፡ መልአክ ፡ ነገረ ፡ አምላክ ፡ ተንሥአ ፡ እስመ ፡ አዕረፈ ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ ዓባይ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ደብረ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ኃያል ፡ መነኰስ ፡ ሰዳዴ ፡ አጋንንት ፡ በኀይለ ፡ ጸሎቱ ፡ እምላዕለ ፡ ሰብእ ።

፶፰ ፤ **ወህየ ፡ ረከበ ፡ ፪ኤተ ፡ አናብስተ ፡** እንዘ ፡ ይትቀነዩ ፡ ሎቱ ፡ ምስለ ፡ ፪ቱ ፡ አልህምት ፡ ወእንዘ ፡ ያስተፋንዎሙ ፡ ለለዕለቱ ፡ በሰላም ። አብሐሙ ፡

፶፱ ፤ **ወሦዓ ፡ መሥዋዕተ ፡** አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ኀበ ፡ **እግዚአብሔር ፡** ከመ ፡ ኢይትበዓሱ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ እሉ ፡ አናብስት ፡ ወአናምርት ፡ ወአልህምትኒ ፡ ኀበ ፡ ወፈሩ ፡ ገዳመ ፡ ወከመ ፡ ይትናገሩ፡ ርቱዓ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ በልሳነ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

፷ ፤ **ወየሐውሩ ፡ ድኅሬሁ ፡** ወእምነ ፡ እሉ ፡ አሐዱ ፡ እመ ፡ ተርፈ ፡ ይጸንሕዎ ፡ ወለእመ ፡ ቀደመ ፡ አሐዱ ፡ ቀዊሞ ፡ ይጼውዖ ፡ ለዘጐንደየ ፡ በፍኖት ።

፶፮ ፤ **ይህም ፡ መልአክ ፡ በጌታችን ፡ ደም ፡** ባረካት ፡ እሷ ፡ ሰፊ ፡ በሆነ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ የምትገኝ ፡ ደሴት ፡ ናትና ።

፶፯ ፤ **ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይኸው ፡ መልአክ ፡ የአምላክን ፡** ሥራ ፡ እያደነቀ ፡ ተነሣና ፡ ከሰው ፡ ላይ ፡ በጸሎቱ ፡ ኃይል ፡ አጋንንትን ፡ ከሚያወጣ ፡ የኃያሉ ፡ መነኩሴ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ደብር ፡ ከምትሆን ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዓባይ ፡ ገብቶ ፡ ዓረፈ ።

፶፰ ፤ **በዚህም ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ አንበሶች ፡** ከሁለት ፡ ላሞች ፡ ጋር ፡ ሲገዙለትና ፡ በየቀኑም ፡ ሲያሠማሯቸው ፡ አብረው ፡ የሚኖሩበትን ፡ መመሪያ ፡ ሲሰጣቸው ፡ ተመለከተ ።

፶፱ ፤ **አባ ፡ ሳሙኤልም ፡**እሊህ፡ አንበሶችና ፡ ነምሮች ፡ ላሞችም ፡ በተሠማሩበት ፡ ቦታ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እንዳይጣሉና ፡ በሰው፡ ልጅ ፡ ቋንቋ ፡ እንዲነጋገሩ ፡ ወደ ፡ **እግዚአብሔር ፡** መሥዋዕት ፡ አቀረበ ።

፷ ፤ **በኋላ ፡ በኋላውም ፡ ይከተሉታል ፡** ከነሱ ፡ አንዱ ፡ ወደኋላ ፡ ቢቀር ፡ ቆመው ፡ ይጠብቁታል ፡ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ ቀድሞ ፡ የሔደ ፡ እንደሆነ ፡ ወደኋላ ፡ የዘገየውን ፡ እየጠሩ ፡ ያበረታቱታል ።

፷፩ ፤ በኃይለ ፡ ጸሎቱ ፡ ለአባ ፡ ሳሙኤል ፡ አናብስት ፡ ወአናምርት ፡ ይትኤዘዙ ፡ ሎቱ ።

፷፪ ፤ እስመ ፡ ከመዝ ፡ ገብረ ፡ ወአኰነነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለቅዱሳኒሁ ፡ ኄሩያን ።

፷፫ ፤ ወአልቦ ፡ ኑፋቄ ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡ አልህምት ፡ በአናብስት ፡ ወበአናምርት ፡ እንዘ ፡ አጽራሪሆሙ ፡ በሙፋሪሆሙ ፡ ውስተ ፡ ሐቅል ።

፷፬ ፤ እፎኑ ፡ ገብረ ፡ ዘንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኪነ ፡ ጥበቡ ፡ ዕጹብ ፡ ወመንክር ፡ ውእቱ ፡ ለአምላክነ ።

፷፭ ፤ እስመ ፡ ዘንተ ፡ ገብረ ፡ አምላክነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለአባ ፡ ሳሙኤል ፡ ወበእንተ ፡ አፍቅሮተ ፡ ቅድስናሁ ።

፷፮ ፤ ወመላእክትኒ ፡ ከመ ፡ አናብስት ፡ ወአናምርት ፡ ይሔውጽዎ ፡ ለለጊዜሁ ።

፷፯ ፤ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ እንዘ ፡ ያስተዓፅብ ፡ ውእቱ ፡ መልአክ ፡ ዓተባ ፡ በደመ ፡ እግዚእነ ፡ ለዛቲ ፡ ደብር ፡ ዓባይ ።

፷፰ ፤ ወለእሉኒ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ፡ ፯፻ ፡ ደቂቁ ፡ ለአባ ፡ ሳሙኤል ፡ እለ ፡ ነሥኡ ፡ እምእዴሁ ፡ ቆብዓ ፡ ወአስኬማ ፡ ባረኮሙ ።

፷፩ ፤ ስለዚህ ፡ ለአባ ፡ ሳሙኤል ፡ በጸሎቱ ፡ ኃይል ፡ አንበሶችና ፡ ነምሮች ፡ ይታዘዙለታል ።

፷፪ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለተመረጡት ፡ ቅዱሳኖቹ ፡ እንደዚህ ፡ እንዲገዙላቸው ፡ ያደርጋልና ።

፷፫ ፤ አንበሶቹና ፡ ነምሮቹ ፡ ጠላቶቻቸው ፡ ሲሆኑ ፡ በዱር ፡ በሚሠማሩበት ፡ ጊዜ ፡ በላሞቹ ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ ይጣሉናል ፡ የሚል፡ መጠራጠር ፡ አያድርባቸውም ፡

፷፬ ፤ እግዚአብሔር ፡ ይህንን ፡ እንዴት ፡ አደረገ ? የአምላካችን ፡ የጥበቡ ፡ ኃይል ፡ ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ ነው ።

፷፭ ፤ አምላካችን ፡ ስለ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ጸሎትና ፡ ቅድስናውን ፡ ስለመውደዱ ፡ ይህንን ፡ አድርጓልና ።

፷፮ ፤ መላእክትም ፡ እንደአንበሶቹና ፡ እንደነምሮቹ ፡ በየጊዜው ፡ ይጐበኙታል ።

፷፯ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ይኸው ፡ መልአክ ፡ በዚህ ፡ እየተደነቀ ፡ ይህችን ፡ ደብረ ፡ ዓባይን ፡ በጌታችን ፡ ደም ፡ ባረካት ።

፷፰ ፤ በውስጧ ፡ የሚኖሩትን ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ የሚሆኑ ፡ ቆብና ፡ አስኪማ ፡ በእጁ ፡ የተቀበሉትን ፡ የአባ ፡ ሳሙኤልንም ፡ ልጆች ፡ ባረካቸው ።



፷፱ ፤ እስመ ፡ ርእሰ ፡ ባሕታውያን ፡ ውእቱ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ።

፸ ፤ ወበእንተዝ ፡ ደቂቁ ፡ አፈድፈዱ ፡ ገቢረ ፡ ሠናይ ፡ በመዓልት ፡ ወበሌሊት ፡ ከመ ፡ መላእክተ ፡ እግዚአብሔር ።

፸፩ ፤ ወኮኑ ፡ ከመ ፡ ውሉድ ፡ ዘሥጋ ፡ እንዘ ፡ ይትኤዘዙ ፡ ሎቱ ፡ በኵሉ ።

፸፪ ፤ ወውእቱኒ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ኢይትመየጥ ፡ ለፌ፡ ወለፌ፡ ጎበ ፡ ቆመ ፡ ለጸልዮ ፡ ከመ ፡ ዓምድ ፡ ትኩል ፡ ዘኢያንቀለቅሎ ፡ ኃይለ ፡ ነፋሳት ፡ ዘዓረብ ፡ ወሠርቅ ።

፸፫ ፤ ወለተልእኮ ፡ ቀኖና ፡ ሰዓታት ፡ ዘመዓልት ፡ ወዘሌሊት ፡ እስከ ፡ ይትፌጸም ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወቱ ፡ በትእዛዘ ፡ አበው ፡ ቀደምት ፡ ርቱዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ አባ ፡ እንጦንዮስ ፡ ወአባ ፡ መቃርዮስ ፡ ዘወሀቦ ፡ አስኬማ ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ዑራኤል ፡ ዓቃቤ ፡ ርእሶሙ ፡ ለእንጦንስ ፡ ወመቃርስ ።

፸፬ ፤ ወበእንተዝ ፡ ተውህበ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕለ ፡ ዛቲ ፡ ደብር ፡ ዓባይ ፡ መርዔተ ፡ ጾማዕቱ ፡ ለአባ ፡ ሳሙኤል ፡ ወላዴ፡ አባግዕ ፡ አእላፍ ።

፷፱ ፤ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ በጾምና ፡ በጸሎት ፡ የባሕታውያን ፡ ሁሉ ፡ የበላይ ፡ ነውና ።

፸ ፤ ስለዚህ ፡ በጐ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መላእክት ፡ ሆኑ ።

፸፩ ፤ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ወለዳቸው ፡ ልጆች ፡ ሁነው ፡ በሁሉም ፡ ነገር ፡ ይታዘዙለታል ።

፸፪ ፤ አባ ፡ ሳሙኤልም ፡ ለጸሎት ፡ ከቆመበት ፡ ቦታ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሳይል ፡ የነፋሳት ፡ ኃይል፡ በምሥራቅም ፡ ሆነ ፡ በምዕራብ ፡ ሊያነዋውጡት ፡ እንደማይቻል ፡ እንደተተከለ ፡ ዓምድ ፡ ነው ።

፸፫ ፤ የእንጦንዮስና ፡ የመቃርዮስ ፡ ጠባቂያቸው ፡ የሆነ ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ ዑራኤል ፡ ሃይማኖታቸው ፡ የቀና ፡ ቀደምት ፡ የሆኑ ፡ አባቶች ፡ በአባ ፡ እንጦንስና ፡ በአባ ፡ መቃርስ ፡ ትእዛዝ ፡ በተሰጠው ፡ አስኪማ ፡ የሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ሰዓቱን ፡ አክብሮ ፡ ለጸሎትና ፡ ለጾም ፡ እንዲተጋ ፡ እንደተተከለ ፡ ዓምድ ፡ አጸናው ።

፸፬ ፤ የአእላፍ ፡ በጎች ፡ አባት ፡ የሆነ ፡ የአባ ፡ ሳሙኤል ፡ የመንጎቹ ፡ ዋሻ ፡ የሆነች ፡ ለዚች ፡ ለደብረ ፡ ዓባይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ተሰጣት ።

፱ ፤ ወሶቤሃ ፡ ጸለየ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወባረከ ፡ አባ ፡ ዮሐኒ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ወወረደ ፡ እሳት ፡ እምሰማይ ፡ ወበልዖሙ ፡ እንዘ ፡ ኢይተርፍ ፡ ምንተኒ ፡ እምእሉ ።

፲ ፤ ወይከውን ፡ ኍልቆሙ ፡ ለእለ ፡ ተቀትሉ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ ፸ወ፭፻ ፡ አጋንንት ፡ ወመሠርያን ፡ ዘምስለ ፡ መምለክያነ ፡ ጣዖት ፡ በኃይለ ፡ ጸሎቱ ፡ ለአባ ፡ ዮሐኒ ፡ ጻድቅ ።

፲፩ ፤ ወአሜሃ ፡ ውእቱ ፡ መልአክ ፡ ቀደሰ ፡ ቦለንታሃ ፡ ለዛቲ፡ ደብር ፡ በደሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

፲፪ ፤ ወበዝንቱ ፡ ነገር ፡ አባ ዮሐኒ ፡ ከመ ፡ ተፈሥሐ ፡ ወተሐሥየ ፡ መላእክተ ፡ ሰማይኒ ፡ ተፈሥሑ ፡ ወተሐሠዩ ፡ ወይቤሉ ፡ ስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሰማያት ፡ ወሰላም ፡ በምድር ፡ ሥምረቱ ፡ ለሰብእ ፡ ዘገብረ ፡ መንክረ ፡ በላዕለ ፡ ቅዱሳኒሁ ።

፲፫ ፤ ወእምድኅረ ፡ ሥርዓተ ፡ ማኅበር ፡ አስተጋብአ ፡ ኵሎ ፡ ቅዱሳነ ፡ ኅሩያኒሁ ፡ ሠናያነ ፡ ምግባር ፡ ዘጽድቅ ፡ በአስተብቍዖ ፡ ከመ ፡ ያስተኃፍር ፡ ኃይለ ፡ ጸላዒ ።

፲፬ ፤ ወከመ ፡ ይትከሠት ፡ ሥነ ምግባሪሁ ፡ ለአምላክነ ፡ ለእለ ፡

፱ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ዮሐኒ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለየና ፡ በመስቀል ፡ አምሳል ፡ አማትቦ ፡ ቢባርክ ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ወርዶ ፡ ከነሱ ፡ አንድ ፡ ስንኳን ፡ ሳይቀር ፡ አቃጠላቸው ።

፲ ፤ በዚችው ፡ ዕለት ፡ በጻድቁ፡ በአባ ፡ ዮሐኒ ፡ የጸሎት ፡ ኃይል ፡ ያለቁት ፡ አጋንንትና ፡ ሟርተኞች ፡ እንዲሁም ፡ የጣዖታት ፡ ተገዦች ፡ የሆኑ ፡ ቍጥር ፡ ሰብዓ ፡ አምስት ፡ እልፍ ፡ ወይም ፡ ሰብዓ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ናቸው ።

፲፩ ፤ መልአኩም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ይህችን ፡ ደብር ፡ ሁለንተናዋን ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደም ፡ ቀደሳት ።

፲፪ ፤ በዚህም ፡ ነገር ፡ ይኸው አባ ፡ ዮሐኒ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ እንዳለው ፡ የሰማይ ፡ መላእክትም ፡ በሰማይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ በምድርም ፡ ሰላም ፡ ይሁን ፡ ሰውን ፡ በመውደዱ ፡ ለወዳጆቹ ፡ ለቅዱሳን ፡ ይህን ፡ ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ ሥራ ፡ ሠርቷልና ፡ በማለት ፡ ተደሰቱ ።

፲፫ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የጠላትን ፡ ኃይል ፡ ያሳፍር ፡ ዘንድ ፡ በጸሎትና ፡ በጽድቅ ፡ ሥራ ፡ ያጌጡ ፡ የተመረጡ ፡ ቅዱሳኖቹን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቦ ፡ ያንድነት ፡ ሥራ ፡ ሠራ ።

፲፬ ፤ በቆብና ፡ በአስኬማ ፡ ከሱ ፡ ለተወለዱት ፡ የአምላካችን ፡



ተወልዱ ፡ እምኔሁ ፡ በቆብዕ ፡ ወአስኬማ ።

፲፭ ፤ ወኮነ ፡ ኍልቆሙ ፡ ፯፻፹ ፡ ዘእንበለ ፡ አንስት ፡ ወደቂቅ ።

፲፮ ፤ ወእንዘ ፡ ውእቶሙ ፡ ጽሩቃን ፡ ወብዙኃን ፡ ሰብአ ፡ ማኅበር ፡ ቦሙ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ሰላም ፡ ወፍቅር ።

፲፯ ፤ ወአጽንዑ ፡ ሃይማኖተ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ አበዊነ ፡ ሐዋርያት ፡ ወኮኑ ፡ መፍቀርያነ ፡ ጾም ፡ ወጸሎት ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐዋርያ ፡ በመልእክቱ ፡ ተፋቀሩ ፡ በምልአ ፡ ልብክሙ ፡ ወጸሐቁ ፡ ለጸሎት ፡ ንዑሳኒክሙ ፡ ወዓቢያኒክሙ ፡ በፍቅረ ፡ አቡክሙ ፡ ሰማያዊ ።

፲፰ ፤ ወምእዎ ፡ ለሰይጣን ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ጸላዒክሙ ፡ ይጥህር ፡ ከመ ፡ አንበሳ ፡ ለውኂጦተክሙ ፡ ዘይቤ ፡ አንጽሑ ፡ በሕሊናሆሙ ።

፲፱ ፤ ወውእቱሰ ፡ ሰይጣን ፡ ያነብር ፡ ቂመ ፡ ወበቀለ ፡ ውስተ፡ ልበ ፡ ሰብእ ፡ ዘጽሉዕ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

፳ ፤ ወአዘዘ ፡ አባ ፡ ዮሐኒ ፡ ማኅበራኒሁ ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ ታቦተ ፡ ለምሥዋዕ ፡ ወለምህላ ፡ በስመ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ወበስመ ፡ ሚካኤል ፡ ወገብርኤል።

የቸርነቱ ፡ ሥራ ፡ ይገለጽ ፡ ዘንድ ።

፲፭ ፤ ቍጥራቸውም ፡ ከልጆችና ፡ ከሴቶች ፡ በቀር ፡ ሰባት ፡ ሺህ ፡ ሆነ ።

፲፮ ፤ እነሱም ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ማኅበራውያን ፡ ሲሆኑ ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ ፍቅርና ፡ ሰላም ፡ አላቸው ።

፲፯ ፤ ሐዋርያው ፡ ጴጥሮስ ፡ በመልእክቱ ፡ በሰማያዊ ፡ አባታችሁ ፡ ፍቅር ፡ ታናናሾቹም ፡ ታላላቆቹም ፡ ለጸሎት ፡ ትጉ ፡ ከልብ ፡ ሁናችሁም ፡ ተፋቀሩ ፡ እንዳለ ፡ ጾምንና ፡ ጸሎትን ፡ የሚወዱ ፡ ሁነው ፡ እንደ ፡ አባቶቻችን ፡ እንደሐዋርያት ፡ በክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ ጸኑ ።

፲፰ ፤ ባላጋራችሁ ፡ ሰይጣንን ፡ ድል ፡ አድርጉት ፡ እሱ ፡ ጠላታችሁ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ሊውጣችሁ ፡ ይጮሃልና ፡ ያለውን ፡ በልባቸው ፡ አስበዋልና ።

